# ሌኒን

## ካርል ማርክስና ትምህርቱ



የመላው ፡ ዓለም ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፤ ተባበሩ!

# ሌኒን

# ካርል ማርክስና ትምህርቱ

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

ተርጓሚው ፤ አራጋው ፡ ወርቁ ።

## ከማተሚያ ፡ ቤቱ ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ጽሑ ፎች ፡ የተተረጐሙት ፡ በሶቪዬት ፡ ኮሙኒስት ፡ ፓርቲ ፡ ማዕከላዊ ፡ ኮሚቴ ፡ ሥር ፡ በሚኪያ ሒያደው ፡ በማርክሲዝም ፡ ሌኒኒዝም ፡ ኢን ስቲቲዩት ፡ ከተዘጋጀው ፡ ከሌኒን ፡ ሥራ ፡ አ ምስተኛ ፡ እትም ፡ ነው ።

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ትር ጉም ፤ ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።

አድራሻው ፤
17, Zubovsky Boulevard, Moscow, U.S.S.R.

© የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ የአማርኛ ፡ ትርጉም ።
እ. ኤ. አ. 1979 ዓ. ም.

በሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ታተመ ።

Л $\frac{10102—181}{014(01)—79}$ -658 0101020000

## ማውጫ

| | ገጽ ፤ |
|---|---|
| የማርክሲዝም ፡ ሶስቱ ፡ ምንጮች ፡ እና ፡ ሶስቱ ፡ የተዋሀዱ ፡ አካሎች ። | ፭ |
| ካርል ፡ ማርክስ ። (አጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩና ፡ የማርክሲዝም ፡ ትንተና ።) | ፲፭ |
| መቅድም | ፲፭ |
| የማርክስ ፡ ትምህርት (ዶክትሪን) | ፳፭ |
| ፊሎሶፊካል ፡ ማቴሪያሊዝም ። | ፳፮ |
| ዲያሌክቲክስ ። | ፴ |
| የታሪክ ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ። | ፴፫ |
| የመደብ ፡ ትግል ። | ፴፯ |
| የማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርት ። | ፵ |
| ዋጋ ። | ፵ |
| ትርፍ ፡ ዋጋ ። | ፵፩ |
| ሶሺያሊዝም ። | ፶፱ |
| የወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ የትግል ፡ ስልቶች ። | ፷፭ |
| ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ። | ፸፫ |
| ማብራሪያዎች ። | ፹፱ |
| የስሞች ፡ ማብራሪያ ። | ፺፫ |

## የማርክሲዝም ፡ ሶስቱ ፡ ምንጮች ፡ እና ፡ ሶስቱ ፡ የተዋሀዱ ፡ አካሎች ።[1]

ማርክሲዝምን «እንደ ፡ ጠንቀኛ ፡ ዕምነት» የሚመለከተው ፡ በመላው ፡ የሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የማርክስን ፡ ትምህርቶች ፡ የሚያጥላላው ፡ መላው ፡ የቡርዥዋ ፡ ሳይንስ (የይፋውም ፡ ሆነ ፡ የሊበራሉ) በጸበኝነት ፡ እና ፡ በጥላቻ ፡ ይመለከተዋል ። በመደቦች ፡ ትግል ፡ በተመሠረተው ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ወገን ፡ የማይመርጥ ፡ የኅብረተሰብ ፡ ሶሺያል ፡ ሳይንስ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ማርክሲዝም ፡ የምንዳዕ ፡ ባርነትን ፡ አጥብቆ ፡ ሲቃወም ፤ የይፋ ፡ እና ፡ የሊበራል ፡ ሳይንስ ፡ ግን ፡ በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ይህንኑ ፡ ባርነት ፡ በሙሉ ፡ ይደግፋል ። የምንዳዕ ፡ ባርነት ፡ ባለበት ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ሳይንስን ፡ ወገን-የማይመርጥ ፡ አድርጎ ፡ መጠበቅ ፤ ባለፋብሪካዎች ፡ ካፒታል ፡ የሚያስገኘውን ፡ ጥቅም ፡ በመቀነስ ፡ ለሠራተኞች ፡ የሚከፈለውን ፡ ምንዳዕ ፡ ወገን ፡ ባለመምረጥ ፡ ይጨምሩ ፡ እንደሆን ፡ ብሎ ፡ እንደመጠባበቅ ፡ ያለ ፡ ጅላጅል ፡ የሆነ ፡ የየዋህ ፡ ግምት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ከዓለም ፡ ሥልጣኔ ፡ የዕድገት ፡ ጎዳና ፡ ውጭ ፡ ያንሠራራ ፡ የግትርነት ፡ እና ፡ በድን ፡ የሆነ ፡ ዕምነትን ፡ በመከተል ፡ ማርክሲዝም «የቡድን ፡ ዕምነት» እንዳልሆነ ፡ የፍልስፍና ፡ ታሪክ ፡ እና ፡ የኅብረተሰብ ፡ ሳይንስ ፡ ግልጥ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ያሳያሉ ። እንዲያውም ፡ በተገላቢጦሽ ፤ የብልህ ፡ ማርክስ ፡ ተግባር ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ አርቆ ፡ አስተዋይ ፡ አዕምሮ ፡ ቀርበው ፡ ለነበሩት ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሳቸውን ፡ መስጠት ፡ ነው ። የርሱ ፡ ትም

ሀርት ፤ ከፍልስፍና ፤ ከፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ እና ፡ ከሶሺ
ያሊዝም ፡ ታላላቅ ፡ ተመራማሪዎች ፡ ትምህርቶች ፡ በቀጥ
ታ ፡ እና ፡ ወዲያውኑ ፡ ተከትሎ ፡ የመጣ ፡ ትምህርት ፡ ነው ።
የማርክሲስት ፡ ትምህርት ፡ እውነት ፡ በመሆኑ ፡ ድል ፡
አድራጊ ፡ ነው ። የማርክሲስት ፡ ትምህርት ፡ የተሟላ ፡
እና ፡ የተጣጣመ ፡ ከመሆኑም ፡ በስተቀር ፤ ማናቸውንም ፡
ዓይነት ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ድኅረትን ፡ ወይንም ፡ የቡርዥ
ዋ ፡ ጭቆናን ፡ መደገፍን ፡ ፈጽሞ ፡ የሚቃወም ፡ የሆነ ፡
ርዕዮተ ፡ ዓለም ፡ ነው ። የአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመ
ን ፡ ምርጥ ፡ የሰዎች ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ላፈራው ፡ የጀርመ
ን ፡ ፍልስፍና ፤ የእንግሊዝ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ እና ፡
የፈረንሳይ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ሕጋዊ ፡ ወራሽ ፡ ነው ።
ሶስቱ ፡ ክፍሎቹ ፡ የሆኑትን ፡ እነዚህን ፡ ሶስቱን ፡ ምን
ጮች ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በአጭሩ ፡ የምናቀርበው ።

## I

የማርክሲዝም ፡ ፍልስፍና ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ነው ። በመ
ላው ፡ የአውሮፓ ፡ ዘመናዊ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፤ በተለይም ፡
በፈረንሳይ ፡ ውስጥ ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመ
ን ፡ ላይ ፡ የመካከለኛውን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አንቶ-ፈንቶ ፤
የአስተዳደር ፡ እና ፡ የአስተሳሰብን ፡ ባርነት ፡ በመቃወም ፡
ቆራጥ ፡ ትግል ፡ በሚካሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሳይን
ስን ፡ ትምህርት ፡ በሙሉ ፡ በመደገፍ ፤ አጉል ፡ እምነት
ን ፤ ግብዝነትን ፡ እና ፡ የመሳሰሉትንም ፡ በመቃወም ፤ ማ
ቴሪያሊዝም ፡ ቀጥተኛ ፡ እና ፡ ሀቀኛ ፡ የሆነ ፡ ፍልስፍና ፡
መሆኑን ፡ አስመስክሮአል ። ስለዚህም ፤ የዴሞክራሲ ፡
ጠላቶች ፡ ማቴሪያሊዝምን «ለመርታት» ፤ ለማሰናከል ፡
እና ፡ ዝናውንም ፡ ለማጉደፍ ፡ በማቀድ ፡ ዙሮ ፡ ዙሮ ፡ የሐ
ይማኖት ፡ ተገን ፡ እና ፡ ደጋፊ ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃሣባ
ዊ ፡ ፍልስፍናዎችን ፡ በተቻላቸው ፡ ሁሉ ፡ ሊያስፋፉ ፡ ሞ
ከሩ ።

ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ቆራጥ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ የፍል
ስፍና ፡ ማቴሪያሊዝምን ፡ ከመደገፋቸውም ፡ በስተቀር ፡ ከ
ዚህ ፡ መነሻ ፡ ማፈንገጥም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ስህተት ፡ እንደ
ሆነ ፡ ደግመው ፡ ደጋግመው ፡ አብራርተዋል ። አስተሳ
ሰባቸውንም «ኮሙኒስት ፡ ማኒፌስቶ» እንደተሰኘው ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ለማንኛውም ፡ መደባዊ ፡ ንቃት ፡ ላለው ፡ ሠራተኛ ፡
መመርያው ፡ በሚሆኑት ፡ እንደ «ሉድዊግ ፡ ፎየርባኽ»
እና «አንቲ-ዱሪንግ» በተሰኙ ፡ የኤንግልስ ፡ መጻሕፍት ፡
ላይ ፡ አብራርተዋል ።
ይሁን ፡ እንጂ ፤ ማርክስ ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡
ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አላበቃም ፤
ፍልስፍናን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ አዳበረው ። በጀርመን ፡
ክላሲካል ፡ ፍልስፍና ፤ በተለየም ፡ በሔግል ፡ ሲስቴም ፡
አበለፀገው ። ይኸውም ፡ ድርጊት ፡ በበኩሉ ፡ ወደ ፡ ፎየር
ባኽ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ አመራ ። ከፍተኛው ፡ አስተዋጽ
ኦ ፡ ዲያሌክቲክስ ፡ ነበር ፡ — ይኸውም ፡ ማለት ፡ ስለ ፡
ዕድገት ፡ የተሟላ ፤ የጠለቀ ፡ እና ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡
ትምህርት ፡ ዘለዓለም ፡ በዕድገት ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ ማቴሪ
ያል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ስለሚኖረው ፡ ተነፃፃሪ ፡ የዕውቀት ፡
ነጸብራቅ ፡ ትምህርት ፡ ያበረከተው ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋጽ
ኦ ፡ ማለት ፡ ነው ። የተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ በስተኋላ ፡ ጊዜ ፡
ያስገኛቸው ፡ እንደ ፡ ራዲየም ፤ ኤሌክትሮኖች ፡ እና ፡ የን
ጥረ-ነገሮች ፡ መለዋወጥ ፡ ከቡርዥዋ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ከአረ
ጀው ፡ እና ፡ ተልካሻ ፡ ከሆነው ፡ ሃሣባዊነት ፡ ውስጥ «ድ
ጋሚ» መልስ ፡ ለማድረግ ፡ ከሚሹት ፡ ውጭ ፤ የማርክስ
ን ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡
የሚያረጋግጡ ፡ ሁነዋል ።
የፍልስፍና ፡ ማቴሪያሊዝምን ፡ ማርክስ ፡ ሙሉ ፡ በ
ሙሉ ፡ በማስፋፋት ፡ እና ፡ በማዳበር ፡ የተፈጥሮ ፡ ምርምር ፡
የኅብረተ ፡ ሰብንም ፡ ምርምር ፡ በውስጡ ፡ እንዲይዝ ፡ አ
ደረገው ። የማርክስ ፡ ታሪካዊ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ በሳይን

ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ነበር ። በታሪ
ሳዊ ፡ ምርምር ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ነበር ። በታሪ
ሳዊ ፡ ምርምር ፡ ውስጥ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡
ክ ፡ እና ፡ በፖለቲካ ፡ ምርምር ፡ ውስጥ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡
አንሠራርቶ ፡ የነበረው ፡ ምስቅልቅል ፡ እና ፡ ውስብስብ ፡
አስተሳሰቦች ፡ በታላቅ ፡ እና ፡ በተጣጣመ ፡ ሳይንሳዊ ፡
ቴዎሪ ፡ እንዲተካ ፡ ተደረገ ። በምርት ፡ ኃይሎች ፡ ማደግ ፡
ምክንያት ፡ ከአንዱ ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ አኗኗር ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ እና ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ የአኗኗር ፡
ዕድገት ፡ እንደሚመሠረት ፡ ለምሳሌም ፡ ከፊውዳሊዝም ፡
ውስጥ ፡ ካፒታሊዝም ፡ እንዴት ፡ እንደሚያድግ ፡ አሳይ
ቷል ።

የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ከቁጥጥሩ ፡ ውጭ ፡ የሆነውን ፡ ተፈ
ጥሮን ፡ እንደሚያንጸባርቅ ፡ ሁሉ ፡ ማለትም ፤ ዳባሪው ፡
ቁስ ፡ አካልን ፤ ሰው ፡ ስለኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ያለው ፡ ዕውቀት
ም (ማለትም ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አመለካከቶቹ ፡ እና ፡ ሃሣቦ
ቹ — የፍልስፍና ፤ የሐይማኖት ፤ የፖለቲካ ፡ እና ፡ የመሳሰ
ሉትም) የኅብረተ ፡ ሰብን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሥርዓት ፡ ያንጸ
ባርቃል ። የፖለቲካ ፡ ተቋሞች ፡ በኤኮኖሚ ፡ መሠረት ፡
ላይ ፡ የተገነቡ ፡ ላዕላይ ፡ መዋቅራን ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡
ያህልም ፡ የዘመናውያን ፡ የአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፖለቲካ ፡ ቅርጾች ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡
ላይ ፡ የቡርዥዋው ፡ መደብ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጭቆና ፡
ለማጠናከር ፡ የቆሙ ፡ መሆናቸውን ፡ እንገነዘባለን ።

የማርክስ ፡ ፍልስፍና ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፤ በተለይም ፡ ደ
ግሞ ፡ ለወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ ኃይለኛ ፡ የዕውቀት ፡ መሣ
ርያን ፡ በመለገስ ፡ ብቃት ፡ ያለው ፡ የፍልስፍና ፡ ማቴሪ
ያሊዝም ፡ ነው ።

## II

የፖለቲካ ፡ ላዕላይ ፡ መዋቅር ፡ የተገነባው ፡ በኤኮኖ
ሚ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ከተገነዘበ ፡ በኋላ ፤ ማርክ



ስ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜውን ፡ ይኸንን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሥርዓት ፡
በመመራመር ፡ ላይ ፡ አዋለ ። «ካፒታል» የተሰኘው ፡ የ
ማርክስ ፡ ታላቁ ፡ ሥራ ፡ ዘመናዊውን ፡ የካፒታሊስት ፡
ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሥርዓት ፡ ለማጥናት ፡ የዋለ ፡
ነው ።

ከማርክስ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ክላሲካል ፡ የሆነ ፡ ፖለ
ቲካዊ ፡ ኤኮኖሚ ፡ የመነጨው ፡ ከካፒታሊስት ፡ ሀገሮች ፡
ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ዳብሮ ፡ በነበረው ፡ በእንግሊዝ ፡ ሀገር ፡ ው
ስጥ ፡ ነው ። አዳም ፡ ስሚት ፡ እና ፡ ዳቪድ ፡ ሪካርዶ ፡ የኤኮ
ኖሚውን ፡ ሥርዓት ፡ በመመራመር ፡ ስለ ፡ ጉልበት ፡ ዋጋ ፡
ቴዎሪ ፡ የምርምር ፡ መሠረት ፡ ጣሉ ። የነርሱን ፡ ምርምር ፡
ማርክስ ፡ ገፋበት ። ለዚህ ፡ ቴዎሪ ፡ ማስረጃ ፡ ከማቅረቡም ፡
በስተቀር ፤ በሚገባ ፡ አዳበረው ። የእየአንዳንዱ ፡ የሸቀጥ ፡
ዋጋ ፡ የሚወስነው ፤ ሸቀጡን ፡ ለማምረት ፡ በኅብረተሰብ ፡
ውስጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ጉልበት ፡ በሚፈጀው ፡ የጊ
ዜ ፡ ብዛት ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ አሳየ ።

የቡርዥዋ ፡ ኤኮኖሚስቶች ፡ በነገሮች ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡
ግንኙነቶችን ፡ ሲመለከቱ (የአንዱ ፡ ሸቀጥ ፡ በሌላኛው ፡
ሸቀጥ ፡ መለወጡን) ማርክስ ፡ ግን ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡
ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ገለጠ ። የሸቀጣ ፡ ሸቀጦች ፡ መለዋወ
ጥ ፡ በገበያ ፡ አማካይነት ፡ በግለኛ ፡ አምራቾች ፡ መካከል ፡
ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ ይገልጻል ። ግንኙነቱ ፡ የበለጠ ፡
መቀራረቡንና ፡ የግለኛ ፡ አምራቾች ፡ ጠቅላላ ፡ የኤኮኖሚ ፡
ሕይወት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይነት ፡ የሚለወጥ ፡ መሆ
ኑን ፡ ገንዘብ ፡ ያበክራል ። ካፒታል ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ግንኙ
ነት ፡ ተጨማሪ ፡ እድገት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሲያበክር ፡
የሰው ፡ የሙያ ፡ ኃይል ፡ ሸቀጥ ፡ ይሆናል ። ለመሬት ፤ ለ
ፋብሪካዎች ፡ እና ፡ ለማምረቻ ፡ መሣርያዎች ፡ ባለቤት ፡
ተቀጣሪው ፡ ሠራተኛ ፡ ጉልበቱን ፡ ይሸጣል ። ሠራተኛ
ው ፤ ገሚሱን ፡ የሥራውን ፡ ቀን ፡ እራሱን ፡ እና ፡ ቤተሰቡን ፡
ለማስተዳደር ፡ የሚያስችለውን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ (ደመወዝ)

ያገባድዳል ፤ በተቀረው ፡ ገሚስ ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ለካፒታሊስቱ ፡ ትርፍ-ዋጋው ፤ የትርፍ ፡ ማግኛ ፡ ምንጬ ፤ ለካፒታሊስቱ ፡ መደብ ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፤ በመሆን ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ክፍያ ፡ ይሠራል ።

የትርፍ-ዋጋ ፡ ትምህርት ፡ በማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ቴዎሪ ፡ ውስጥ ፡ የማዕዘን ፡ መሠረት ፡ ነው ።

በሠራተኞች ፡ ጉልበት ፡ የተመሠረተ ፡ ካፒታል ፡ ሠራተኛውን ፡ ይደቁስዋል ፤ የትናንሽ ፡ ንብረት ፡ ባለመሬቶችን ፡ ያጠፋቸዋልና ፡ ሥራ-አጥ ፡ የሕዝብ ፡ መንጋ ፡ ይፈጥራል ። በኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፤ በሰፊው ፡ የሚወጠን ፡ የምርት ፡ ተግባር ፡ እንደሚኖር ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፤ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ክስተት ፡ በእርሻ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ በመታየት ፡ በሰፊው ፡ የሚወጠን ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ይጨምራል ፤ በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ መሣሪያዎች ፡ መጠቀም ፡ ይቀጥላል ፤ በገንዘብ ፡ ካፒታል ፡ የተተበተበው ፡ የገበሬ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ኋላ-ቀር ፡ በሆነው ፡ የአስተራረስ ፡ ዘዴው ፡ በማዘቅዘቅ ፡ እና ፡ በመውደቅ ፡ ድራሹ ፡ ይጠፋል ። በጥቂቱ ፡ የሚወጠን ፡ የምርት ፡ ተግባር ፡ ማቆልቆል ፡ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ ቢኖረውም ፤ ማቆልቆሉ ፡ ራሱ ፡ የማያከራክር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

በጥቂቱ ፡ የተወጠኑ ፡ የምርት ፡ ሥራዎችን ፡ በመደምሰስ ፡ የጉልበት ፡ ውጤት ፡ እንዲጨምር ፡ በማድረግ ፡ የትላልቅ ፡ ካፒታሊስቶች ፡ ማኅበሮች ፡ የሞኖፖሊ ፡ አቋም ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያደርጋል ። ምርት ፡ ራሱ ፡ ከጊዜ-ጊዜ ፡ የኅብረተሰብ ፡ ጠባይ ፡ ይኖረዋል — ብዙ ፡ መቶ ፤ ብዙ ፡ ሺህ ፡ እና ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሠራተኞች ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ ይተሣሠራሉ — ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዚህ ፡ የተባበረ ፡ ጉልበት ፡ ውጤት ፡ እፍኝ ፡ በማይሞሉ ፡ ካፒታሊስቶች ፡ የተያዘ ፡ ነው ። የምርት ፡ ቀውስ ፤ ክሥረት ፤ ቀውጢነት ፡ ያልተለየው ፡ የገበያን ፡



ሁኔታ ፡ ክትትል ፡ እና ፡ የሰፊው ፡ ሕዝብ ፡ ለኑሮው ፡ ዋስትናን ፡ ማጣት ፡ ይስፋፋሉ ።

ሠራተኞች ፡ በካፒታል ፡ ጥገኝነት ፡ ሥር ፡ እንዲውሉ ፡ የሚያስገድዳቸውን ፡ ሁናቴ ፡ በማጠናከር ፡ የካፒታሊስት ፡ ሥርዓት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የተባበረ ፡ የሞያ ፡ ኃይል ፡ ይፈጥራል ።

የካፒታሊዝም ፡ ዕድገት ፤ ገና ፡ እምቡጥ ፡ ከሆነው ፡ የሸቀጥ ፡ ኤኮኖሚ ፤ ቀላል ፡ ከሆነ ፡ ልውውጥ ፡ በሰፊው ፡ ከሚወጠን ፡ የምርት ፡ ተግባር ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃው ፡ ላይ ፡ እንደምን ፡ እንደሚደርስ ፡ ማርክስ ፡ አሳይቷል ።

የአሮጌዎቹ ፡ እና ፡ የአዲሶቹ ፡ የመላው ፡ ካፒታሊስት ፡ ሀገሮች ፡ ልምምድ ፤ ቁጥራቸው ፡ እየጨመረ ፡ ለሚሄዱት ፡ ሠራተኞች ፡ የዚህ ፡ ማርክሳዊ ፡ ትምህርት ፡ እውነተኛነትን ፡ በግልጽ ፡ ያሳያቸዋል ።

ካፒታሊዝም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ድል ፡ አድርጓል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ይኸ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፤ ጉልበት ፡ በካፒታል ፡ ላይ ፡ ለሚያገኘው ፡ ድል ፡ መቅድሙ ፡ ነው ።

## III

ፊውዳሊዝም ፡ በተገለበጠበት ፡ ጊዜ ፡ እና «ነፃ» የካፒታሊስት ፡ ኅብረተሰብም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ነፃነት ፡ ለሠርቶ-አደር ፡ ሕዝቦች ፡ አዲስ ፡ ዓይነት ፡ የጭቆና ፡ እና ፡ የብዝበዛ ፡ ሥርዓት ፡ መሆኑ ፡ ወዲያውኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆነ ። ይኸንን ፡ ጭቆና ፡ በማንጸባረቅ ፡ እና ፡ በመቃወም ፡ የተለያዩ ፡ የሶሺያሊስት ፡ አስተሳሰቦች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ ጀመሩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ቀደም ፡ ሲል ፡ የነበረው ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ተምኔታዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ነበር ። የካፒታሊስት ፡ ኅብረተሰብን ፡ ነቀፈው ፤ ኮነነው ፡ እንደዚሁም ፡ አጥላላው ፤ የሚወድቅበትን ፡ መንገድ ፡ አለመ ። አዲስ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲመሠረት ፡ ምኞት ፡

ስለነበረው ፤ ብዝበዛ ፡ ከሥነ ፡ ምግባር (ሞራል) ውጭ ፡
መሆኑን ፡ ለህብታም ፡ ሊያስተምር ፡ ሞከረ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ ተምኔታዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ትክክለ
ኛውን ፡ መፍትሔ ፡ አላመለከተም ። በካፒታሊዝም ፡ ሥር ፡
የሚገኘውን ፡ የጉልበት ፡ ባርነት ፡ ዓይነተኛ ፡ ባህርይ ፡
ለማስረዳት ፡ አልቻለም ። የካፒታሊስት ፡ የዕድገት ፡ ሕ
ጎችን ፡ ለመግለጽ ፡ አልቻለም ። ወይንም ፡ ደግሞ ፤ ምን ፡
ዓይነት ፡ የኅብረተሰብ ፡ ኃይል ፡ የአዲስ ፡ ኅብረተሰብን ፡
መሥራች ፡ ለመሆን ፡ እንደሚችል ፡ ማሳየት ፡ አልቻለም ።

በመካከሉም ፤ መላውን ፡ አውሮፓ ፡ እና ፡ በተለይም ፡
ፈረንሳይን ፡ ያጥለቀለቁት ፡ የሬቮሉሽን ፡ ማዕበሎች ፡ የፊ
ውዳሊዝምን ፡ እና ፡ የገባርነትን ፡ መደምሰስ ፡ አስከተሉ ።
የመደቦች ፡ ትግል ፡ የመላው ፡ ዕድገት ፡ መሠረት ፡ እና ፡
አንቀሳቃሽ ፡ ኃይል ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ አሳዩ ።

በፊውዳሉ ፡ መደብ ፡ የተገኘው ፡ ማናቸውም ፡ የፖለ
ቲካ ፡ ነፃነት ፡ ያለ ፡ ፊውዳሉ ፡ የመጨረሻ ፡ መፍጨር
ጨር ፡ የተገኘ ፡ አልነበረም ። በዛም-አነሰ ፤ ነፃ ፡ እና ፡ ዴ
ሞክራሲያዊ ፡ መሠረት ፡ ውስጥ ፡ ለመሸጋገር ፡ በአን
ዱም ፡ የካፒታሊስት ፡ ሀገር ፡ ቢሆን ፤ የካፒታሊስት ፡
ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ የተለያዩ ፡ መደቦች ፡
መካከል ፡ የሕይወት ፡ እና ፡ የሞት ፡ ትግል ፡ ሳይደረግ ፡ የተ
ገኘ ፡ አልነበረም ።

የማርክስ ፡ ብልሕነት ፡ የሚታወቀው ፤ ከዚህ ፡ ሁኔታ ፡
የዓለም ፡ ታሪክ ፡ የሚያስተምረውን ፡ ትምህርት ፤ ይኸንን
ም ፡ ትምህርት ፡ በሚገባ ፡ ለማዋል ፡ ማርክስ ፡ የመጀመሪ
ያው ፡ የዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቀሳሚ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። እርሱ ፡
የቀሰመው ፡ ትምህርትም ፡ የመደቦች ፡ ትግል ፡ ትምህርት ፡
ነው ።

ሕዝቦች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በፖለቲካ ፡ ውስጥ ፡ በማታለያ ፡
እና ፡ በራስን-ማታለያ ፡ ሞኞ-ሞኝ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡
ሲገቡ ፡ ይገኛሉ ። ከማናቸውም ፡ የሥነ ፡ ምግባር ፤ የሐይማ



ኖት ፤ የፖለቲካ ፡ እና ፡ የሶሺያል ፡ አባባሎች ፡ መግለጫ
ዎች ፡ እና ፡ ተስፋዎች ፡ ውጭ ፡ የአንድን ፡ ወይም ፡ የሌላ
ኛውን ፡ መደብ ፡ ጥቅሞች ፡ ለማወቅ ፡ እስካልቻሉ ፡ ድረስ ፡
ሁልጊዜም ፡ ሞኞ-ሞኝ ፡ ይሆናሉ ። እየአንዳንዱ ፡ ያረጀ ፡
ተቋም ፡ የፈለገውን ፡ ያህል ፡ ጨካኝ ፡ እና ፡ የበሰበሰ ፡ ቢመ
ስልም ፤ ቆሞ ፡ ሊሄድ ፡ የሚቻለው ፡ በተወሰኑ ፡ መሪ ፡
መደቦች ፡ መሆኑን ፡ የለውጥ ፡ እና ፡ የመሻሻል ፡ ሃዋርያት ፡
እስካልተገነዘቡት ፡ ድረስ ፡ ምንጊዜም ፡ ተታልለው ፡ ይ
ኖራሉ ። የነዚያን ፡ መደቦች ፡ መፍጨርጨር ፡ ድራሹ ፡
የሚጠፋውም ፡ በአንድ ፡ ብቻ ፡ መንገድ ፡ ነው ። ይኸው
ም ፡ እኛን ፡ በከበበን ፡ በዚያው ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፤
አሮጌውን ፡ አፈራርሰው ፡ አዲሱን ፡ ለመመሥረት ፡ የሚ
ያስችል ፡ ኃይል ፡ ያላቸውን — በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡
ባላቸው ፡ ቦታ ፡ ምክንያትም ፡ ይኸንኑ ፡ ማድረግ ፡ የሚገ
ባቸውን — እነዚህን ፡ ኃይሎችም ፡ ለትግሉ ፡ ለማጕል
መስ ፡ እና ፡ ለማደራጀት ፡ የሚቻሉትን ፡ ፈልጐ ፡ ማወቁ ፡
ነው ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የነበሩ ፡ ተጨቋኝ ፡ መደቦች ፡ ሁሉ ፡
ይማቅቁበት ፡ ከነበረው ፡ የመንፈስ ፡ ባርነት ፡ የወዝ ፡ አደ
ሩ ፡ መደብ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ እንደሚወጣ ፡ ያሳየው ፡
የማርክስ ፡ የፍልስፍና ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ብቻ ፡ ነው ። በካ
ፒታሊዝም ፡ ጠቅላላ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡
መደብ ፡ ያለውን ፡ ትክክለኛ ፡ ቦታ ፡ ያሳየው ፡ የማርክስ ፡
የኤኮኖሚ ፡ ቴዎሪ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ከአሜሪካ ፡ እስከ ፡ ጃፓን ፤ ከስዊድን ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡
አፍሪካ ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ ድር
ጅቶች ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ በእጥፍ ፡ ድርብ ፡ እየጨመ
ሩ ፡ ናቸው ። የወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ የመደብ ፡ ትግሉን ፡
በመቀጠል ፡ እየጎለመሰ ፡ እና ፡ እየተማረ ፡ ነው ፤ ለቡር
ዥዋው ፡ ኅብረተሰብ ፡ ይሰጥ ፡ ከነበረው ፡ አግባብ-የለሽ ፡
አስተያየት ፡ ራሱን ፡ እያወጣ ፡ ነው ፤ የራሱን ፡ ወገኖች ፡

ይበልጥ ፡ በማቀራረብ ፡ እያሰለፈ ፡ እና ፡ የድሎቹን ፡ ውጤቶች ፡ እየለካ ፤ ኃይሉን ፡ እያጠናከረ ፡ እና ፡ በማይበገር ፡ ሁኔታም ፡ እየዳበረ ፡ ነው ።

«ፕሮስቬሼኒየ» ፤ ቁጥር ፡ 3 ፤ እ.ኤ.አ. መጋቢት ፡ ወር ፤ 1913 ዓ. ም. ቅጽ ፡ 23 ፤ ገጾች ፡ 40-48

ፊርማ ፤ ቭ. ኢ.

## ካርል ፡ ማርክስ ።

(አጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩና ፡ የማርክሲዝም ፡ ትንተና)

### መቅድም ።

ይህ ፡ አሁን ፡ በተለየ ፡ እትም ፡ የወጣው ፡ ስለካርል ፡ ማርክስ ፡ የተጻፈው ፡ አርቲክል (እንደማስታውሰው) እ. ኤ. አ. በ 1913 ዓ. ም. ግራናት ፡ ለተባለው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የጻፍኩት ፡ ነው ። በአርቲክሉ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ስለማርክስ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ የሚያስረዱ ፡ በአብዛኛው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ ታክለውበታል ። ይህ ፡ በአሁኑ ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ አልሠፈረም ። የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ አዘጋጅም ፡ በበኩሉ ፡ በሳንሱር ፡ ምክንያት ፡ የማርክስን ፡ የአብዮታዊ ፡ ትግል ፡ ታክቲክ ፡ የሚያስረዳውን ፡ የአርቲክሉን ፡ የመጨረሻ ፡ ክፍል ፡ አስቀርቶታል ። ይህን ፡ የአርቲክሉን ፡ የመጨረሻ ፡ ክፍል ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለመቻሌ ፡ አዝናለሁ ። ምክንያቱም ፡ የጽሑፉ ፡ ረቂቅ ፡ ከሌሎች ፡ ሠነዶች ፡ ጋር ፡ ክራኮቭ ፡ ወይንም ፡ ስዊዘርላንድ ፡ ውስጥ ፡ ስለቀረ ፡ ነው ። እንዳጋጣሚ ፡ የጠቀስኩት ፡ ማርክስ ፡ ለኤንግልስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1856 ዓ. ም. ሚያዝያ ፡ 16 ቀን ፡ ከጻፈው ፡ ደብዳቤ «የጀርመን ፡ ጠቅላላ ፡ ሁናቴ ፡ ሊወሰን ፡ የሚችለው ፡ የገበሬውን ፡ ጦርነት ፡ የመሰለ ፡ ንቅናቄ ፡ እንደገና ፡ በመፍጠር ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ አብዮት ፡ ለማጠናከር ፡ የሚችልበትን ፡ መንገድ ፡ በመመሥረት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ጉዳዩ ፡ እጅግ ፡ የተቃና ፡ መልክ ፡ ይኖረዋል» የሚለውን ፡ ክፍል ፡ ነው ። ሶሺያሊዝምን ፡ የከዱት

ና ፡ ከቡርዥዋዎች ፡ ጐን ፡ አሁን ፡ ተሠልፈው ፡ የሚገኙት ፡ የኛ ፡ ሜንሼቪኮች[2] ፡ እ. ኤ. አ. በ 1905 ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ያልገባቸው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሞስኮ ፤ እ. ኤ. አ. ግንቦት ፡ 14 ቀን ፤ 1918 ዓ. ም.

ሌኒን ።

ካርል ፡ ማርክስ ፡ ትሬየር ፡ በተባለው ፡ ከተማ (በሬይን ፡ ፕሩስያ) እ. ኤ. አ. ግንቦት ፡ 5 ቀን ፡ በ 1818 ዓ. ም. ተወለደ ። የካርል ፡ ማርክስ ፡ አባት ፡ በጥብቅና ፡ የሚኖር ፡ እ. ኤ. አ. በ 1824 ዓ. ም. የፕሮተስታንት ፡ ሐይማኖትን ፡ የተቀበለ ፡ አይሁድ ፡ ነበር ። በጠቅላላው ፡ ቤተሰቡ ፡ ባለፀጋና ፡ ጨዋ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ሲሆን ፡ አብዮተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ አልነበረም ። ካርል ፡ ማርክስ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርቱን ፡ በትሬየር ፡ ከተማ ፡ እንዳጠናቀቀ ፡ በመጀመሪያ ፡ በቦን ፡ ዩኒቬርሲቲ ፤ ከዚያም ፡ በበርሊን ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ተከታትሎ ፡ በታሪክና ፡ በፍልስፍና ፡ ከፍተኛ ፡ ዕውቀት ፡ አጠናቀቀ ። የዩኒቬርሲቲ ፡ ትምህርቱን ፡ እንደጨረሰ ፡ ለዶክተር ፡ ማዕረግ ፡ ስለኤፒኩሩስ ፡ ፍልስፍና ፡ የግል ፡ ጽሑፍን ፡ እ. ኤ. አ. በ 1841 ዓ. ም. አቀረበ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማርክስ ፡ የሔግልን ፡ ፍልስፍና ፡ የሚከተል ፡ ሐሳባዊ ፡ ነበር ። በርሊንም ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ «ግራ ፡ ክንፍ ፡ ከሆኑ ፡ ከሔግል ፡ ፍልስፍና» ተከታዮች (ከነብሩኖ ፡ ባወርና ፡ ሌሎች ፡ መሰሎቻቸው) ጋር ፡ ተጐዳኝቶ ፡ ነበር ። ጥረታቸውም ፡ ከሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ ፀረ ፡ አምልኰ ፡ አቋምና ፡ አብዮታዊ ፡ ትምህርት ፡ ለመመሥረት ፡ የታቀደ ፡ ነበር ።

ማርክስ ፡ የዩኒቬርሲቲውን ፡ ትምህርት ፡ ካጠናቀቀ ፡ በኋላ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ለመሆን ፡ በማቀድ ፡ ወደ ፡ ቦን ፡ ተዛወረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጊዜው ፡ የነበረው ፡ አድኃሪ ፡ መንግሥት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1832 ዓ. ም. ሉድቪግ ፡ ፎየርባኽን ፡

የመምሕርነት ፡ ወንበሩን ፡ ነፍጐት ፡ ስለነበረና ፡ እ. ኤ. አ. በ 1836 ዓ. ም. ወደ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ እንዳይመለስ ፡ አግዶት ፡ ስለነበር ፡ ከዚያም ፡ ወጣቱን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ብሩኖ ፡ ባወርን ፡ እ. ኤ. አ. በ 1841 ዓ. ም. በቦን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ እንዳያስተምር ፡ ከልክሎት ፡ ስለነበር ፡ ማርክስ ፡ ለመከታተል ፡ አቅዶት ፡ የነበረውን ፡ የአካዳሚ ፡ ሥራ ፡ እንዲተወው ፡ ተገደደ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግራ ፡ ክንፈኞች ፡ የሆኑ ፡ የሔግል ፡ ተከታዮች ፡ አስተሳሰብ ፡ ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ እየተጠናከረ ፡ መሔድ ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ። ሉድዊግ ፡ ፎየርባኽ ፡ በተለይ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1836 ዓ. ም. መንፈሳዊነትን ፡ በመንቀፍ ፡ ማቴሪያሊዝምን ፡ ማጋነን ፡ ጀመረ ። ባደረገውም ፡ ጥረት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1841 ዓ. ም. «የክርስትና ፡ ምንነት» በሚል ፡ አርዕስት ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈ ። እ. ኤ. አ. በ 1843 ዓ. ም. ደግሞ «የወደፊቱ ፡ ፍልስፍና ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መርሆዎች» በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈ ። «እነዚህ ፡ መጽሐፎች ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ አዕምሮ ፡ አርቆ ፡ ለማስተዋልና ፡ ለማዳበር ፡ የሚያስችል ፡ ከፍተኛ ፡ ኃይል ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን ፡ ያነበባቸው ፡ ሁሉ ፡ ሊገነዘብ ፡ ይችላል» ሲል ፡ ኤንግልስ ፡ ስለፎየርባኽ ፡ ሥራዎች ፡ ገልጿል ። «እኛ» (ማለት ፡ ግራ ፡ ክንፍ ፡ የሆኑ ፡ የሔግል ፡ ተከታዮች ፤ ማርክስ ፡ ጭምር) «ወዲያውኑ ፡ ሁላችንም ፡ የፎየርባኽ ፡ ደጋፊዎች ፡ ሆነናል» በማለት፡ ኤንግልስ ፡ አድናቆቱን ፡ ገልጿል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሬይን ፡ ቀበሌ ፡ የነበሩ ፡ ከግራ ፡ ክንፈኛ ፡ የሔግል ፡ ተከታዮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የነበራቸው ፡ የቡርዥዋ ፡ ተስፈንጣሪዎች ፡ «የሬይን ፡ ጋዜጣ» በሚል ፡ መጠሪያ ፡ አንድ ፡ ተቃዋሚ ፡ ጋዜጣ ፡ ኰሎኝ ፡ ውስጥ ፡ አቋቋሙ ። (የመጀመሪያው ፡ እትም ፡ የወጣው ፡ እ. ኤ. አ. ጥር ፡ 1 ቀን ፡ 1842 ዓ. ም. ነበር ።) ማርክስና ፡ ብሩኖ ፡ ባወር ፡ ለዚህ ፡ ጋዜጣ ፡ ጽሑፎች ፡ እንዲያበረክቱ ፡ ጥሪ ፡ ቀረበላቸው ፤ እ. ኤ. አ. በ 1842 ዓ. ም. ማርክስ ፡ የጋዜጣው ፡



ዋና ፡ አዘጋጅ ፡ ሆኖ ፡ ከቦን ፡ ወደ ፡ ኰሎኝ ፡ ተዛወረ ። የዚህ ፡ ጋዜጣ ፡ አብዮታዊ ፡ የዴሞክራቲክ ፡ ዓላማ ፡ በካርል ፡ ማርክስ ፡ አዘጋጅነት ፡ እየጐላና ፡ እየተስፋፋ ፡ ሔደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ቁጥጥር ፡ እንዲደረግበት ፤ በኋላም ፡ እ. ኤ. አ. ጥር ፡ 1 ቀን ፡ በ 1843 ዓ. ም. ላይ ፡ ጋዜጣውን ፡ ለመዝጋት ፡ ወሰነ ። ይህ ፡ ጭቆና ፡ ከመጣሉ ፡ በፊት ፡ ማርክስ ፡ በፈቃዱ ፡ ከሥራው ፡ የተሰናበተ ፡ ሲሆን ፡ የማርክስ ፡ ሥራውን ፡ መልቀቅ ፡ ጋዜጣውን ፡ በቀጥታ ፡ ከመጨቆን ፡ አላዳነውም ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ እ. ኤ. አ. በመጋቢት ፡ ወር ፡ በ 1843 ዓ. ም. የጋዜጣው ፡ እየታተመ ፡ መውጣት ፡ አቆመ ። ካርል ፡ ማርክስ ፡ ለዚህ ፡ ጋዜጣ ፡ ካበረከታቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ከሚሰጣቸው ፡ ጽሑፎች ፡ («ሥነ ፡ ጽሑፍን» ተመልከት)[3] አንደኛው ፡ በሞስሊ ፡ ሸለቆ ፡ ስለነበሩት ፡ የወይን ፡ እርሻ ፡ ገበሬዎች ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ የጻፈው ፡ አርቲክል ፡ እንደነበር ፡ ኤንግልስ ፡ በጽሑፉ ፡ ገልጾታል ። ማርክስ ፡ የጋዜጠኛነት ፡ ሥራ ፡ ባኪያሔደበት ፡ ጊዜ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ዕውቀቱ ፡ የሚያረካ ፡ ሆኖ ፡ ስለአላገኘው ፡ ይህን ፡ የዕውቀት ፡ መስመር ፡ በከፍተኛ ፡ ጉጉት ፡ መከታተል ፡ ጀመረ ።

እ. ኤ. አ. በ 1843 ዓ. ም. ካርል ፡ ማርክስ ፡ ከልጅነት ፡ ጊዜው ፡ ጀምሮ ፡ እጮኛው ፡ የነበረችውን ፡ ጄኒ ፡ ፎን ፡ ቬስትፋለን ፡ ክሬይጽናህ ፡ ውስጥ ፡ በኑሮ ፡ ጓደኛነት ፡ አገባት ። የካርል ፡ ማርክስ ፡ ባለቤት ፡ የተወለደችው ፡ በጊዜው ፡ ከነበሩት ፡ ከፕሩስያ ፡ መሣፍንት ፡ አድኃሪ ፡ ቤተሰብ ፡ ነበር ። ታላቅ ፡ ወንድሟም ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1850 ዓ. ም. እስከ 1858 ዓ. ም. ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በነበረው ፡ የብዝበዛ ፡ አገዛዝ ፡ የፕሩስያ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ነበር ። እ. ኤ. አ. በ 1843 ዓ. ም. በመፀው ፡ ወር ፡ ላይ ፡ ማርክስ ፡ አንድ ፡ ተራማጅ ፡ መጽሔት ፡ እያተመ ፡ ለማውጣት ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ሔደ ። ከሱም ፡ ጋር ፡ አርኖልድ ፡ ሩጌ ፡ አብሮት ፡ ለመሥራ

ት ፡ ሒዶ ፡ ነበር ። (ይህ ፡ ሰው ፡ እ. ኤ. አ. በ 1802 ዓ. ም. እስከ 1880 ዓ. ም. ድረስ ፡ ግራ ፡ ክንፍ ፡ የሔግል ፡ ደጋፊ ፡ ሆኖ ፡ የቆየ ፡ ሲሆን ፡ እ. ኤ. አ. 1825-30 ዓ. ም. ታስሮ ፡ ነበር ፤ እ. ኤ. አ. ከ 1848 ዓ. ም. ጀምሮ ፡ በፖለቲካ ፡ ስደተኝነት ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እ. ኤ. አ. ከ 1866 ዓ. ም. እስከ 1870 ዓ. ም. ደግሞ ፡ የቢስማርክ ፡ ሐሳብ ፡ ተከታይ ፡ ነበር ። ) መጽሔቱ «የጀርመንና ፡ የፈረንሳይ ፡ ዓመታዊ ፡ መጽሔት» በሚል ፡ መጠሪያ ፡ ታትሞ ፡ የወጣው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። መጽሔቱን ፡ ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ በሚስጢር ፡ ለማሠራጨት ፡ ባለመቻሉና ፡ በማርክስና ፡ በሩጌ ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ በመፈጠሩ ፡ ሥራው ፡ ወዲያውኑ ፡ ቆሟል ። ካርል ፡ ማርክስ ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ላይ «ርሕራሔ ፡ የሌለው ፡ ሒስ» በሚል ፡ አርዕስትና «ሒስ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ» በሚል ፡ አርዕስት ፡ ያሳተማቸው ፡ ጽሑፎች ፡ አብዮት ፡ ለመጀመር ፡ የተነሳ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዱ ፡ ነበሩ ። ማርክስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታው ፡ ሁሉ ፡ ለሠፊው ፡ ጭቁን ፡ ሕዝብና ፡ ለወዝ ፡ አደሩ ፡ የቀረበ ፡ ነበር ።

እ. ኤ. አ. በ 1844 ዓ. ም. በመስከረም ፡ ወር ፡ ላይ ፡ ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ መጣ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮም ፡ የማርክስ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛ ፡ ሆኖ ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኛ ፡ በአንድነት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፓሪስ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አብዮተኞች ፡ ቡድን ፡ አቋም ፡ በማስተካከልና ፡ በማረም ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋጽኦ ፡ አድርገዋል ። (በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ተሰጥቶት ፡ የነበረው ፡ የፕሩዶን ፡ ትምህርት ፡ ሲሆን ፡ ማርክስ «የፍልስፍና ፡ ድህነት» በሚል ፡ አርዕስት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1847 ዓ. ም. በጻፈው ፡ ሒስ ፡ የፕሩዶን ፡ ትምህርት ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ አድርጎታል) ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ በአንድነት ፡ በመሥራት ፡ የንዑስ ፡ ቡርዥዋ ፡ ሶሺያሊዝምን ፡ በመቃወም ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ አብዮታዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ሐደት ፡ ሥርዓትና ፡ ስልት ፡ ወይንም ፡ የኮሙኒዝምን ፡ ፍልስፍና (ማርክሲዝምን) ተለሙ ። ለዚህም ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1844 ዓ. ም. እስከ 1848 ዓ. ም. ድረስ ፡ የተጻፉትን ፡ በማርክስ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ ማየት ፡ ይቻላል ። የፕሩስያ ፡ መንግሥት ፡ በማከታተል ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1845 ዓ. ም. ማርክስ ፡ አደገኛ ፡ የአብዮት ፡ ቆስቋሽ ፡ በመባል ፡ ከፓሪስ ፡ ተባረረ ። በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ብሩሰልስ ፡ ሔደ ። እ. ኤ. አ. በ 1847 ዓ. ም. በፀደይ ፡ ወር ፡ ላይ ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ «የኮሙኒስቶች ፡ ኅብረት» ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ የአንድ ፡ ሕቡዕ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ሆኑ ። እ. ኤ. አ. ኅዳር ፡ ወር ፡ በ 1847 ዓ. ም. ለንደን ፡ ውስጥ ፡ በተሰበሰበው ፡ በኅበረቱ ፡ ሁለተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባዔ ፡ ላይ ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ከፍተኛ ፡ ሚና ፡ የተጫወቱ ፡ ሲሆን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ወደር ፡ የሌለውን ፡ ዝናና ፡ አድናቆት ፡ ያተረፈውን «ኮሙኒስት ፡ ፓርቲ ፡ ማኒፌስቶ» የተባለውን ፡ መጽሔት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. አትመው ፡ ያወጡት ፡ በዚሁ ፡ ጉባዔ ፡ በቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ይህ ፡ መጽሔት ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ በሆነ ፡ በተብራራና ፡ በረቀቀ ፡ መንገድ ፡ አዲስና ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሆነውን ፡ የኅብረተሰብን ፡ ኑሮ ፡ ቁልጭ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳየውን ፡ የማይዛባውን ፡ ማተሪያሊዝምንና ፡ የባሕርያትን ፡ ጠቅላላና ፡ የተጣራ ፡ ዕድገት ፡ የሚያስተምረውን ፡ ዲያሌክቲክስን ፤ የመደቦችን ፡ ትግልና ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ ማለት ፡ የአዲሱን ፡ የኮሙኒስት ፡ ኅብረተሰብ ፡ መሥራች ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ አብዮታዊ ፡ ሚና ፡ ታሪክ ፡ በከፍተኛ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።

እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. በየካቲት ፡ ወር ፡ ላይ ፡ አብዮቱ[4] ፡ በፈነዳ ፡ ጊዜ ፡ ማርክስ ፡ ከቤልጅግ ፡ እንዲወጣ ፡ ተደረገ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ተመልሶ ፡ ከመጋቢት ፡ ወር ፡ አብዮት[5] ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ ከተማ ፤ ማለት ፡ በማርክስ ፡ አዘጋጅነት «አዲሱ ፡ የሬይን ፡ ጋዜጣ» በሚል ፡

መጠሪያ ፡ እ. ኤ. አ. ከሰኔ ፡ 1 ቀን ፡ 1848 ዓ. ም. እስከ ፡ ግንቦት ፡ 19 ቀን ፡ 1849 ዓ. ም. ድረስ ፡ ጋዜጣ ፡ እየታተመ ፡ ይወጣባት ፡ ወደነበረችው ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ኰሎኝ ፡ ሔደ ። አዲሱ ፡ ቴዎሪ ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1848-49 ዓ. ም. ድረስ ፡ በተከያሔዱት ፡ አብዮታዊ ፡ ሁናቴዎች ፡ ትክክለኛነቱ ፡ የታየ ፡ ሲሆን ፡ ከዚያም ፡ በማከታተል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ትግልና ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ ንቅናቄዎች ፡ ተረጋግጧል ። ጊዜያዊ ፡ ድል ፡ ያገኙት ፡ ፀረ ፡ አብዮተኞች ፡ በመጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርበው ፡ ከአስወነጀሉት ፡ በኋላ (እ. ኤ. አ. የካቲት ፡ 9 ቀን ፡ በዋስ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ተደርጐ) በኋላም (እ. ኤ. አ. ግንቦት ፡ 16 ቀን ፡ 1849 ዓ. ም.) ከጀርመን ፡ ተባረረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ማርክስ ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ የሔደ ፡ ሲሆን ፡ እዚያም ፡ እ. ኤ. አ. ሰኔ ፡ 13 ቀን ፡ 1849 ዓ. ም.[6] ሠላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ በመደረጉ ፡ አሁንም ፡ ከሀገር ፡ እንዲወጣ ፡ ተደረገ ። ከፓሪስ ፡ በኋላ ፡ ማርክስ ፡ እስከዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ኑሮውን ፡ ወደ ፡ አሳለፈባት ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ሔደ ።

(እ. ኤ. አ. በ 1913 ዓ. ም. ታትመው ፡ የወጡት) ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ የተጻጻፉቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ እንደሚያስረዱት ፡ ማርክስ ፡ በፖለቲካ ፡ ስደተኛነት ፡ ያሳለፈው ፡ ኑሮ ፡ የችግር ፡ ኑሮ ፡ ነበር ። ማርክስና ፡ ቤተሰቡ ፡ በድሕነት ፡ ተቆራምተዋል ፤ ኤንግልስ ፡ ያለማቋረጥና ፡ ያለ ፡ መሰልቸት ፡ ማርክስን ፡ በገንዘብ ፡ ባይረዳው ፡ ኖሮ ፡ ካፒታል ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፉን ፡ ለመጨረስ ፡ ካለመቻሉም ፡ በላይ ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሳ ፡ ከሰውነት ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ ወድቆ ፡ በቀረ ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ የንዑስ ፡ ከበርቴ ፡ ሶሺያሊዝምና ፡ በጠቅላላው ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ ያልተመሠረተው ፡ ሶሺያሊዝም ፡ መመሪያዎች ፡ ማርክስ ፡ በቆራጥነት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ትግሉን ፡ እንዲቀጥልና ፡ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የሚሠነዘሩትን ፡ ጭካኔ ፡ የተመላ



ባቸውን ፡ ጥቃቶች ፡ ለመቋቋምና ፡ አፀፋውን ፡ ለመመለስ ፡ በወኔ ፡ እንዲሠራ ፡ አድርገውታል («Herr Vogt») ከፖለቲካ ፡ ስደተኞች ፡ ክበቦች ፡ እራሱን ፡ አግልሎ ፡ የተቀመጠው ፡ ማርክስ ፡ የማተሪያሊዝም ፡ ቴዎሪውን ፡ በይበልጥ ፡ ያዳበረው ፡ በፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጥናት ፡ ላይ ፡ ጊዜውን ፡ በማዋል ፡ በፈጸማቸው ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራዎች ፡ ነው ። ቢብሊዮግራፊውን ፡ ይመልከቱ ። ማርክስ ፡ ይህን ፡ ሳይንሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ዕድገትና ፡ ጥራት ፡ የሰጠው ፡ (እ. ኤ. አ. በ 1859 ዓ. ም. ) «ለፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሒስ» በበኩሉ ፡ ባቀረበው ፡ አስተዋፅኦና (እ. ኤ. አ. በ 1867 ዓ. ም.) በታተመው «ካፒታል» በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ቅጽ ፡ ነው ። (ከበታች ፡ ያለውን ፡ የማርክሲስት ፡ መመሪያ ፡ ይመልከቱ ።)

እ. ኤ. አ. በ 1850 ዎቹ ፡ ዓ. ም. እና ፡ በ 1860 ዎቹ ፡ ዓ. ም. ገደማ ፡ እንደገና ፡ ያንሰራሩት ፡ የዴሞክራቲክ ፡ ንቅናቄዎች ፡ ማርክስን ፡ ወደ ፡ ተግባራዊ ፡ ድርጊት ፡ እንዲያተኩር ፡ አድርጐታል ። ስመጥር ፡ የሆነው ፡ የመጀመሪያው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ ማለት «ዓለም ፡ አቀፉ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር» እ. ኤ. አ. በ 1864 ዓ. ም. መስከረም ፡ 28 ቀን ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ ተመሠረተ ። ለዚህ ፡ ድርጅት ፡ ዋልታው ፡ ካርል ፡ ማርክስ ፡ ሲሆን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጉባዔ ፡ በንግግር ፡ ከመክፈቱም ፡ በላይ ፡ አያሌ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲተላለፉ ፡ አስደርጓል ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮችን ፡ የሠራተኞች ፡ እንቅስቃሴ ፡ በማስተባበር ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ ሳይሆን ፡ በሌሎች ፡ የተመሠረቱትንና ፡ ቅድመ ፡ ማርክሲስት ፡ የነበሩትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ይዘት ፡ ያላቸውን ፡ የሶሺያሊዝም ፡ ተከታዮች ፡ (እነማዚኒን ፤ ፕሩዶንን ፤ ባኩኒንን ፤ በብሪታንያ ፡ የነበረውን ፡ ሊበራል ፡ የሞያተኞች ፡ ንቅናቄ ፤ በጀርመን ፡ የነበሩትን ፡ የላሳሊያን ፡ የቀኝ ፡ ክንፍ ፡ ወላዋዮችና ፡ ሌሎችን) በአንድ ፡ መስመር ፡ ለመምራት ፡ ጥረት ፡ በማድረግና ፡ የእነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ቡድኖች ፡ ልዩ ፡

ልዩ ፡ አስተሳሰቦች ፡ ጉድለት ፡ በተርታው ፡ በማጋለጥ ፡ ማርክስ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ትግል ፡ አንድ ፡ ወጥ ፡ የሆነና ፡ ሁሉም ፡ የሚከተሉት ፡ የትግል ፡ መንገድ ፡ ቀየሰላቸው ። ማርክስ (እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም.) («በፈረንሳይ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት») በሚል ፡ አርዕስት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም. ቁልጭ ፡ ያለና ፡ አርኪ ፡ የሆነ ፡ ትንተና ፡ የሰጠበት ፡ የፓሪስ ፡ ኮሙን (እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም.)[7] ከከሸፈ ፡ በኋላና ፡ የባኩኒን ፡ ተከታዮች ፡ የተገንጣይነት ፡ መንፈስ ፡ ካደረባቸው ፡ ወዲህ ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ የተባለው ፡ ድርጅት ፡ አውሮፓ ፡ ውስጥ ፡ ሊሠራ ፡ አልቻለም ። እ. ኤ. አ. በ 1872 ዓ. ም. የኢንተርናስዮናል ፡ ጉባዔ ፡ ሔግ ፡ ላይ ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ማርክስ ፡ የድርጅቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ኒዮርክ ፡ እንዲዛወር ፡ አድርጓል ። የመጀመሪያው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ እንደተቋቋመ ፡ ከፍተኛ ፡ ታሪካዊ ፡ ሚና ፡ በመጫወት ፡ ለዓለም ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ትግል ፡ ከፍተኛ ፡ ኃይል ፡ አበርክቶ ፡ ሥፍራ ፡ በመልቀቅ ፡ ትግሉ ፡ በየሀገሩ ፡ በከፍተኛ ፡ ወኔና ፡ በተፋፋመ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲቀጥልና ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ ሰፊ ፡ የሶሺያሊስት ፡ ፓርቲዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ እንዲቋቋሙ ፡ በር ፡ ከፍቷል ።

ማርክስ ፡ በኢንተርናስዮናል ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ በመሥራቱና ፡ አድካሚ ፡ የቴዎሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ባለማረፍ ፡ በመከታተሉ ፡ ጤንነቱ ፡ ሊዳከም ፡ በቅቷል ። ይሁንና ፡ ማርክስ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሳይንስ ፡ ጥራት ፡ ለመስጠትና «ካፒታል» የተባለውን ፡ መጽሐፉን ፡ ለመጨረስ ፡ የሚያስችሉትን ፡ አዳዲስ ፡ መረጃዎች ፡ በመሰብሰብና ፡ እንደመስኰብኛ[8] ፡ ያሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ በማጥናት ፡ ሲጥር ፤ ጤንነቱ ፡ እየተዳከመ ፡ በመሔዱ «ካፒታልን» ለመጨረስ ፡ አላስቻለውም ።

የማርክስ ፡ ባለቤት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1881 ዓ. ም. ታሕሳስ ፡ 2 ቀን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለየች ። ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ማለት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1883 ዓ. ም. መጋቢት ፡ 14 ቀን ፡ ማርክስ ፡ በሥራ[9] ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አርፎ ፡ ተገኘ ። የዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሰውና ፡ የባለቤቱ ፡ መቃብር ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ በሐይጌት ፡ መካነ ፡ መቃብር ፡ ይገኛል ። ከማርክስ ፡ ልጆች ፡ ግማሾቹ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ በድሕነት ፡ ይኖር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በልጅነታቸው ፡ የተቀጩ ፡ ሲሆን ፤ ሦስቱ ፡ ሴት ፡ ልጆቹ ፡ ኤልያኖር ፡ አቬሊንግ ፤ ላኡራ ፡ ላፋርግና ፡ ዤኒ ፡ ሎንጌ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳይ ፡ ሶሺያሊስቶች ፡ ጋር ፡ ተጋብተው ፡ የኖሩ ፡ ሲሆን ፡ የዤኒ ፡ ሎንጌ ፡ ልጅ ፡ የፈረንሳይ ፡ ሶሺያሊረስት ፡ ፓርቲ ፡ አባል ፡ ነው ።

## የማርክስ ፡ ትምህርት (ዶክትሪን) ።

ማርክሲዝም ፡ ማለት[10] ፡ የካርል ፡ ማርክስ ፡ አስተያየትና ፡ እሱ ፡ ያበረከተው ፡ ትምህርት ፡ ነው ። ማርክስ ፡ በ 19 ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በገሠገሡት ፡ ሦስት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ይታዩ ፡ የነበሩትን ፡ ሦስት ፡ የርዕዮተ ፡ ዓለም ፡ መሠረቶች ፡ ማለት ፡ ክላሲካል ፡ የጀርመን ፡ ፍልስፍናን ፤ ክላሲካል ፡ የእንግሊዝ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚንና ፤ ከፈረንሳይ ፡ ጠቅላላ ፡ አብዮታዊ ፡ መመሪያዎች ፡ ጋር ፡ የተጣመረውን ፡ የፈረንሳይን ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ተመራምሮና ፡ አጥንቶ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥራት ፡ በመስጠት ፡ ዕልባት ፡ ያበጀላቸው ፡ ታላቅ ፡ ምሁር ፡ ነው ። በመላው ፡ ዓለም ፡ ሥልጣኔ ፡ በፈነጠቀባቸው ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ትግል ፡ ቴዎሪና ፡ ፕሮግራም ፡ የሆነው ፡ በጠቅላላው ፡ ዘመናዊ ፡ ማቴሪያሊዝምንና ፡ ዘሙናዊ ፡ ሳይንቲፊክ ፡ ሶሺያሊዝምን ፡ የመሠረተው ፡ የማርክስ ፡ አስተያየትና ፡ ትምህርት ፡ ትክክለኛና ፡ ያልተዛባ ፡ ለመሆኑ ፡ በተቃዋሚዎቹ ፡ እንኳ ፡ የተመሠከረለት ፡ ነው ። በመሆኑም ፡ ለማርክሲዝም ፡ ትምህር

ት ፡ መሠረታዊ ፡ ይዘት ፡ ማለት ፡ ስለማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርት ፡ ከመግለጣችን ፡ በፊት ፡ ማርክስ ፡ በጠቅላላው ፡ ስለዓለም ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ በአጭሩ ፡ ለመግለጽ ፡ እንገደዳለን ።

## ፊሎሶፊካል ፡ ማቴሪያሊዝም ።

ካርል ፡ ማርክስ ፡ አስተያየቱ ፡ ጥንካሬና ፡ መሠረት ፡ እያበጀ ፡ በሔደበት ፡ ማለት ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1844 ዓ. ም. እስከ 1845 ዓ. ም. ማቴሪያሊዝምን ፡ በማዳበር ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ ሲሆን ፡ የሉድዊግ ፡ ፎየርባኽ ፡ ተከታይ ፡ ሁኖ ፤ የሉድዊግ ፡ ፎየርባኽን ፡ የማቴሪያሊዝም ፡ አስተያየት ፡ በየረድፉ ፡ ብቃትና ፡ ጥራት ፡ እንዳልነበረው ፡ ተገንዝቧል ። በማርክስ ፡ አስተሳሰብ ፡ ፎየርባኽ ፡ የፈጸመው ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ታሪካዊና ፡ መሠረታዊ ፡ ሥራ ፡ ከሔግል ፡ ሐሳባዊነት ፡ ትምህርት ፡ ተላቆ ፡ ማቴሪያሊዝምን ፡ መመሪያው ፡ ማድረጉና ፡ የማጠናከርም ፡ ጥረት ፡ ማድረጉ ፡ ነው ። ገና «በ XVIII ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በተለይም ፡ የፈረንሳይ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ይታገል ፡ የነበረው ፡ የፖለቲካ ፡ ድርጅቶችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሐይማኖትን ፤ መንፈሳዊነትንና … ተጨባጭነት ፡ የሌላቸውን ፡ ፍልስፍናዎች ፡ ሜታፊዚክስን ፡ ሲሆን («የፍልስፍና ፡ ድለላ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ስካር» «ከጠራ ፡ ፍልስፍና» በመነጠል ፡ ነው) (ይህ ፡ የተገለጸው «የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ውርስ» በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ «ቅዱስ ፡ ቤተሰብ» በተባለው ፡ አርዕስት ፡ ነው ።) ማርክስ ፡ ሲጽፍ «ለሔግል ፡ አስተሳሰብ ፡ በሚል ፡ መጠሪያ ፡ የተያዘው ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚገኝ ፡ የአስተሳሰብ ፡ ምርምር ፡ የዓለምን ፡ መሥራች (ፈጣሪን) የሚያሳይ ፡ ነው… በበኩሌ ፡ ያለኝ ፡ ዕምነት ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ ሲሆን ፡ ሐሳብ ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ልቡና ፡ የሚታይና ፡ የሚታሰብ ፡ ማቴሪያላዊ ፡ ዓለም ፡ ነው («ካፒታል» ቅጽ ፡ I



የሁለተኛው ፡ እትም ፡ መደምደሚያ) ። ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ በዚህ ፡ በማርክስ ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ፍልስፍና ፡ በመስማማትና ፡ ሐሳቡንም ፡ በማስፋፋት «አንቲ-ዱሪንግ» በተባለው ፡ መጽሐፉ (ተመልከት) — ማርክስ ፡ ይህን ፡ ድርሰት ፡ ከመታተሙ ፡ በፊት ፡ አንብቦታል — «የዓለም ፡ ኅብረ ፡ አቋም ፡ የተመሠረተው ፡ ዓለም ፡ በመኖሩ ፡ አይደለም ፤ የዓለም ፡ እውነተኛ ፡ ኅብረ ፡ አቋም ፡ የተመሠረተው ፡ በቁስ ፡ አካላዊነቱ (ማቴሪያሊቲ) ሲሆን ፡ ይህም ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ የፍልስፍናና ፡ የተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ ከባድ ፡ ጥናት ፡ ተረጋግጧል … የማቴር ፡ የኑሮ ፡ መልኩ ፡ ቅስቃሴ ፡ ነው ። በየትኛውም ፡ ሥፍራ ፤ በየትኛውም ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ ማቴር ፡ ያለ ፡ ቅስቃሴ ፡ እንዲሁም ፡ ቅስቃሴ ፡ ያለማቴር ፡ አይኖሩም … እንዲሁም ፡ አስተሳሰብና ፡ የሕሊና ፡ ንቃት ፡ ከየት ፡ እንደመጡና ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ከተጠየቀ … የአዕምሮ ፡ ውጤት ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፤ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ከአካባቢው ፡ ተፈጥሮ ፡ ጋር ፡ ያደገና ፡ የደረጀ ፡ የተፈጥሮ ፡ ውጤት ፡ ሲሆን ፤ በዚሁ ፡ አንፃር ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ አዕምሮ ፡ የሚመነጬት ፡ ውጤቶች ፡ የተፈጥሮ ፡ ውጤቶች ፡ ለመሆናቸው ፡ እራሱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይህም ፡ ከቀሩት ፡ የተፈጥሮ ፡ ተወሳሳቢ ፡ ሁናቴዎች ፡ ጋር ፡ የሚቃረን ፡ ሳይሆን ፡ አብሮ ፡ የሚሔድ ፡ ነው» «ሔግል ፡ ሐሳባዊ ፡ የነበረ ፡ ማለት ፡ በአዕምሮው ፡ ውስጥ ፡ የሚወጡኑት ፡ ሐሳቦች ፡ በእሱ ፡ አስተሳሰብ ፡ የማይጨበጡና ፡ የማይዳሰሱ ፡ የእውነተኛ ፡ ሁናቴዎችና ፡ ሒደቶች ፡ ቅርፅ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ዓለም ፡ ከመፈጠሯ ፡ በፊት ፡ የነበረና ፡ ያለ ፡ የሐሳብ ፡ ውጤቶች ፡ ወይንም ፡ ቅርጾች ፡ ናቸው» (ኤንግልስ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአዕምሮ ፡ የሚጠነሰሱትን ፡ ሐሳቦች ፡ Abbilder ፡ ወይንም ፡ የሌላ ፡ ሁናቴዎች «ብልጭታ» ይላቸዋል ።) ኤንግልስ ፡ እሱና ፡ ማርክስ ፡ በፎየርባኽ ፡ ፍልስፍና ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ በማብራራት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1844-1845 ዓ. ም. ሁለ

ቱ ፡ ሆነው ፡ ስለሔግል ፡ ስለፎየርባኽና ፡ ስለታሪክ ፡ የማቴሪያሊስት ፡ አስተሳሰብ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ የነደፉትን ፡ ጽሑፍ ፡ ደጋግሞ ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ ለሕትመት ፡ በላከው ፡ ሉድዊግ ፡ ፎየርባኽ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ሲጽፍ «የማንኛውም ፡ ፍልስፍና ፡ በተለይም ፡ በቅርቡ ፡ የፈለቀው ፡ ፍልስፍና ፡ ታላቁ ፡ መሠረታዊ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ በማሰብና ፡ በመሆን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት … የትኛው ፡ ነው ፡ ቀዳሚ ፡ መንፈስ ፡ ወይስ ፡ ተፈጥሮ … ፈላስፎችን ፡ በሁለት ፡ ከፍተኛ ፡ ሠፈሮች ፡ የለዩዋቸው ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የሰጧቸው ፡ መልሶች ፡ ናቸው ። ከተፈጥሮ ፡ መንፈስ ፡ ይቀድማል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑትና ፡ ዓለምም ፡ የተፈጠረችው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ … የሚሉት ፡ በሐሳባዊ ፡ ሠፈር ፡ ተወስነዋል ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ማለት ፡ ተፈጥሮ ፡ ከመንፈስ ፡ ይቀድማል ፡ የሚሉት ፡ በማቴሪያሊዝም ፡ ሠፈር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መስመሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።» (የፊሎሶፊካል) ሐሳባዊነትንና ፡ የማቴሪያሊዝምን ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳቦች ፡ ከዚህ ፡ በተለየ ፡ መገመት ፡ ወደ ፡ ውዥንብር ፡ ያመራል ። ማርክስ ፡ የተቃወመው ፡ በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ከሐይማኖት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ ሐሳባዊነትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በተለይም ፡ በጊዜያችን ፡ ተሠራጭተው ፡ የሚገኙትን ፡ የህዩምና ፡ የካንትን ፡ አስተሳሰብ ፤ አግኖስቲሲዝምን ፤ ክሪትሲዝምንና ፤ ፖሲቲቪዝምን ፡ በተለያየ ፡ መልካቸው ፡ ተቃውሟቸዋል ። ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ፍልስፍና ፡ ማርክስ ፡ አድሐሪ ፡ የሆነ ፡ ከሐሳባዊነት ፡ ጋር ፡ የተገመዳኘ ፡ ቢበዛም ፡ ማቴሪያሊዝምን ፡ በስውር ፡ ተቀብሎ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ግን ፡ የሚቃረነው ፡ ነው» ይለዋል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከላይ ፡ የተገለፁትን ፡ የኤንግልስንና ፡ የማርክስን ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ ቶማስ ፡ ኼክስሊን «እስከተመለከትንና ፡ እስከአሰብን ፡ ድረስ ፡ ከማቴሪያሊዝም ፡ ልናመልጥ ፡ አንችልም »



በማለት ፡ ስለተናገረው ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ሐሳብ ፡ ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1866 ዓ. ም. ታሕሳስ ፡ 12 ቀን ፡ ለኤንግልስ ፡ የጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ይመልከቱ ። በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ኼክስሊ ፡ በአባባሉ ፡ ለአግኖስቲስዝምና ፡ ለህዩሚዝም ፡ ቦታ ፡ በመተው ፡ ማርክስ ፡ በጥብቅ ፡ ነቅፎታል ። ማርክስ ፡ በነፃነትና ፡ በአስፈላጊነት ፡ መካከል ፡ ስለአለው ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ መገንዘብ ፡ ይበጃል ፤ «አስፈላጊነት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ እስከአልታወቀ ፡ ድረስ ፡ ስውር ፡ ነው ። ነፃነት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ የአስፈላጊነት ፡ ጣዕሙ ፡ ሲታወቅ ፡ ነው ።» (ኤንግልስ «በአንቲ-ዱሪንግ») = ይህም ፡ ማለት ፡ የተፈጥሮ ፡ ነባራዊ ፡ ሕጎችና ፡ አስፈላጊነት ፡ ወደ ፡ ነፃነት ፡ የሚያደርጉት ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ ለውጥ ፡ እንዲሁም (በዚሁ ፡ አንፃር ፡ ከሌላው ፡ ተለይቶ ፡ በራሱ ፡ ያለ ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተውን ፡ ነገር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ጥቅም ፡ ወደሚውል ፡ ነገር ፡ መለወጥንና ፡ የነገሮችን ፡ ምንነት ፡ ወደ ፡ ክስተት ፡ መለወጥ ፡ ማወቅ) ማለት ፡ ነው ። «አሮጌው» ማቴሪያሊዝም ፡ የፎየርባኽን ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ጭምር ፤ (ከዚያም ፡ አልፎ ፡ «ብስሉን ፡ ከቀሊል ፡ ያልለየው» የቡኽነር ፡ የፎግትና ፡ የሞሌሾት ፡ ማቴሪያሊዝም) የሚከተሉት ፡ ዓበይት ፡ ጉድለቶች ፡ እንደአሉዋቸው ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ገልፀዋል ፤ (1) ይህ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ በአብዛኛው ፡ መካኒካል ፡ ሲሆን ፡ በጊዜው ፡ የነበረውን ፡ የኬሚስትሪና ፡ የባዮሎጂ ፡ ዕድገት ፡ ያላጠናቀረና (ዛሬም ፡ ደግሞ ፡ የማተርን ፡ የኤሌክትሪካል ፡ ቴዎሪ ፡ ያልተገነዘበ ፡ ነው ።) (2) አሮጌው ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ታሪካዊና ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ ያልሆነ ፤ (በፀረ ፡ ዲያሌክቲካዊነቱ ፡ ሜታፊዚካል ፡ የሆነ) ከዚያም ፡ የዕድገትን ፡ መስመር ፡ በሚገባና ፡ በጥሞና ፡ ያልተከታተለ ፡ ነው ። (3) «የሰውን ፡ ልጅ ፡ ምንነት» የተመለከተው ፡ በኅብረተሰብ «ውስብስብ ፡ ግንኙነቶች» ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆኑን ፡ ሳይሆን ፡ (ይህም ፡ በጉልህ ፡ በታሪክ ፡ የተረጋገ

ጠ ፡ ነው) የማይጨበጥ ፡ ረቂቅ ፡ አስተሳሰብ ፡ በመሆኑ ፤
ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ዓለምን ፡ ከጊዜ ፡ ጋር ፡ መለወጥ ፡ ሲሆን «አ
ብዮታዊና ፡ ተጨባጭ ፡ ተግባሮችን» ባለመረዳት ፡ ዓለምን
«በመተርጐም» ብቻ ፡ ተወስኗል ።

## ዲያሌክቲክስ ።

የሔግል ፡ ዲያሌክቲክስ ፡ እጅግ ፡ የተጣራና ፡ ግልጽ ፡
ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ስለዕድገት ፡ ያለው ፡ ትምህርታዊ ፡ ይዘ
ቱም ፡ የበለፀገ ፡ ክላሲካል ፡ የጀርመን ፡ ፍልስፍና ፡ ውጤት ፡
ቁንጮ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ያምኑ ፡
ነበር ። ከዚህም ፡ በተለየ ፡ ለዕድገት ፡ ማለት ፡ ለአዝጋሚ ፡
ለውጥ (ኢቮሉሽን) ሌላ ፡ ፈሊጥና ፡ ትርጉም ፡ ማውጣት ፡
በአንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ በትምሕርታዊ ፡ ይ
ዘቱም ፡ የደኸየ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ በተፈጥሮና ፡ በኅብረተ
ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የዕድገትን ፡ ጐዳና (ማለት ፡ በየጊ
ዜው ፡ በግብታዊ ፡ ሁኔታ ፡ በከፍተኛ ፡ ዕልቂትና ፡ በአብዮ
ት ፡ የሚኪያሔደውን ፡ ዕድገት ፡ ትክክለኛ ፡ መልክ ፡ ማቃ
ወስና ፡ ቅጥ ፡ ማሳጣት) ይሆናል ፡ ብለው ፡ ይገምቱ ፡ ነበር ።
ኤንግልስ ፡ ሲጽፍ ፤ «ትክክለኛ ፡ ዲያሌክቲክስን (ከሐሳ
ባዊነትና ፡ ከሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ ጥፋት ፡ አትርፈን) በተ
ፈጥሮ ፡ ማቴሪያላዊ ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ለማዋ
ል ፡ የምንችለው ፡ እኔና ፡ ማርክስ ፡ ብቻ ፡ ነበርን» «ተፈ
ጥሮ ፡ የዲያሌክቲክስ ፡ ምስክር ፡ ነው ። ለዘመናዊ ፡ የተፈጥ
ሮ ፡ ሳይንስም ፡ መዳበር ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋፅኦ ፡ በማድረግ ፡
ለምርምሩም ፡ ውጤት ፡ በየዕለቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ሁናቴዎችን ፡
ያበረከተ ፡ ሲሆን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሒደት ፡ ሜታፊዚካዊ ፡ ሳይ
ሆን ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጧል ።» ብሏል ።
(ይህ ፡ የተጻፈው ፡ ሬዲዮም ፡ ኤሌክትሮንስና ፡ የንጥረ ፡



ነገሮች ፡ አለዋወጥ ፡ ዘዴና ፡ ሌሎች ፡ ጥበቦች ፡ ከመታወ
ቃቸው ፡ በፊት ፡ ነው!)

ኤንግልስ ፡ ሲጽፍ ፤ «ታላቁ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡
ዓለምን ፡ መገንዘብ ፡ ያለብን ፡ ቀድሞ ፡ የነበሩ ፡ ነገሮች ፡ ው
ስብስብ ፡ አካል ፡ አድርገን ፡ ሳይሆን ፡ አዕምሮአችን ፡ ብ
ቻ ፡ ቋሚ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ የሚገምታቸው ፡ ግን ፡ እንደዕው
ነቱ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚመጡና ፡ የሚሔዱ ፡ የሚታዩና ፡
የሚጠፉ ፡ ነገሮች ፡ ሒደት ፡ ውስብስብ ፡ አካል ፡ አድርገ
ን ፡ ነው ። ይህ ፡ ታላቅ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ በተለይም ፡
ከሔግል ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ንቃተ ፡ ሕሊና ፡ በሰፊው ፡ የሰጠ ፡
ሲሆን ፡ በጠቅላላው ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የማይነቀፍና ፡ የማ
ይሻር ፡ ሆኖአል ። ይሁንና ፡ ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡
በቃል ፡ አውቆ ፡ መቀበልና ፡ በማንኛውም ፡ የምርመራ ፡
መስክ ፡ በዝርዝር ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ሁለት ፡ የተ
ለያዩ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።» «ለዲያሌክቲካዊ ፡ ፍልስፍና ፡
የመጨረሻ ፤ ፍጹምነትና ፡ ቅዱስነት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ የለ
ም ። ዲያሌክቲካዊ ፡ ፍልስፍና ፡ የማንኛውንም ፡ ነገርና ፡
በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ተለዋዋጭ ፡ ጠባ
ይ ፡ ያሳያል ። ይህ ፡ ፍልስፍና ፡ በጠቅላላው ፡ ሁናቴዎች
ን ፡ የሚመለከተው ፡ ባለማቋረጥ ፡ እየታዩ ፡ የሚጠፉ ፡ ዘ
ወትር ፡ ከዝቅተኛ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ የሚለዋወጡ ፡ አድር
ጐ ፡ ነው ። ዲያሌክቲካዊ ፡ ፍልስፍናም ፡ እራሱ ፡ በአዕም
ሮ ፡ ሲታሰብ ፡ የዚህ ፡ ሒደት ፡ ተንፀባራቂ ፡ ገጽ ፡ ነው ።»
በዚህ ፡ መሠረት ፡ እንደማርክስ ፡ አባባል ፡ ዲያሌክቲክስ
«የውጭው ፡ ዓለምና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሐሳብ ፡ ቅስቃሴ ፡
ጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ነው ።»

ይህን ፡ የሔግልን ፡ ፍልስፍና ፡ አብዮታዊ ፡ አቅጣጫ ፡
ተቀብሎ ፡ ያዳበረው ፡ ማርክስ ፡ ነው ። ዲያሌክቲካዊ ፡ ማ
ቴሪያሊዝም «ማንኛውም ፡ ፍልስፍና ፡ ከሌሎች ፡ ሳይን
ሶች ፡ በላይ ፡ እንዲሆን ፡ አይሻም ።» ከቀድሞ ፡ ፍልስፍና
«የአስተሳሰብ ፡ ሳይንስና ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ መሠረታዊ ፡

ሎጂክና ፡ ዲያሌክቲክስ ፡ ቀርተዋል ።»ዲያሌክቲክስ ፡ ማር
ክስ ፡ እንደሚገነዘበውና ፡ ከሔግልም ፡ ጋር ፡ እንደሚስማማ
በት ፡ የዕውቀትን ፡ ወይንም ፡ የኢፒስቲሞሎጂን ፡ ቴዎሪ ፡
ይጨምራል ። የዕውቀት ፡ አመጣጥም ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሒ
ደቱና ፡ ዕድገቱ ፡ ከዚያም ፡ ዕውቀት ፡ ካልነበረበት ፡ ወደተ
ገኘበት ፡ እንዴት ፡ እንደተለወጠ ፡ በታሪክ ፡ አንፃር ፡ መታ
የት ፡ መጠናትና ፡ መጠናቀር ፡ ይኖርበታል ።

በእኛ ፡ ዘመን ፡ የዕድገትና ፡ የአዝጋሚ ፡ ለውጥ ፡ መሠ
ረተ ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ንቃተ ፡ ሕሊና ፡ ሠርጎ ፡
የገባው ፡ በሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ አማካኝነት ፡ ሳይሆን ፡
በሌሎች ፡ መንገዶች ፡ ነው ። በሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ ተመሥ
ርተው ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ የቀመሩት ፡ ሐሳብ ፡ በአሁ
ኑ ፡ ጊዜ ፡ ካለው ፡ የአዝጋሚ ፡ ለውጥ ፡ አስተሳሰብ ፡ እጅግ ፡
የሰፋና ፡ ይዘቱም ፡ የበለፀገ ፡ ነው ። ራሱን ፡ የሚደግም ፡
ዕድገት ፤ ያለፈውን ፡ በተለየ ፡ መንገድ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረ
ጃ («የአፍራሽ ፡ አፍራሽ») ፤ መልሶ ፡ የሚያሳይ ፡ ዕ
ድገት ፤ በቀጥታ ፡ ሳይሆን ፡ በጥምዝምዝ ፡ መንገድ ፡ የ
ሚኪያሔድ ፡ ዕድገት ፤ አልፎ ፡ አልፎና ፡ በአደጋዎች ፡
እንዲሁም ፡ በአብዮታዊ ፡ መንገድ ፡ የሚመሠረት ፡ ዕድ
ገት ፤ «የጠቅላላው ፡ ሒደት ፡ መቋረጦች ፤» በአንድ ፡ በተ
ወሰነ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ወይንም ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ክስተት ፡
ውስጥ ፡ አለዚያም ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ኅብረተሰብ ፡
ውስጥ ፡ በሚቃረኑና ፡ በሚጋጩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኃይሎችና ፡
ዝንባሌዎች ፡ የሚመሠረቱ ፡ ከመጠን ፡ ወደ ፡ ጥራትና ፡
ከውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ወደ ፡ ተጨባጭ ፡ ዕድገት ፡ የሚኪያ
ሔዱ ፡ ለውጦች ፤ በማንኛውም ፡ ክስተት ፡ የሚገኙት ፡
ሁናቴዎች ፡ ሁሉ ፡ መደጋገፍና ፡ በመካከላቸው ፡ የሚገ
ኘው ፡ የማይደመሰሰው (ታሪክ ፡ ያለማቋረጥ ፡ አዳዲስ ፡ ሁ
ናቴዎችን ፡ ያሳያል) የተወሰኑ ፡ ሕግጋትን ፡ የሚከተል ፡
አንድ ፡ ዓይነትና ፡ ሁለንታዊ ፡ የሆነ ፡ የቅስቃሴ ፡ ሒደት ፡
የሚመሠርት ፡ ግንኙነት — ናቸው — (ከልማዳዊው ፡ ዕ



ድገት) ይበልጥ ፡ የዳበረው ፡ ዕድገት ፡ ትምህርታዊ ፡ መመሪ
ያዎች ፡ የሆነው ፡ የዲያሌክቲክስ ፡ ልዩ ፡ ጠባዮች ። (ማር
ክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1868 ዓ. ም. ጥር ፡ 8 ቀን ፡ በሽቴይን
«Wooden trichotomies» ላይ ፡ በመቀለድ ፡ የጻፈውን ፡
ደብዳቤ ፡ ይመልከቱ ።)

## የታሪክ ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ።

አሮጌው ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ የፀናና ፡ የተሟላ ፡ አለመሆ
ኑንና ፡ በአንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ብቻ ፡ በመወሰኑ «የኅብረተሰ
ብን ፡ ዕድገት ፡ ሳይንስ ፡ ከማቴሪያሊስት ፡ መሠረት ፡
ጋር ፡ በማዋሀድ ፡ እንደገና ፡ በአዲስ ፡ ማቅረብ» አስፈላጊ ፡
መሆኑን ፡ ማርክስ ፡ ተገነዘበው ። በጠቅላላው ፡ ሕልውና ፡
ሕሊናን ፡ የሚወስን ፡ እንጂ ፡ ሕሊና ፡ ሕልውናን ፡ የሚወ
ስን ፡ እንደአለመሆኑ ፡ መጠን ፡ የኅብረተሰብን ፡ ኑሮ ፡ በ
ሚመለከተውም ፡ ረገድ ፡ የኅብረተሰብን ፡ ሕሊና ፡ የሚወ
ስነው ፡ የኅብረተሰብ ፡ ሕልውና ፡ መሆኑን ፡ ማቴሪያሊዝ
ም ፡ ማስረዳት ፡ ይኖርበታል ፡ እንላለን ። «ቴክኒዮሎጂ»
ይላል ፡ ማርክስ (በ«ካፒታል» ቅጽ ፡ አንድ) ሲጽፍ ፡
«ሰው ፡ ከተፈጥሮ ፡ ጋር ፡ የሚያደርገውን ፡ ትግልና ፡ ኑሮ
ውን ፡ የሚደግፍበትን ፡ የምርት ፡ ስልት ፡ በመግለጽ ፡
ከዚያም ፡ ከኅብረተሰቡ ፡ ጋር ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶችና ፡
ከነሱም ፡ የሚፈልቁትን ፡ አስተሳሰቦች ፡ ስልት ፡ በገሐድ ፡
ያሳያል ።» «ስለፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሒስ» በተባለው ፡ መ
ጽሐፉ ፡ የመግቢያ ፡ ማብራሪያ ፡ ላይ ፡ ማርክስ ፡ በሚከተ
ሉት ፡ ቃላት ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ኅብረተሰብ
ና ፡ ከታሪኩ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ ግንኙነት ፡ እንዳለው ፡
መሠረታዊ ፡ መርሆውን ፡ በሚገባ ፡ ያስረዳል ፤

«ሰዎች ፡ በኑሮአቸው ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የምርት ፡
ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ በየበኩላቸው ፡ በሚያበረክቱትም ፡ ምር
ት ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ በፍላጐታቸው ፡ ያልታቀዱ ፡

ከምርት ፡ ኃይሎቻቸው ፡ ጋር ፡ አንፃር ፡ ለአንፃር ፡ እስከተወሰነ ፡ የዕድገት ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፡ አብረው ፡ የሚጓዙ ፡ የምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ አሏቸው ።

እነዚህ ፡ የምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ በአንድነት ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ንቃተ ፡ ሕሊና ፡ የሚታይበት ፡ የሕግና ፡ የፖለቲካ ፡ ላዕላይ ፡ መዋቅር ፡ የሚመሠረትበት ፡ የኅብረተሰብ ፡ የኤኮኖሚ ፡ መዋቅር ፡ ይመሠርታሉ ። በጠቅላላው ፡ በአንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የማኅበራዊ ፡ የፖለቲካና ፡ የሥልጣኔ ፡ አቋሙ ፡ የሚወስነው ፡ ወይንም ፡ የሚመራው ፡ ባለው ፡ የኑሮ ፡ ስልተ ፡ ምርት ፡ ነው ። የሰዎች ፡ ሕልውና ፡ የሚወሰነው ፡ በሕሊናቸው ፡ ሳይሆን ፡ በማኅበራዊ ፡ ሕልውናቸው ፡ ነው ። ሕሊናቸው ፡ የሚወስነው ፡ የአንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ የምርት ፡ ኃይሎች ፡ ከአንድ ፡ ከተወሰነ ፡ የዕድገት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ የምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ ማለት ፡ ሲሠሩበት ፡ ከቆዩት ፡ በሕግ ፡ እስተሳሰብ ፡ የሐብት ፡ ግንኙነት ፡ መስለው ፡ ከሚታዩት ፡ ጋር ፡ አለመስማማትና ፡ መጋጨት ፡ ይጀምራሉ ። እነዚህ ፡ ግንኙነቶች ፡ የምርት ፡ ኃይሎቹ ፡ ዕድገት ፡ ዓይነት ፡ መሆናቸው ፡ ይቀርና ፡ መሰንከያ ፡ የእግር ፡ ብረታቸው ፡ ይሆናሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አብዮታዊ ፡ ለውጥ ፡ ይጀመራል ። የማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ የኤኮኖሚ ፡ አቋም ፡ እየተለዋወጠ ፡ ሲሔድ ፡ ግዙፉና ፡ ጠቅላላው ፡ የኅብረተሰብ ፡ ላዕላይ ፡ መዋቅር ፡ በአንፃሩ ፡ እየተለወጠ ፡ ይሔዳል ። እነዚህ ፡ ለውጦች ፡ በሚታዩበት ፡ ጊዜ ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጠረውን ፡ ቅራኔ ፡ ሰዎች ፡ ተገንዝበው ፡ የሚታገሉበት ፡ በአጭሩ ፡ የርዕዮተ ፡ ዓለማቸው ፡ መሠረት ፡ በሆኑት ፡ በሕግ ፤ በፖለቲካ ፤ በሐይማኖት ፡ ወይም ፡ በፍልስፍና ፡ ለውጥና ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ ጥራት ፡ ሊወሰን ፡ በሚችለው ፡ የምርቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ በሚመለከተው ፡ የማቴሪያል ፡ ለውጥ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ማጣራት ፡ ያስፈልጋል ።



ስለአንድ ፡ ግለሰብ ፡ ያለን ፡ አስተያየት ፡ በአስተሳሰቡ ፡ ያልተመሠረተ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ የለውጥ ፡ ዘመን ፡ ባለው ፡ ንቃተ ፡ ሕሊና ፡ ልንመዝነው ፡ ወይንም ፡ ልንወስነው ፡ አንችልም ። እንዲያውም ፡ የንቃተ ፡ ሕሊናው ፡ መንስሔ ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በምርት ፡ ኃይሎችና ፡ በምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ መካከል ፡ ከሚፈጠረው ፡ ግጭት ፡ የሚጠነሰሱት ፡ የማቴሪያል ፡ ኑሮ ፡ ቅራኔዎች ፡ ናቸው ... » «የኤሽያዊያን ፤ የጥንት ፤ የፊውዳልና ፡ የዘመናዊ ፡ ቡርዥዋ ፡ ስልተ ፡ ምርት ፡ በኅብረተሰብ ፡ የኤኮኖሚ ፡ አመሠራረት ፡ በኩል ፡ በሰፊው ፡ ሲታዩ ፡ የተራማጅ ፡ ዘመኖች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።» (ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1866 ዓ. ም. ሐምሌ ፡ 7 ቀን ፡ ለኤንግልስ ፡ በደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ ባጭሩ ፡ «የሞያ ፡ ድርጅት ፡ የሚወሰነው ፡ በምርት ፡ መገልገያዎች ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ የኛ ፡ ቴዎሪ» በማለት ፡ የገለጸውን ፡ አስተያየት ፡ ተመልከት ።)

የታሪክ ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ፡ መታወቅ ፡ ወይንም ፡ ይበልጥ ፡ በትክክል ፡ ለመናገር ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ በማኅበራዊ ፡ ክስተት ፡ መስክ ፡ ባለማቋረጥ ፡ መቀጠሉና ፡ መስፋፋቱ ፡ በቀድሞ ፡ የታሪክ ፡ ቴዎሪዎች ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ከፍተኛ ፡ ጉድለቶች ፡ አስወግዷል ። ከነገረ ፡ ቀደም ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ቴዎሪዎች ፡ ቢበዛ ፡ ያደረጉት ፡ ቢኖር ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ታሪካዊ ፡ ድርጊቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የርዕዮተ ፡ ዓለም ፡ ምክንያቶች ፡ መመርመር ፡ ሲሆን ፡ የእነዚህን ፡ ምክንያቶች ፡ መነሻዎች ፡ ምንጭ ፡ ካለመመርመራቸው ፡ በላይ ፡ የማኅበራዊ ፡ ግንኙነቶችን ፡ ሥርዓት ፡ ዕድገት ፡ የሚመሩትን ፡ ነባራዊ ፡ ሕጐች ፡ አላረጋገጡም ። እንዲሁም ፡ የማቴሪያል ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ በደረሰበት ፡ ደረጃ ፡ የእነዚህን ፡ ግንኙነቶች ፡ ሥር ፡ አልተመለከቱም ። በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ታሪካዊ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ትክክል ፡ በሆነ ፡ ሳይንሳዊ ፡ መንገድ ፡ የሰፊውን ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ የማኅበራዊ ፡ ሁናቴዎችና ፡ በእ

ነዚህ ፡ ሁናቴዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚኪያሔዱትን ፡ ለውጦች ፡ ለመመርመር ፡ ያስቻለ ፡ ሲሆን ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ቴዎሪዎች ፡ ግን ፡ የሰፊውን ፡ ሕዝብ ፡ ተግባሮች ፡ አላቀፉም ። ከማርክስ ፡ በፊት ፡ የነበሩት «የኅብረተሰብና ፡ የታሪክ ፡ ጥናቶች» ቢበዛ ፡ ያደረጉት ፡ ቢኖር ፡ በደፈናው ፡ ያለማሰብ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ያልተጣሩ ፡ መረጃዎችን ፡ አስገኝተዋል ። ማርክሲዝም ፡ የተቃራኒ ፡ ዝንባሌዎችን ፡ ጠቅላላነት ፡ በመመርመርና ፡ እነሱንም ፡ ለተለያዩ ፡ መደቦች ፡ ኑሮና ፡ ምርት ፡ ወደ ፡ ተጨባጭ ፡ ሁናቴዎች ፡ በመለወጥ ፡ አንድ «የገነነ» ሐሳብ ፡ በመምረጥና ፡ እሱንም ፡ በመተርጐም ፡ ረገድ ፡ የነበረውን ፡ አድላዊነትና ፡ ሳብጀክቲቪዝም ፡ በማስወገድ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የተለየ ፡ ሁናቴ ፡ ሳይኖር ፡ ሁሉም ፡ ሐሳቦችና ፡ የተለያዩት ፡ ዝንባሌዎች ፡ በሙሉ ፡ የሚመነጩት ፡ ከምርት ፡ ኃይሎች ፡ ሁኔታ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የሶሺያል ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሥርዓቶችን ፡ መነሳት ፡ ዕድገትና ፡ ውድቀት ፡ ሒደት ፡ የሚያሳይ ፡ ሁሉን ፡ አቀፍ ፡ የሆነና ፡ ጠቅላላነት ፡ ያለው ፡ ጥናት ፡ አቅርቧል ። ሕዝቦች ፡ የራሳቸውን ፡ ታሪክ ፡ ይሠራሉ ፡ ግን ፡ የሕዝቦችን ፡ የሰፊውን ፡ ሕዝብ ፡ ተግባር ፡ ምክንያቶች ፡ የሚወስነው ፡ ማለት ፡ ለተቃራኒ ፡ ሐሳቦችና ፡ ጥረቶች ፡ ግጭት ፡ መነሻ ፡ የሚሆነው ፡ ምንድን ፡ ነው? በሰው ፡ ልጅ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮዎች ፡ ውስጥ ፡ እነዚህ ፡ ግጭቶች ፡ በጠቅላላው ፡ የሚያስከትሉት ፡ ምንድን ፡ ነው? ለሰው ፡ ልጅ ፡ ታሪካዊ ፡ ተግባሮች ፡ በሙሉ ፡ መሠረት ፡ ማለት ፡ ለኑሮ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ምርት ፡ ተጨባጭ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምንድን ፡ ናቸው? የእነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ዕድገት ፡ ሕግ ፡ ምንድን ፡ ነው? ማርክስ ፡ እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ በሙሉ ፡ በመገንዘብ ፡ ታሪክ ፡ በውስጡ ፡ የተለያዩ ፡ ሁናቴዎችና ፡ ግጭቶች ፡ ቢኖሩም ፡ በተጨባጭ ፡ ሕጐች ፡ የተወሰነ ፡ አንድ ፡ ነጠላ ፡ ሒደት ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሳይንሳዊ ፡ ጥናት ፡ አሳይቶናል ።



## የመደብ ፡ ትግል ።

በአንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የግማሾቹ ፡ አባሎች ፡ ጥረትና ፡ ፍላጐት ፡ ከሌሎቹ ፡ አባሎች ፡ ጥረትና ፡ ፍላጐት ፡ ጋር ፡ ይፃረራል ። ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በመሠረቱ ፡ ቅራኔዎች ፡ የሞሉበት ፡ ነው ። ታሪክም ፡ በሕዝቦችና ፡ በኅብረተሰቦች ፡ መካከል ፡ እንደዚሁም ፡ በውስጣቸው ፡ መፃረርና ፡ ተፃራሪ ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዳሉ ፡ ያመለክተናል ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ አብዮት ፤ አድኃሪነት ፤ ሠላም ፤ ጦርነት ፤ የድክመት ፤ የከፍተኛ ፡ ግስጋሴና ፡ የውድቀት ፡ መለዋወጫ ፡ ጊዜዎች ፡ በኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ማርክሲዝም ፡ ለዚህ ፡ የተወሳሰበና ፡ ዝብርቅርቁ ፡ የወጣ ፡ መስሎ ፡ ለሚታየው ፡ ሁኔታ ፡ ዕውቀት ፡ ወሳኝ ፡ የሆኑትን ፡ ሕጐች ፡ የሚመራውን ፡ የመደብ ፡ ትግልን ፡ ቴዎሪ ፡ አቅርቧል ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍላጐቶችንና ፡ ጥረቶችን ፡ ውጤት ፡ ሳይንሳዊ ፡ ትንታኔ ፡ መስጠት ፡ የሚቻለው ፡ በአንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ወይንም ፡ በተለያዩ ፡ ኅብረተሰቦች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ አባሎች ፡ በተለያዩ ፡ ፍላጐቶችና ፡ ጥረቶች ፡ በጠቅላላው ፡ በማጥናት ፡ ነው ። በአንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ተፃራሪ ፡ የሆኑት ፡ ሁናቴዎች ፡ የሚፈጠሩት ፡ እያንዳንዱ ፡ ኅብረተሰብ ፡ በተከፋፈለባቸው ፡ መደቦች ፡ የኑሮ ፡ ዓይነትና ፡ አቋም ፡ ልዩነት ፡ ላይ ፡ ነው ። ማርክስ ፡ «በኮሙኒስት ፡ ማኒፌስቶ» «እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ የኅብረተሰብ ፡ ታሪክ ፡ የመደብ ፡ ትግል ፡ ታሪክ ፡ ነው» ብሎ ፡ በጻፈው ፡ ላይ ፡ ኤንግልስም ፡ ከጥንታዊው ፡ ኅብረተሰብ ፡ በስተቀር ፡ የሚለውን ፡ አክሎበታል ። ነፃ ፡ ሰውና ፡ በባርነት ፡ የሚኖር ፤ ጨዋና ፡ ተራ ፡ ሰው ፤ ባለርስትና ፡ ገበሬ ፤ በአንድ ፡ ቃል ፡ ጨቋኝና ፡ ተጨቋኝ ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲቃወሙ ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ አልፈው ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ አብዮታዊ ፡ ለውጥ ፡ የሚያስከትል ፡ አለበለዚያም ፡ የሁለቱ

ንም : ተቃራኒ : ወገኖች : ጥፋት : የሚያስከትል : የማያቋርጥ : አንዳንዴም : ስውር : አንዳንዴም : ግልጽ : የሆነ : ትግል : ያደርጋሉ ... ከፊውዳል : ኅብረተሰብ : ርዝራዥ : የተወለደው : የዘመኑ : የቡርዥዋ : ኅብረተሰብ : በመደቦች : መካከል : ያለውን : ቅራኔ : ገና : አላስወገደም ። ይልቁንም : ያስገኘው : ቢኖር : አዲስ : መደቦች : መፍጠር ፤ አዳዲስ : የጭቆና : ሁናቴዎች : መመሥረትና : በጥንታዊው : ምትክ : አዲስ : የትግል : ዓይነት : ማፍለቅ : ነው ። ያለንበት : ዘመን : ማለት : የቡርዥዋው : ዘመን : እነዚህ : ጠባዮች : ያሉት : ሲሆን : የመደብ : ቅራኔዎችን : አቃሏል ። በጠቅላላው : ኅብረተሰብ : ፊት : ለፊት : ተፋጥጠው : በሚገኙ : ሁለት : ተቃራኒ : ካምፖች : ማለትም : ሁለት : ከፍተኛ : መደቦች : ይከፈላል — እነሱም : የቡርዥዋውና : የወዝ : አደሩ : መደቦች : ናቸው ። »ከታላቁ : የፈረንሳይ : አብዮት : ወዲህ : በብዙ : አገሮች : ውስጥ : እንደታየው : የአውሮፓ : ታሪክ : የሚያስረዳው : የታሪክ : ሁናቴዎች : ሥረ : መሠረታቸው : የመደቦች : ትግል : መሆኑን : ነው ። በፈረንሳይ : የቀድሞ : መንግሥት : እንደገና : ሥልጣን : በያዘበት : ጊዜ[8] : የሁናቴዎችን : ጠቅላላ : አመጣጥ : ተመልክተው : ለፈረንሳይ : ታሪክ : በሙሉ : ቁልፉ : የመደብ : ትግል : መሆኑን : የተገነዘቡ : ታሪክ : አዋቂዎች (ቲየሪ ፤ ጊዞ ፤ ሚኚየና : ቲየር) ሊፈጠሩ : ችለዋል ። የአዲሱ : ዘመን ፤ ቡርዥዋው : ሙሉ : ድል : የተጐናፀፈበት : ዘመን (በጠቅላላ : እንኳ : ባይሆን) በሰፊ : የድምፅ : አሰጣጥ : ምርጫ : ድርጅቶች ፤ ለሕዝቡ : በሰፊው : በየዕለቱ : የሚሠራጩ : ርካሽ : ጋዜጣዎችና : ወዘተ : የተስፋፉበት : ዘመን ፤ ኃይለኛና : እየተስፋፉ : የሚሔዱ : የሠራተኞች : የተቀጣሪዎችና : እንዲሁም : የሌሎች : ድርጅቶች : የተፈጠሩበት : ዘመን (ምንም : እንኳ : አንዳንዴ : በአንድ : አቅጣጫ : የተወሰነ : ቢሆንም : ወይንም «በሠላም» እና «በሕገ : መንግሥት» የተወሰነ : ቢሆንም) የመ



ደብ : ትግል : የሁናቴዎች : ዋናው : መነሾ : መሆኑን : በጉልህ : አሳይቷል ። ከ«ኮሙኒስት : ፓርቲ : ማኒፌስቶ» ላይ : የተገኘው : የሚቀጥለው : የማርክስ : አገላለጽ : በዘመናዊ : ኅብረተሰብ : ውስጥ : እያንዳንዱ : መደብ : ያለውን : አቋም : በሚመለከተው : ረገድ : የየአንዳንዱን : መደብ : የዕድገት : ሁኔታ : በመጠቆም : ማርክስ : ከኅብረተሰብ : ሳይንስ : ለማግኘት : የፈለገውን : ውጤት : ያስረዳል ። «በዛሬው : ጊዜ : ከቡርዥዋው : ጋር : ተፋጥጠው : ከሚገኙት : መደቦች : በሙሉ : ሐቀኛው : አብዮታዊ : መደብ : የወዝ : አደሩ : መደብ : ነው ። ሌሎቹ : መደቦች : ዘመናዊ : ኢንዱስትሪ : እየተስፋፋ : ሲሔድ : እየመነመኑ : በመሔድ : በመጨረሻ : ላይ : ይጠፋሉ ። የኢንዱስትሪው : ልዩና : ዓይነተኛ : ኃይል : ወዝ : አደሩ : ነው ። በመካከለኛ : ኑሮ : የሚገኘው : መደብ : ማለት : ባለትንሽ : ፋብሪካው ፤ ባለሱቁ ፤ ቀጥቃጩና : ገበሬው : የመካከለኛው : መደብ : ክፍል : ከመሆን : እንዳይሠረዙና : ኑሮአቸውም : ከዚሁ : ዝቅ : እንዳይል : ሁሉም : በየበኩሉ : ቡርዥዋውን : ይታገሉታል ። እነዚህ : በዚህ : ጠባያቸው : የነበራቸውን : የጥንቱን : ልማድ : ለመጠበቅ : የሚፍጨረጨሩ : እንጂ : አብዮተኞች : አይደሉም ። እንዲያውም : የታሪክን : ጐማ : ወደ : ኋላ : ለማሽከርከር : የሚሞክሩ : በመሆናቸው : አድኃሪዎች : ናቸው ። በአጋጣሚም : አብዮተኛ : ሆነው : ቢገኙ : ከወዝ : አደሩ : መደብ : ጋር : ለመቀላቀል : አቋማቸው : ያመቸ : በመሆኑ : ነው ። በዚህም : መንገድ : የሚከላከሉት : የጊዜውን : ሳይሆን : የወደፊት : ጥቅማቸውን : ነው ። በወዝ : አደሩ : መስመር : ለመሰለፍም : የራሳቸውን : አቋም : ይክዳሉ ።» ማርክስ «እያንዳንዱ : የመደብ : ትግል : ለምንና : እንዴት : የፖለቲካ : ትግል : እንደሆነ» ቁልጭ : አርጐ : በማስረዳት : የየአንዳንዱን : መደብና : አንዳንዴም : በአንድ : መደብ : ውስጥ : የሚገኙትን : ቡድኖችና : በኑሮ : ደረጃ : የተከፋ

ፈሉትን ፡ ወገኖች ፡ አቋም ፡ ትንታኔ ፡ የሚገልጹ ፡ የማቴ
ሪያሊስት ፡ ታሪክ ፡ ጥናት ፡ ጉልህና ፡ ሰፊ ፡ ምሳሌዎች ፡ በብ
ዙ ፡ የታሪክ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ አቅርቧል ። ይህ ፡ ከላይ ፡
የተጠቀሰው ፡ የ «ኮሙኒስት ፡ ፓርቲ ፡ ማኒፌስቶ» ጥቅስ ፡
የታሪካዊ ፡ ዕድገትን ፡ ለመወሰን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ው
ስብስብ ፡ ግንኙነቶችን ፡ ከአንድ ፡ መደብ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡
መደብ ፡ የሚደረገውንና ፡ ከአሮጌው ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ የሚ
ደረገውን ፡ ሽግግር ፡ ማርክስ ፡ በሰፊው ፡ ማጥናቱን ፡ ያስረ
ዳል ።

የማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርት ፡ ከሁሉም ፡ ይበል
ጥ ፡ የተጣራ ፡ የተሟላና ፡ የተጠቃለለ ፡ ሲሆን ፡ ቴዎሪውን ፡
በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚገባ ፡ የሚያውል ፡ ነው ።

## የማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርት ።

ማርክስ ፡ በ «ካፒታል» መግቢያ ፡ ላይ ፡ ባሠፈረው ፡
ጽሑፍ «የዚህ ፡ ሥራ ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የዘመናዊ ፡ ኅብረ
ተሰብን ፡ ማለት ፡ የካፒታሊስትን ፡ የቡርዥዋ ፡ ኅብረተሰ
ብን ፡ ቅስቃሴ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሕግ ፡ በጉልህ ፡ ለማሳየት ፡ የታ
ቀደ ፡ ነው» ይላል ። የማርክስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ መመሪያ ፡
ይዘት ፡ በአንድ ፡ በታሪክ ፡ አመጣጡ ፡ የተወሰነ ፡ ኅብረተ
ሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ አመ
ሠራረታቸውን ፡ ዕድገታቸውንና ፡ ውድቀታቸውን ፡ መመርመ
ር ፡ ነው ። በአንድ ፡ በካፒታሊስት ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡
ትልቁ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሸቀጣሸቀጦችን ፡ ማምረት ፡ ስለሆ
ነ ፡ የማርክስም ፡ ትንተና ፡ የሚጀምረው ፡ ከሸቀጣሸቀጦ
ች ፡ ነው ።

## ዋጋ ።

አንድ ፡ ሸቀጥ ፡ የመጀመሪያ ፡ ተግባሩ ፡ የሰውን ፡ ፍላ
ጐት ፡ ማርካት ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ እቃ ፡



የሚለወጥ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የአንድ ፡ ነገር ፡ ባገልግሎት ፡
ላይ ፡ መዋል ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋ ፡ ይሰጠዋል (use-
value) ። አንድ ፡ ነገር ፡ የሚለወጥበት ፡ ዋጋ (ወይንም ፡
ባጭሩ ፡ ዋጋው) ማለት ፡ የዕቃው ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋዎ
ች ፡ ብዛት ፡ በሌላ ፡ ዕቃ ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋዎች ፡ ብዛት ፡
የሚለወጥበት ፡ መለኪያና ፡ መጠን ፡ ማለት ፡ ነው ። በብዙ ፡
ሚሊዮን ፡ የሚቆጠሩ ፡ በየቀኑ ፡ የሚፈፀሙ ፡ የዚህ ፡ ዓይ
ነት ፡ ልውውጦች ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆንና ፡ ወደር ፡ የሌለ
ው ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡
ከሌላ ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋ ፡ ካለው ፡ ዕቃ ፡ ጋር ፡ ሊመጣ
ጠን ፡ እንደሚችል ፡ ያስረዱናል ። በአንድ ፡ የተወሰነ ፡ የ
ኅብረተሰብ ፡ ግንኙነቶች ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ ባለማቋረ
ጥ ፡ በየጊዜው ፡ በሚመጣጠኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ወይንም ፡ ነ
ገሮች ፡ መካከል ፡ የሚገኘው ፡ የጋራ ፡ ባህርይ ፡ ምንድን ፡
ነው? በጋራ ፡ ቤት ፡ ያላቸው ፡ ባህርይ ፡ ወይንም ፡ ተመሳሳ
ይነታቸው ፡ ሁሉም ፡ የሙያ ፡ ምርት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።
ሰዎች ፡ ምርቶችን ፡ በሚለዋወጡበት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ የተ
ለያዩ ፡ ሙያዎችን ፡ ያመጣጥናሉ ፡ ማለትም ፡ በዋጋ ፡ ያ
ስተካክላሉ ። ሸቀጣሸቀጦችን ፡ ማምረት (በሙያ ፡ ክፍፍል ፡
መሠረት) እያንዳንዱ ፡ ግለሰብ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ የተለ
ያዩ ፡ ምርቶች ፡ የሚያቀርብበትና ፡ እነዚህ ፡ ምርቶች ፡ በ
ሙሉ ፡ በልውውጥ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ በዋጋ ፡ የሚስ
ተካከልበትና ፡ የሚመጣጠንበት ፡ የኅብረተሰብ ፡ ግንኙ
ነቶች ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የሸቀጣሸቀጦች ፡
የጋራ ፡ ባህርይአቸው ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው ፡ የአንድ ፡ የምር
ት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሙያ ፡ ወይንም ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ሙያ ፡
ሳይሆን ፡ በጉልህ ፡ ሊታይ ፡ የማይቻለው ፡ የሰው ፡ ሙያ ፡
ማለትም ፡ በጠቅላላው ፡ የሰው ፡ ጉልበት ፡ ነው ። በሸቀ
ጣሸቀጦች ፡ ዋጋዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ የሚመዘነው ፡ የ
አንድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ የሙያ ፡ ኃይል ፡ ያው ፡ የሰው ፡ ጉልበ
ት ፡ ነው ። በብዙ ፡ ሽህ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቆጠሩ ፡ የዕቃ ፡

ወይንም ፡ የሸቀጣሸቀጦች ፡ ልውውጦች ፡ ይህንኑ ፡ ያረጋግጣሉ ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሸቀጥ ፡ በውስጡ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነው ፡ የሙያ ፡ ሰዓት ፡ የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የአንድ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፤ ያንድ ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋ ፤ ዝቅተኛነቱና ፡ ከፍተኛነቱ ፡ የሚወሰነው ፡ አንድን ፡ ሸቀጥ ፡ ለማምረት ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ ዕድገት ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ሙያ ፡ በሚባክነው ፡ ወይንም ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ ዕድገት ፡ ከሚያስፈልገው ፡ የሙያ ፡ ሰዓት ፡ ለዚሁ ፡ ምርት ፡ በሚጠፋው ፡ ጊዜ ፡ መጠን ፡ መሠረት ፡ ነው ። «ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምርቶቻችንን ፡ በልውውጥ ፡ በዋጋ ፡ ስናስተካክላቸው ፡ ይህንኑ ፡ በማድረግ ፡ የምንፈጽመው ፡ በእነዚህ ፡ ምርቶች ፡ ላይ ፡ የተፈጸሙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሙያዎች ፡ በሰው ፡ ሙያተኛነት ፡ ወይንም ፡ ለሥራው ፡ በባከነው ፡ ጉልበት ፡ እናመዛዝናቸዋለን ። ይህ ፡ ለኛ ፡ ባይታወቀንም ፡ ሁልጊዜም ፡ እየፈጸምነው ፡ ነው ።» የአንድ ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ግንኙነት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ የጥንት ፡ ኤኮኖሚስት ፡ እንደተናገረው ፤ በእርግጥም ፡ በመጠቅለያ ፡ የተሸፈነ ፡ ግንኙነት ፡ ማለት ፡ ነው ። ዋጋ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ ልንገነዘብ ፡ የምንችለው ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግሞ ፡ በሚፈጸመው ፡ በዕቃዎች ፡ ልውውጥ ፡ ሰፊ ፡ ክስተት ፡ ውስጥ ፡ በሚታዩ ፡ ግንኙነቶችና ፡ በአንድ ፡ በተለየ ፡ ታሪካዊ ፡ ኅብረተሰብ ፡ የምርት ፡ ግንኙነቶች ፡ ሥርዓት ፡ ስንመለከተው ፡ ብቻ ፡ ነው ። «ሸቀጦች ፡ በሙሉ ፡ እንደዋጋ ፡ ሲታዩ ፡ ከሙያ ፡ ሰዓት ፡ የተፈጠሩ ፡ አካሎች ፡ ናቸው ።» ካርል ፡ ማርክስ ፡ በሸቀጦች ፡ ውስጥ ፡ ተከማችቶ ፡ ወይንም ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚገኘውን ፡ የሙያ ፡ መንታ ፡ ጠባይ ፡ በዝርዝር ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ የዋጋንና ፡ የገንዘብን ፡ ዓይነት ፡ መመርመር ፡ ጀመረ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የማርክስ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ዋጋ ፡ በገንዘብ ፡ መተመን ፡ የጀመረበትንና ፡ አመጣጡን ፡ እንዲሁም ፡ የዕቃ ፡ በቃን ፡ ልውውጥ ፡



ዕድገት ፡ ታሪካዊ ፡ ሒደት ፡ ማጥናት ፡ ነበር ። የዕቃ ፡ በዕቃ ፡ ለውጥ ፡ ከጀመረበት (ማለት ፡ ዝቅተኛው ፡ ወይንም ፡ ድንገተኛው ፡ የዋጋ ፡ ዓይነት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ከነበረው ፡ በተለያዩ ፡ ዕቃዎችና ፡ በነሲብ (incidental) ይደረግ ፡ ከነበረው ፡ ልውውጥ ፡ ማለትም) የአንድ ፡ ዕቃ ፡ የተወሰነ ፡ ብዛት ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ዕቃ ፡ በተወሰነ ፡ ብዛት ፡ ይለወጥ ፡ ከነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሁለንታዊ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ዋጋ ፡ ማለትም ፡ የተለያዩ ፡ ሸቀጦች ፡ ሁልጊዜም ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሸቀጥ ፡ ወደ ፡ መለወጥ ፡ እስከደረሱበት ፡ ጊዜና ፡ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ በገንዘብ ፡ መገበያየት ፡ እስከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ማለት ፡ ወርቅ ፡ የተለየ ፡ ሸቀጥ ፡ ሆኖ ፡ አጠቃላይ ፡ መገበያያ ፡ እስከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነበረውን ፡ ሒደት ፡ መመርመርና ፡ ማጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ገንዘብ ፡ የዕቃ ፡ በዕቃ ፡ ልውውጥና ፡ የሸቀጦች ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ወይንም ፡ ምርት ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የግለሰብን ፡ ሙያ ፡ ማኅበራዊ ፡ ጠባይና ፡ በገበያ ፡ በተዋሀዱት ፡ ግለሰብ ፡ አምራቾች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ኅብረተሰብዓዊ ፡ ግንኙነት ፡ ይሸፍናል ፡ እንዲሁም ፡ ይደብቃል ። ማርክስ ፡ የገንዘብን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ በሰፊው ፡ መርምሯል ። እዚህ ፡ ላይ (በማርክስ «ካፒታል» መጽሐፍ ፡ የመጀመሪያ ፡ ምዕራፎች ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ) መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ረቂቅ ፡ የማይጨበጥና ፡ ከሁናቴዎች ፡ ተውጣጥቶ ፡ የቀረበ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ ከዕቃዎች ፡ ልውውጥና ፡ ከሸቀጦች ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ ታሪክ ፡ ተጨባጭ ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ ከተሰበሰበ ፡ መረጃ ፡ የተገኘ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። «ገንዘብን ፡ ብንመለከት ፡ ሕልውናው ፡ በሸቀጦች ፡ ለውጥ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ደረጃ ፡ መኖሩን ፡ ያሳየናል ። ገንዘብ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ የተለዩ ፡ ተግባሮች ፡ ማለት ፡ የሸቀጦች ፡ ማመዛዘኛ ፤ መገበያያ ፡ በመሆን ፡ ወይንም ፡ ከእጅ ፡ ወደ ፡ እጅ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ በመሆን ፡ የክፍያ ፡ መሣሪያ ፡

በመሆንና ፡ የንብረት ፡ ማከማቻ ፡ ወይም ፡ ሁለንታዊ ፡ አገልጋይ ፡ በመሆን ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ እንደተደጋጋሚነታቸው ፡ መጠን ፡ በማኅበራዊ ፡ ምርት ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ደረጃዎችን ፡ ያመለክቱናል («ካፒታል» ፤ ቅጽ ፡ አንድ) ።

## ትርፍ ፡ ዋጋ (Surplus value)

በሸቀጦች ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ካፒታል ፡ ይለወጣል ። የሸቀጥ ፡ ዝውውር ፡ ቅንብር ፡ formula ሸ — ገ — ሸ (ሸቀጥ — ገንዘብ — ሸቀጥ) ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ አንድን ፡ ሸቀጥ ፡ ሸጦ ፡ ሌላ ፡ ሸቀጥ ፡ መግዛት ፡ ማለት ፡ ነው ። የካፒታል ፡ ጠቅላላ ፡ ቅንብር ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በተለየ ፡ ገ — ሸ — ገ (ገንዘብ — ሸቀጥ — ገንዘብ) ሲሆን ፡ በትርፍ ፡ ለመሸጥ ፡ መግዛት ፡ ማለት ፡ ነው ። በዝውውር ፡ ላይ ፡ በዋለው ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የተፈጠረው ፡ ጭማሪ ፡ በማርክስ ፡ አባባል ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ (surplus value) ይባላል ። በካፒታሊስቶች ፡ የገንዘብ ፡ ዝውውር ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የገንዘብ «ዕድገት» ግልጽ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህ «ዕድገት» ነው ፡ ገንዘብን ፡ የተለየ ፡ የማኅበራዊ ፡ የምርት ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ወደ ፡ ካፒታል ፡ የሚለውጠው ። ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ ከሸቀጦች ፡ ዝውውር ፡ አይፈጠርም ፤ ምክንያቱም ፡ የሸቀጦች ፡ ዝውውር ፡ ማለት ፡ በዋጋ ፡ አቻ ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎች ፡ ልውውጥ ፡ ብቻ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከመሸጫ ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ሊፈጠር ፡ አይችልም ፡ ምክንያቱም ፡ ገዥዎችና ፡ ሻጮች ፡ በጋራ ፡ ቤት ፡ የሚደርስባቸው ፡ ክስረትና ፡ የሚያገኙት ፡ ትርፍ ፡ ስለሚያስተካክላቸው ፡ ነው ። ነባራዊው ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ክስተት ፡ ሳይሆን ፡ ሰፊና ፡ መካከለኛ ፡ ማኅበራዊ ፡ ክስተት ፡ ነው ። «ባለገንዘቦች» ትርፍ ፡ ዋጋውን ፡ ለማግኘት



«በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ በሚውልበትና ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ዋጋ ፡ እየፈጠረ ፡ የሚሔድ ፡ የጠቃሚነት ፡ ዋጋው ፡ የዋጋ ፡ ምንጭ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስችል ፡ የተለየ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ሸቀጥ ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው ።» የዚህ ፡ ዓይነትም ፡ ሸቀጥ ፡ አለ ። እሱም ፡ የሰው ፡ የሙያ ፡ ኃይል ፡ ጉልበት ፡ ነው ። ይህ ፡ ጉልበት ፡ በሚያልቅበትና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ ሙያ ፡ ነው ። ሙያ ፡ ደግሞ ፡ ዋጋ ፡ ያመጣል ። ባለገንዘቡ ፡ ጉልበትን ፡ በዋጋው ፡ ይገዛል ። የጉልበት ፡ ዋጋ ፡ እንደሌሎች ፡ ሸቀጦች ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ የሚወሰነው ፡ ተፈላጊውን ፡ ጉልበት ፡ ለመፍጠር ፡ በሚገባው ፡ ለማኅበራዊ ፡ ዕድገት ፡ ከሚያስፈልገው ፡ የሙያ ፡ ሰዓት ፡ በሚባክነው ፡ ነው (ይህም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሠራተኛውንና ፡ ቤተሰብን ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚያስችለው ፡ ሒሳብ ፡ ማለት ፡ ነው) ። ባለገንዘቡ ፡ ጉልበት ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ጉልበት ፡ ለአሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንበል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ መብት ፡ አለው ። ይሁንና ፡ በስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ («በተገቢው» የሙያ ፡ ሰዓት) ሠራተኛው ፡ እሱንና ፡ ቤተሰቡን ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚበቃ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ምርት ፡ ይመርታል ። በሚቀጥሉት ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ («ከተገቢው ፡ በላይ» በሆነው ፡ ትርፍ (surplus) የሙያ ፡ ሰዓት) ካፒታሊስቱ ፡ የማይከፍልበት «ትርፍ» ምርት ፡ ማለትም ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ ያተርፋል ። ስለዚህ ፡ በምርት ፡ ሒደት ፡ አንፃር ፡ በካፒታል ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ መታወቅ ፡ አለባቸው ። እነሱም ፡ ቋሚ ፡ ካፒታል ፡ ማለት ፡ በምርት ፡ መሣሪያዎች (በማሽነሪ ፤ በሥራ ፡ ዕቃዎች ፤ በጥሬ ፡ ሸቀጦች ፡ ወዘተ.) ላይ ፡ የሚውለው ፡ ገንዘብ ፡ አንደኛው ፡ ሲሆን ፡ የምርት ፡ መሣሪያዎቹም ፡ ዋጋ ፡ ያለአንዳች ፡ ለውጥ (ወዲያውኑ ፡ ወይንም ፡ ከፊል ፡ በከፊል) ወደተሰራው ፡ ምርት ፡ ይተላለፋል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በሙያ ፡ ኃይል ፡ ላይ ፡ ወይንም ፡ ለሥራ ፡ ጉልበት ፡ የሚወጣው ፡ ተለዋዋጭ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡

ካፒታል ፡ ነው ። የዚህ ፡ ካፒታል ፡ ዋጋ ፡ ዘወትር ፡ አንድ ፡
ዓይነት ፡ ሳይሆን ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ እየፈጠረ ፡ ከሙያው ፡
ሒደት ፡ ጋር ፡ የሚያድግ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ካፒታል ፡ የሠ
ራተኛን ፡ ጉልበት ፡ እንዴት ፡ እንደሚበዘብዝ ፡ ለመግለጽ ፡
ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ መመዛዘን ፡ ያለበት ፡ ከጠቅላላው ፡ ካፒታል ፡
ጋር ፡ ሳይሆን ፡ ከተለዋዋጩ ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ነ
ው ። ስለዚህ ፡ ከላይ ፡ በተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ ዓይነት ፡ የት
ርፍ ፡ ዋጋ ፡ መጠን (ብዝበዛው) ማርክስ ፡ እንደሚለው ፡
6 በ 6 ይሆናል ፡ ይህም ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ለካፒታል ፡ አመጣጥ ፡ ወይንም ፡ መነሻ ፡ ሁለት ፡ ተቀ
ዳሚ ፡ ምክንያቶች ፡ ነበሩ ። የመጀመሪያው ፡ የሸቀጣሸ
ቀጥ ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ በጠቅላላው ፡ በመጠኑ ፡ ከፍተኛ ፡
ደረጃ ፡ በደረሰበት ፡ ሁናቴ ፡ በግለሰቦች ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡
ገንዘብ ፡ እየተከማቸ ፡ ሲሔድ ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡
በጣምራ ፡ መንገድ «ነፃ» የሆነ ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ሲኖር ፡
ማለት ፡ የሙያ ፡ ኃይሉን ፡ ጉልበቱን ፡ ለመሸጥ ፡ በምንም ፡
ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ያልታገደ ፤ በጠቅላላው ፡ ከግብርና
ና ፡ ከሌላ ፡ ዓይነት ፡ ምርት ፡ ጋር ፡ ያልተሳሰረ ፤ በምንም ፡
ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ያልታሰረ ፤ ግዴታ ፡ የሌለበት ፡ ጉልበቱን ፡
ካልሸጠ ፡ ለመኖር ፡ የማይችል ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ሲኖር ፡
ነው ። ሰርፕላስ ፡ ቫሉዮን ፡ ለማዳበር ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ መንገ
ዶች ፡ አሉ ። አንደኛው ፡ የሥራውን ፡ ቀን ፡ ማራዘም (አ
ብሰሉት ፡ ሰርፕላስ ፡ ቫሉዮ) ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ አስፈላ
ጊውን ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ መቀነስ (ሬላቲቭ ፡ ሰርፕላስ ፡ ቫሉ
ዮ) ማርክስ ፡ ስለአብሰሉት ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ ሲተነትን ፡ ከ
አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ አ
ሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሠራተኛ
ው ፡ መደብ ፡ የሥራው ፡ ቀን ፡ እንዲያጥርለት ፡ ያደረገው
ን ፡ ትግልና ፡ በዘመኑ ፡ የነበሩት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሥራ
ውን ፡ ቀን ፡ ለማስረዘም ፡ የፈጸሙትን ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት
ና ፡ በኋላም ፡ በ 19 ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሥራውን ፡ ቀ



ን ፡ ለማሳጠር ፡ ያወጡትን ፡ የፋብሪካ ፡ የሥራ ፡ ደንብ ፡
የሚያብራራ ፡ ስዕል ፡ ያቀርባል ። «ካፒታል» ከተፈጠረ ፡
ወዲህ ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የተኪያሔደው ፡
የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ይህን ፡ ስዕል ፡ ይበልጥ ፡
አጉልተው ፡ የሚያሳዩ ፡ በሺ ፡ የሚቆጠሩ ፡ አዳዲስ ፡ ጠ
ቃሚ ፡ ማስረጃዎች ፡ አበርክቷል ።

ማርክስ ፡ የሬላቲቭ ፡ ትርፍ ፡ ዋጋን ፡ ምርት ፡ ሲተነት
ን ፡ በሙያ ፡ የምርት ፡ ዕድገት ፡ በኩል ፡ ካፒታሊዝም ፡
ያለፈባቸውን ፡ ሦስት ፡ መሠረታዊ ፡ የታሪክ ፡ ደረጃዎች ፡
ይመረምራል ። 1) ቀላል ፡ ተራድኦ ፤ 2) የሙያ ፡ ክፍፍል
ና ፡ ማኑፋክቸር (የፋብሪካ ፡ ሥራ) ፤ 3) ማሽነሪና ፡ ሰፊ ፡
የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ። ማርክስ ፡ የካፒታሊስት ፡ ዕድገት
ን ፡ ቁልጭ ፡ ያለ ፡ መሠረታዊ ፡ ጠባይ ፡ አጉልቶ ፡ ያሳየ ፡
ለመሆኑ ፡ ስለሩስያ «የእጅ ፡ ጥበብ» ኢንዱስትሪዎች ፡ የ
ተደረገው ፡ ጥናት ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ ሁለት ፡ ደረጃዎ
ች ፡ ለማብራራት ፡ ጠቃሚ ፡ መረጃዎች ፡ የሚያበረክት ፡
በመሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ። ሰፊ ፡ የማሽን ፡
ኢንዱስትሪ ፡ ዕድገት ፡ ያለው ፡ አብዮታዊ ፡ ተፅዕኖ ፡ ማር
ክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1867 ዓ. ም. እንደገለጸው ፡ ከዚያን ፡
ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ባለፈው ፡ ግማሽ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን (በሩስያ ፤
በጃፓንና ፡ በሌሎች ፡ አገሮች) ሊታይ ፡ ችሏል ።

ከዚሁ ፡ በመቀጠል ፡ ከማርክስ ፡ ትንተና ፡ አዲሱና ፡
ከፍተኛው ፡ ውጤት ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ በከፊል ፡ ወደ ፡ ካፒታ
ል ፡ እየተለወጠ ፡ የካፒታል ፡ ክምችት ፡ ሲፈጠር ፡ የሚያ
ሳየው ፡ ክፍል ፡ ነው ። የካፒታሉም ፡ ክምችት ፡ ግልጋሎ
ት ፡ ለካፒታሊስቱ ፡ የግል ፡ ፍላጐትና ፡ ጥቅም ፡ ሳይሆን ፡
የሚውለው ፡ ምርትን ፡ ለማበራከቻ ፡ ነው ። ማርክስ ፡ ከአ
ዳም ፡ ስሚት ፡ ጀምሮ የነበሩት ፡ የፓለቲካ ፡ ኤኮኖሚስ
ቶች ፡ ወደ ፡ ካፒታል ፡ የሚለወጠው ፡ ትርፍ ፡ ዋጋ ፡ በጠ
ቅላላው ፡ የሚመሠርተው ፡ ተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ነው ፡
በማለት ፡ የነበራቸውን ፡ የተሳሳተ ፡ ሐሳብ ፡ አርሞታል ።

እንደዕውነቱ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ አንዱ ፡
ለምርት ፡ መሣሪያነት ፡ ሲውል ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡
በተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ያገለግላል ፡፡ ለካፒታሊዝም ፡
ዕድገት ፡ ሒደትና ፡ ብሎም ፡ ወደ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ለሚያ
ደርገው ፡ ለውጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ተፅዕኖ ፡ የሚኖረ
ው (ከጠቅላላው ፡ ካፒታል) የቋሚው ፡ ካፒታል ፡ ድርሻ ፡
ዕድገቱ ፡ ከተለዋዋጩ ፡ ካፒታል ፡ ድርሻ ፡ ጋር ፡ ሲመዛ
ዘን ፡ ፈጣን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡፡

የካፒታል ፡ ክምችት ፡ ሠራተኞችን ፡ በሥራ ፡ መሣሪ
ያ ፡ ማሽኖች ፡ በአጣዳፊ ፡ በመተካትና ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡
በጥቂቶች ፡ ዘንድ ፡ ሐብትን ፡ እያካበተ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡
ደግሞ ፡ የብዙዎችን ፡ መቆርቆዝ ፡ የሚያስከትል ፡ በመሆኑ
«ተጠባባቂ ፡ የሙያ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት» ተብሎ ፡ የሚጠ
ራውን ፡ በልዩ ፡ልዩ ፡ መልክና ፡ ሁናቴ ፡ ካፒታል ፡ ምርት
ን ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ለማሳደግ ፡ እንዲችል ፡ የሚረዳ ፡
የሠራተኞች ፡ መትረፍረፍ ፡ ማለት ፡ የካፒታሊስት ፡
የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ይፈጥራል ፡፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ከባንክ ፡ የብ
ድር ፡ አገልግሎትና ፡ የምርት ፡ መሣሪያ ፡ በመሆን ፡ ከሚ
ከማቸው ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ በመጣመር ፡ የምርት ፡ መትረ
ፍረፍ ፡ ለሚያስከትለው ፡ ቀውስ ፡ ማስረጃ ፡ ቁልፍ ፡ ነ
ው ፡፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የምርት ፡ መትረፍረፍ ፡ በካፒታሊ
ስት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡
በየአሥር ፡ ዓመቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ሲሆን ፡ በኋላ
ም ፡ በአልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ቆይቷል ፡፡ በካፒታሊ
ዝም ፡ ሥርዓት ፡ ሥር ፡ ከካፒታል ፡ ክምችት ፡ ጥንታዊ ፡
ክምችት ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ መለየት ፡ አለብን ፤
የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ክምችት ፡ የተኪያሒደው ፡ የሥራ ፡ መሣ
ሪያዎችን ፡ ከሠራተኛው ፡ በመንጠቅ ፤ ገበሬዎችን ፡ ከእ
ርሻ ፡ በማባረር ፡ የጋራ ፡ ርስትን ፡ አጭበርብሮ ፡ በመው
ሰድ ፤ በቅኝ ፡ አገዛዝና ፡ አንድን ፡ ሀገር ፡ የብድር ፡ ባለዕ
ዳ ፡ በማድረግ ፤ የጥቅም ፡ ታሪፍ ፡ በመደንገግና ፡ በመሳሰ



ሉት ፡ መንገዶች ፡ ነው ፡፡ «ጥንታዊ ፡ የካፒታል ፡ ክምች
ት» በአንድ ፡ ጫፍ «ነፃ» ወዝ ፡ አደር ፡ ሲፈጥር ፡ በሌላ ፡
ጫፍ ፡ ደግሞ ፡ ባለገንዘቡን ፡ ካፒታሊስት ፡ ይፈጥራል ፡፡

«የካፒታሊስት ፡ የገንዘብ ፡ ክምችት ፡ ታሪካዊ ፡ ዝንባሌ»
እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ማርክስ ፡ በሚከተሉት ፡ ቃላት ፡
ይገልጻል ፤ «የመሠረታዊው ፡ የምርት ፡ አምራቹ ፡ ንብረት ፡
የተነጠቀው ፡ ሀፍረተ ፡ ቢስ ፡ ወራዳ ፡ ቅሌታም ፡ በሆነና ፡
አረመኔነት ፡ በተመላበት ፡ ስግብግብ ፡ ውንብድና ፡ ነው ፡፡
በግለኛነት ፡ ለብቻው ፡ የሚሠራው ፡ የሥራ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡
ግለሰብ ፡ ከሙያው ፡ ጋር ፡ በመዋሀድ ፡ በድካሙ ፡ ያፈራ
ው ፡ የግል ፡ ንብረቱ (ገበሬውና ፡ ባለእጁ) «ለይስሙላ ፡
ነፃ ፡ ሙያ ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ የሌሎችን ፡ ጉልበት ፡
በመበዝበዝ ፡ በተመረኰዘው ፡ በካፒታሊዝም ፡ የግል ፡
ባለንብረትነት ፡ ይተካል … እዚህ ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ ንብረቱ
ን ፡ መነጠቅ ፡ የሚኖርበት ፡ ለራሱ ፡ የሚሠራው ፡ ሞያተ
ኛ ፡ ሳይሆን ፡ አያሌ ፡ ሞያተኞችን ፡ የሚበዘብዘው ፡ ካፒታ
ሊስት ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ የንብረት ፡ ንጥቂያ ፡ የሚፈጸመው ፡
ከፍተኛ ፡ ተፅዕኖ ፡ ባለው ፡ በካፒታሊስት ፡ የምርት ፡ ሕ
ግጋት ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ ማለት ፡ ካፒታል ፡ በአማክሎ ፡ ሲ
ሠራበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ አንድ ፡ ካፒታሊስት ፡ ሁልጊ
ዜም ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች ፡ ያጠፋል ፡፡ አያሌ ፡ ካፒታሊስ
ቶች ፡ በጥቂት ፡ ካፒታሊስቶች ፡ እየተዋጡና ፡ ንብረታ
ቸው ፡ እየተወረሰ ፡ ሲሔድ ፡ የሙያ ፡ ሒደት ፡ በኅብረት ፡
መልክ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ እየተስፋፋ ፡ ይሔዳል ፤ ሳይን
ስ ፡ በትክክል ፡ በቴክኒካዊ ፡ መንገድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይ
ውላል ፤ መሬት ፡ ሥርዓት ፡ ባለው ፡ ዕቅድ ፡ እንዲለማ ፡
ይደረጋል ፤ ሙያ ፡ ለጋራ ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ወደሚው
ል ፡ የሙያ ፡ መሣሪያነት ፡ ይለወጣል ፤ በተጣመረ ፡ ኅብረ
ተሰብዓዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የምርት ፡ መሣሪያዎችን ፡
በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ግልጋሎታቸው ፡ ይቆጠ
ባል ፤ እንዲሁም ፡ ሕዝቦች ፡ በሙሉ ፡ በዓለም ፡ ገብያ ፡

መረብ ፡ የተጠመዱ ፡ ይሆኑና ፡ የካፒታሊስቱ ፡ መንግ
ሥት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጠባይ ፡ ይይዛል ። የለውጥ ፡ ሒደ
ት ፡ የሚያስገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፡ እየነጠቁ ፡ ለራሳቸ
ው ፡ ግልጋሎት ፡ የሚያውሉት ፡ የካፒታል ፡ ባለንብረቶ
ች ፡ ብዛት ፡ እያነሰ ፡ በሔደ ፡ ቁጥር ፡ የሰፊው ፡ ሕዝብ ፡
ችግር ፡ መጨቆን ፡ ባርነት ፡ መዋረድና ፡ መበዝበዝ ፡ እ
የተስፋፋ ፡ ይሔዳል ። ይሁንና ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡ በ
ራሱ ፡ በካፒታሊስት ፡ ምርት ፡ ሒደት ፡ ሥርዓቱ ፡ ትብብ
ሩና ፡ ድርጅቱ ፡ እየተጠናከረ ፡ የሚሔደውና ፡ ቁጥሩ ፡ ባ
ለማቋረጥ ፡ የሚበራከተው ፡ የሠራተኛው ፡ መደብም ፡ አ
መጽ ፡ እየከረረ ፡ ይሔዳል ። የካፒታል ፡ በሞኖፖል ፡ መያ
ዣ ፡ ከእሱ ፡ ጋር ፡ በእሱ ፡ ሥር ፡ እየደረጀ ፡ ሲራመድ ፡
ለቆየው ፡ ሥልተ ፡ ምርት ፡ እንቅፋት ፡ ይሆናል ። በመጨረ
ሻም ፡ የምርት ፡ መሣሪያዎች ፡ በአማክሎ ፡ መወሰንና ፡
የሙያ ፡ በኅብረተሰብዓዊ ፡ መንገድ ፡ መኪያሔድ ፡ የውጭ ፡
መልካቸው ፡ ከነበረው ፡ ከሽፋናቸው ፡ ከካፒታሊዝም ፡
ጋር ፡ የሚጋጩበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይደርሳሉ ። ይህም ፡
ሽፋን ፡ በግጭቱ ፡ ግለት ፡ ይበጣጠሳል ። የካፒታሊዝምም ፡
የግል ፡ ባለንብረትነት ፡ ግብዓተ ፡ መሬት ፡ ደወል ፡ ያስተጋባ
ል» («ካፒታል» ቅጽ ፡ አንድ) ።

አንድ ፡ ሌላ ፡ አዲስና ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡
ነው ፡ የሚባለው ፡ የማርክስ ፡ ትምህርት ፡ ተጠቃሎ ፡ በአ
ንድነት ፡ ስለሚሠራው ፡ ማኅበራዊ ፡ ካፒታል ፡ መበራከ
ት ፡ በ «ካፒታል» ቅጽ ፡ ሁለት ፡ ያቀረበው ፡ ትንታኔ ፡
ነው ። እዚህም ፡ ላይ ፡ ማርክስ ፡ ያተኰረው ፡ ስለአንድ ፡
ተነጥላ ፡ ክስተት ፡ ሳይሆን ፡ ሁሉን ፡ አቀፍ ፡ ስለሆነ ፡
ክስተት ፡ ስለኅብረተሰብ ፡ ኤኮኖሚ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ብ
ቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስለጠቅላላው ፡ ኤኮኖሚ ፡ ነው ። ማርክስ ፡
ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የክላሲካል ፡ ኤኮኖሚስቶችን ፡
ስሕተት ፡ በማረም ፡ ማኅበራዊ ፡ ምርትን ፡ በሁለት ፡ ከ
ፍተኛ ፡ ክፍሎች ፡ ከፍሎታል ። አንደኛው ፡ የምርት ፡ መ



ሣሪያዎችን ፡ ማምረት ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ለ
ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ግልጋሎት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ማምረት ፡
ነው ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ማርክስ ፡ ብዙ ፡ ምሣሌዎችን ፡
በአስረጅነት ፡ በማቅረብ ፡ የጠቅላላውን ፡ የማኅበራዊ ፡
ካፒታልን ፡ ዝውውር ፡ በመጀመሪያ ፡ ይዞታውና ፡ በክም
ችት ፡ መልኩ ፡ እንዴት ፡ እንደሚበራከት ፡ መርምሯል ።
የ «ካፒታል» ቅጽ ፡ ሦስት ፡ የትርፍ ፡ መካከለኛ ፡ መጠን ፡
እንዴት ፡ በዋጋ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደሚፈጠር ፡ ያሳያ
ል ። በማርክስ ፡ ጥረት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሳይንስ ፡ ያደረገው ፡
ከፍተኛ ፡ እርምጃ ፡ ሊገኝ ፡ የቻለው ፡ ማርክስ ፡ የማኅበራ
ዊ ፡ ኤኮኖሚን ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ስድ ፡ የፖለቲካ ፡
ኤኮኖሚና «theory of marginal utility» በተነጣጣይ ፡ ሁና
ቴዎችና ፡ ለመታየትና ፡ ለይስሙላ ፡ በሚነገረው ፡ ፋክ
ክር ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ መልክ ፡ ሳይሆን ፡ በአጠ
ቃላይና ፡ በሰፊው ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ማርክስ ፡ በመጀመሪ
ያ ፡ የትርፍ ፡ ዋጋን ፡ አመጣጥ ፡ ከተነተነ ፡ በኋላ ፡ በትር
ፍ ፡ በወለድና ፡ በመሬት ፡ ኪራይ ፡ እንዴት ፡ እንደተከፋፈ
ለ ፡ ደግሞ ፡ ይመለከታል ። ትርፍ ፡ ማለት ፡ በትርፍ ፡ ዋጋ
ና ፡ በአንድ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ለሥራ ፡ በወጣው ፡ ካፒታ
ል ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የመጠን ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። ከሶ
ሺያል ፡ አቨሬጅ ፡ በላይ ፡ በተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ላይ ፡
ቋሚው ፡ ካፒታል ፡ ከፍተኛ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ካፒታል ፡
ማለት «high organic composition» ያለው ፡ ካፒታል ፡ የሚ
ያስገኘው ፡ ትርፍ ፡ ከመካከለኛው ፡ መጠን ፡ ያነሰ ፡
ነው ። «Low organic composition» ያለው ፡ ካፒታል ፡ ደ
ግሞ ፡ የሚያስገኘው ፡ ትርፍ ፡ ከመካከለኛው ፡ መጠን ፡
በላይ ፡ ነው ። በካፒታል ፡ መካከል ፡ የሚኪያሔደው ፡ ፉ
ክክርና ፡ ካፒታላቸውን ፡ ከአንድ ፡ የሥራ ፡ ቅርንጫፍ ፡
ወደ ፡ ሌላ ፡ ለማዛወር ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ የሚገኘውን ፡
ትርፍ ፡ በመካከለኛ ፡ መጠን ፡ ያስቀረዋል ። በአንድ ፡ ሕ
ብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ሸቀጦች ፡ ዋጋ ፡ ጠቅላላ ፡

ድምር ፡ ከመሸጫ ፡ ዋጋቸው ፡ ጠቅላላ ፡ ዋጋ ፡ ጋር ፡ እኩ
ል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንዳንድ ፡ ድርጅቶችና ፡
ምርት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ውስጥ ፡ በፉክክር ፡ የተነሳ ፡
ሸቀጦች ፡ የሚሸጡት ፡ በዋጋቸው ፡ ሳይሆን ፡ እነሱን ፡
ለማምረት ፡ በወጣው ፡ ሒሳብ ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ ማለት ፡
ለሥራው ፡ በተመደበው ፡ ካፒታል ፡ ላይ ፡ መካከለኛ ፡
መጠን ፡ ያለው ፡ ትርፍ ፡ ታክሎበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

በዚህ ፡ መንገድ ፡ ማርክስ ፡ የታወቀውንና ፡ የማያከ
ራክረውን ፡ በሸቀጦች ፡ የመሸጫ ፡ ዋጋና ፡ በመሠረታዊ ፡
ዋጋቸው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነትና ፡ የትርፍን ፡ አ
መጣጥ ፡ የዋጋን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አብራር
ቷል ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ የሸቀጦች ፡ ጠቅላላ ፡
ዋጋቸው ፡ ከመሸጫ ፡ ዋጋቸው ፡ ጋር ፡ በመስተካከሉ ፡
ነው ። ይሁንና (የማኅበራዊ) ዋጋን (ከግለሰብ) የመሸጫ ፡
ዋጋ ፡ ጋር ፡ ማመጣጠን ፡ እንዲሁ ፡ በቀላሉና ፡ በቀጥታ
ው ፡ የሚፈጸም ፡ ሳይሆን ፡ እጅግ ፡ ውስብስብ ፡ በሆነ ፡ መ
ንገድ ፡ ነው ። በገብያ ፡ ብቻ ፡ የሚገናኙ ፡ የተለያዩ ፡ የሸቀ
ጥ ፡ አምራቾች ፡ ባሉበት ፡ ሕብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የዋጋ ፡
በሕግ ፡ መወሰን ፡ የጠቅላላውን ፡ ሕዝብ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑ
ሮ ፡ በመጠኑ ፡ የሚያሳይ ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ግለሰብ ፡
ግን ፡ በየበኩሉ ፡ የሚፈጽመው ፡ ጥረት ፡ ያካክሰዋል ።

የሙያን ፡ ምርት ፡ ብርካቴ ፡ ለማሳደግ ፡ ቋሚ ፡ ካፒታ
ል ፡ ከተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ ሲመጣጠን ፡ ከፍተ
ኛ ፡ ዕድገት ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። ትርፍ ፡ ዋጋ ፡
ግንኙነቱ ፡ ከተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ እንደመ
ሆኑ ፡ መጠን ፡ የትርፍ ፡ መጠን (የትርፍ ፡ ዋጋ ፡ የመጠን ፡
ግንኙነት ፡ ከተለዋዋጭ ፡ ካፒታል ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ሳይ
ሆን ፡ ከጠቅላላው ፡ ካፒታል ፡ ጋር) ለመውረድ ፡ ያዘነ
ብላል ። ማርክስ ፡ ስለዚህ ፡ ዝንባሌና ፡ ዝንባሌውን ፡ ስለ
ሚሸፍኑትና ፡ በአፀፋው ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ አንዳንድ ፡ ሁና
ቴዎች ፡ ሰፊ ፡ ዝርዝር ፡ ያለው ፡ ትንታኔ ፡ አቅርቧል ። በ



ከፍተኛ ፡ ወለድ ፡ ካፒታል ፡ ስለሚያበድሩ ፡ ስለንግድ ፡
ካፒታልና ፡ ስለገንዘብ ፡ ካፒታል ፡ ስለሚያብራሩ ፡ የ
«ካፒታልን» ቅጽ ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ ከመመልከታችን ፡
በፊት ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ክፍል ፡ ስለመሬት ፡ ኪራይ ፡ ቴዎ
ሪ ፡ ወደሚያወራው ፡ ክፍል ፡ ማለፍ ፡ ይኖርብናል ። የመ
ሬት ፡ ስፋት ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑና ፡ በካፒታሊስት ፡ አገሮች
ም ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ በግለሰቦች ፡ የግል ፡ ይዞታ ፡ ሥር ፡
በመገኘቱ ፡ የእርሻ ፡ ምርቶች ፡ የማምረቻ ፡ ዋጋ ፡ የሚወሰነው ፡
ለምነቱ ፡ በመካከለኛ ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝ ፡ መሬት ፡ ስሌት ፡
ሳይሆን ፡ ጠፍ ፡ በሆነ ፡ መሬትና ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ገ
ብያ ፡ የሚቀርብበትም ፡ ዋጋ ፡ የሚታየው ፡ መካከለኛ ፡
በሆነ ፡ ዓይነት ፡ ሳይሆን ፡ እጅግ ፡ አድካሚ ፡ በሆነው ፡ ዓ
ይነት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዋጋና ፡ በተሻለ ፡ መሬት ፡ ላይ (ወ
ይንም ፡ በደህናው ፡ ሁኔታ) በሚታሰብ ፡ ዋጋ ፡ መካከል ፡
ያለው ፡ ልዩነት ፡ ዲፈረንሽያል ፡ የመሬት ፡ ኪራይ ፡ ይፈ
ጥራል ። ይህን ፡ በሰፊው ፡ በመተንተንና ፡ በተለያዩ ፡ ማሣ
ዎች ፡ ለምነትና ፡ ጠፍነት ፡ የተነሳ ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡
ልዩ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ በሚወጣው ፡ ካፒታል ፡ ልዩነት ፡
የተነሳ ፡ እንዴት ፡ ሊፈጠር ፡ እንደሚችል ፡ በማሳየት ፡ ማ
ርክስ (በሮድቤርቱስ ፡ ላይ ፡ ያቀረበውን ፡ ጠቃሚ ፡ ነቀፌ
ታ ፡ የሚያስረዳውን «የትርፍ ፡ ዋጋን ፡ ቴዎሪዎች» ይመ
ልከቱ ፤)ዲፈረንሽያል ፡ የመሬት ፡ ኪራይ ፡ ሊኖር ፡ የሚች
ለው ፡ ከደህና ፡ መሬት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ወደ ፡ ጠፍ ፡ መሬት ፡
መሸጋገር ፡ ሲኖር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሪካርዶ ፡ የነበረ
ውን ፡ የተሳሳተ ፡ ግምት ፡ አርሞታል ። እንዲያውም (በእ
ርሻ ፡ ቴክኒኮች ፡ መሻሻል ፡ በከተሞች ፡ ዕድገትና ፡ በተ
መሳሳይ ፡ ሁናቴዎች) በተገላቢጦሽ ፡ መሸጋገር ፡ በመኖ
ሩ ፡ መሬት ፡ ከአንድ ፡ ደረጃ ፡ ወይንም ፡ መደብ ፡ ወደ ፡
ሌሎች ፡ ሊሸጋገር ፡ ይችላል ። የካፒታሊዝምን ፡ ጉድለ
ቶች ፡ በጠባብ ፡ መወሰንና ፡ የቅራኔዎችን ፡ መኖር ፡ በተፈ
ጥሮ ፡ ላይ ፡ የሚያመካኘው «law of diminishing returns»

የተባለው ፡ አጉል ፡ ቴዎሪ ፡ ፍጹም ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በማንኛውም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ቅርንጫፍና ፡ በጠቅላላ ፡ ብሔራዊ ፡ ኤኮኖሚ ፡ የሚኖረው ፡ የትርፍ ፡ ተመጣጣኝነት ፡ ሙሉ ፡ የፉክክር ፡ ነፃነትና ፡ የካፒታልን ፡ ከአንድ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቅርንጫፍ ፡ በነፃ ፡ መተላለፍ ፡ ያስከትላል ። ይሁንና ፡ የመሬት ፡ በግል ፡ ንብረትነት ፡ መያዝ ፡ ይህን ፡ ነፃ ፡ የካፒታል ፡ መተላለፍ ፡ የሚገታ ፡ ሞኖፖሊ ፡ ይፈጥራል ። በዚያ ፡ ሞኖፖሊ ፡ ምክንያት ፡ አነስተኛ ፡ ኦርጋኒክ ፡ ኮምፖዚሽን ፡ ያለው ፡ ካፒታልና ፡ ይህም ፡ በመሆኑ ፡ በግል ፡ ከፍተኛ ፡ ትርፍ ፡ የሚያገኙ ፡ የእርሻ ፡ ምርቶች ፡ የትርፍ ፡ መጠን ፡ በሚስተካከልበት ፡ በነፃው ፡ ሒደት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ። ባለመሬቱ ፡ ሞኖፖሊስት ፡ እንደመሆኑ ፡ ዋጋውን ፡ ከመካከለኛ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ያደርገዋል ። ይህም ፡ የሞኖፖሊ ፡ ዋጋ ፡ ለአብሰሉት ፡ ኪራይ ፡ ዕድገት ፡ ይሰጠዋል ። ዲፈረንሽያል ፡ ኪራይ ፡ በካፒታሊዝም ፡ ሥርዓት ፡ ሊወገድ ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ አብሰሉት ፡ ኪራይ ፡ ግን ፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ መሬትን ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ንብረትነት ፡ በማዛወር ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በማድረግ ፡ የግል ፡ ባለመሬቶችን ፡ ሞኖፖሊ ፡ ለማዳከምና ፡ በርሻ ፡ ረገድ ፡ ጽኑና ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ ፉክክር ፡ መመሥረት ፡ ይቻላል ። ማርክስ ፡ እንደሚለው ፡ የቡርዥዋ ፡ ተስፈንጣሪዎች ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ተራማጅ ፡ የሆነ ፡ ሀሳብ ፡ ማለት ፡ መሬት ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ እንዲሆን ፡ በየጊዜው ፡ ጠይቀዋል ። ይሁንና ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ አብዛኞቹን ፡ ቡርዥዋዎች ፡ ሥጋት ፡ ይለቅባቸዋል ። ምክንያቱም ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠውን ፡ ና ፡ አሳሳቢ ፡ የሆነውን ፡ ሌላ ፡ ሞኖፖሊ ፡ ማለት ፡ የምርት ፡ መገልገያዎችን ፡ ሞኖፖሊ ፡ በቅርብ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። (ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1862 ዓ. ም. ነሐሴ ፡ 2 ቀን ፡ ለኤንግልስ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ በካፒታልና ፡ በአብሰሉት ፡ የመሬት ፡



ኪራይ ፡ ስለሚገኘው ፡ መካከለኛ ፡ ትርፍ ፡ የራሱን ፡ ቴዎሪ ፡ በማስረዳት ፡ የሚያረካ ፡ ለሁሉም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አጭርና ፡ በጉልህ ፡ የሚያስረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ አቅርቧል ። «ለኤንግልስ ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎች» ይመልከቱ ፡ ቅጽ ፣ ሦስት ፤ ገጾች ፡ ከ 77-81 ። እንዲሁም ፡ እ. ኤ. አ. በ 1862 ዓ. ም. ነሐሴ ፡ 9 የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ገጾች ፣ 86-87) ። የመሬትን ፡ ኪራይ ፡ ታሪክ ፡ በሚመለከተውም ፡ ረገድ ፡ የሙያ ፡ ኪራይ (ገበሬው ፡ በባለ ፡ መሬቱ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ እየሠራ ፡ ትርፍ ፡ ምርት ፡ ያስገባል) ፤ ይህም ፡ እንዴት ፡ በምርት ፡ ወይንም ፡ በዓይነት ፡ ወደሚከፈል ፣ ኪራይ ፡ እንደሚለወጥ (ገበሬው ፡ በራሱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እየሠራ ፡ ትርፍ ፡ በማምረት «ከኤኮኖሚ ፡ ውጭ ፡ ባለው ፡ ተፅዕኖ ፡ በመኖሩ ፡ ትርፉን ፡ ለባለመሬቱ ፡ ለባላባቱ ፡ ያስረክባል) ፤ ከዚያም ፡ ይሄው ፡ ኪራይ ፡ እንዴት ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ኪራይ ፡ እንደሚለወጥ (በዓይነት ፡ የሚከፈለው ፡ ኪራይ ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ይለወጣል ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ኪራይ ፡ በሩስያ «ኦብሮክ» ይባል ፡ ነበር ። የተመሠረተውም ፡ የሸቀጦች ፡ ምርት ፡ በማደጉ ፡ ነው) በመጨረሻም ፡ በቅጥር ፡ ሞያተኞች ፡ መሬቱን ፡ የሚያለማ ፡ ድርጅት ፡ ያለው ፡ ባለእርሻ ፡ ገበሬውን ፡ በሚተካበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ካፒታሊስት ፡ ኪራይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚለወጥ ፡ የሚያሳየውን ፡ የማርክስን ፡ ትንተና ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ። «የካፒታሊስትን ፡ የመሬት ፡ ኪራይ ፡ አመጣጥ ፡ ሥረ ፡ መሠረት ፡ የሚያስረዳውን» ትንተና ፡ ስንመለከት ፡ የካፒታሊዝም ፡ አዝጋሚ ፡ ለውጥ ፡ በእርሻ ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ማርክስ ፡ ካቀረባቸው ፡ ሐሳቦች (በተለይም ፡ እንደሩስያ ፡ ስለአሉት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ስለቀሩት ፡ አገሮች ፡ የተገለጹትን ፡ ሐሳቦች) እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ አንዳንድ ፡ ሐሳቦች ፡ ማገናዘብ ፡ ያስፈልጋል ። በዓይነት ፡ ይከፈል ፡ የነበረው ፡ ኪራይ ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ኪራይ ፡ ሲለወጥ ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ የሌላቸው ፡ በገንዘብ ፡ እየተቀጠሩ ፡ የሚሠሩ ፡ የቀን ፡ ሞያ

ተኞች ፡ መደብ ፡ የሚፈጠር ፡ መሆኑ ፡ የማይቀርና ፡ የሚጠበቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ አዲስ ፡ መደብ ፡ ሲፈጠር ፡ ገና ፡ በጭቅላነቱ ፡ ኪራይ ፡ እየከፈሉ ፡ በሚኖሩት ፡ በበለፀጉት ፡ ገበሬዎች ፡ ዘንድ ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ ተቀጥረው ፡ የሚሠሩትን ፡ የቀን ፡ ሞያተኞች ፡ የመበዝበዝ ፡ ባሕል ፡ ይመሠረታል ። በፊውዳሉም ፡ ዘመን ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ባሕል ፡ ነበረ ። ይኸውም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የበለፀጉት ፡ ገባሮች ፡ እነሱም ፡ በበኩላቸው ፡ ገባር ፡ የነበራቸው ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መንገድ ፡ ማለት ፡ የቀን ፡ ሞያተኞውን ፡ ገበሬ ፡ በመበዝበዝ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ሐብት ፡ በማካበት ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ካፒታሊስት ፡ ይለውጣሉ ። በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ የመሬት ፡ ባለቤት ፡ የሆኑት ፡ የጥንቶቹ ፡ ባለርስቶች ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ከገጠር ፡ አልፎ ፡ በተስፋፋው ፡ ከካፒታሊስት ፡ ምርት ፡ ዕድገት ፡ ጋር ፡ ዕድገታቸው ፡ አብሮ ፡ የሚራመድ ፡ የካፒታሊስት ፡ ጭሰኞች ፡ የሚበራከቱበት ፡ ሁናቴ ፡ ይፈጥራሉ ።» («ካፒታል» ቅጽ ፡ ሦስት ፡ ገጽ ፡ 332) «በእርሻ ፡ ይኖር ፡ ከነበረው ፡ ሕዝብ ፡ በከፊል ፡ እርሻው ፡ የተወሰደ ፡ መሆኑና ፡ ከዚሁ ፡ ኑሮው ፡ መወገዱ ፡ የቀን ፡ ሞያተኞችንና ፡ የኑሮ ፡ መገልገያቸውን ፡ እንዲሁም ፡ የሙያ ፡ መሣሪያዎቻቸውን ፤ ለኢንዱስትሪ ፡ ካፒታል ፡ አገልግሎት ፡ ከማዋሉም ፡ በላይ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገብያ ፡ ከፍቷል» («ካፒታል» ፤ ቅጽ ፡ አንድ ፤ ገጽ ፡ 778) ። የገጠሩ ፡ ሕዝብ ፡ መደህየቱና ፡ በኑሮ ፡ መራቆቱ ፡ ሥራ ፡ የፈታ ፡ የሙያ ፡ ሠራዊት ፡ ክምችት ፡ በመፍጠር ፡ ለካፒታል ፡ መገንባት ፡ ሌላ ፡ ምንጭ ፡ ሆኖአል ። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ የካፒታሊስት ፡ አገር «በእርሻ ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ በከፊል ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ማለት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ወደተስፋፋበት (እርሻ ፡ ወደሌለበት) በየጊዜው ፡ በመዛወር ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ... ይህ ፡ የሠራተኞች ፡ መትረፍረፍ (ሬላቲቭ ፡ ሰርፕላስ) ምንጭ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይጐር



ፉል ። የእርሻ ፡ ሞያተኛው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ በምፅዋት ፡ ኑሮ ፡ አዘቅት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ እግሩ ፡ ተውጦ ፡ እጅግ ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ እየተከፈለው ፡ ኑሮውን ፡ ይገፉል» («ካፒታል» ፤ ቅጽ ፡ አንድ ፤ ገጽ ፡ 668) ። ገበሬው ፡ የሚያርሰው ፡ መሬት ፡ ባለንብረት ፡ መሆኑ ፡ ለዝቅተኛ ፡ ምርት ፡ መሠረት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለገበሬው ፡ ብልጽግናና ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ አቋም ፡ መሸጋገሪያ ፡ ይሆነዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ዝቅተኛ ፡ አመራረት ፡ ሥፍራ ፡ የሚኖረውና ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆነው ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ ፡ አመራረትና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በካፒታሊዝም ፡ ሥርዓት ፡ ሥር «በገበሬው ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ብዝበዛ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ውስጥ ፡ በሚሠራው ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ላይ ፡ ከሚፈጸመው ፡ ብዝበዛ ፡ የሚለየው ፡ በመልኩ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በሁለቱም ፡ ዘንድ ፡ በዝባዡ ፡ ያው ፡ ካፒታል ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ካፒታሊስት ፡ እያንዳንዱን ፡ ገበሬ ፡ የሚበዘብዘው ፡ በአራጣና ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ሲሆን ፡ የካፒታሊስቱ ፡ መደብ ፡ ደግሞ ፡ የገበሬውን ፡ መደብ ፡ የሚበዘብዘው ፡ በመንግሥት ፡ ቀረጥ ፡ ነው» («የፈረንሳይ ፡ የመደብ ፡ ትግል») «ገበሬው ፡ ያለው ፡ ጥቂት ፡ ይዞታ ፡ ካፒታሊስቱ ፡ ትርፍ ፡ ወለድና ፡ ኪራይ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆነው ፡ ገበሬው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ ጉልበቱን ፡ በሌላ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ይኖርበታል» («አሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ብሩሜር») ። የግል ፡ ባለንብረት ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ገበሬው «እንደ ፡ አየርላንድ ፡ ጭሰኛ ፡ ገበሬ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ» ለካፒታሊስቱ ፡ መደብ ፡ የድካም ፡ ዋጋውን ፡ በከፊል ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል («የፈረንሳይ ፡ የመደብ ፡ ትግል») ። የዝቅተኛ ፡ ገበሬዎች ፡ የመሬት ፡ ባለንብረትነት ፡ በአየለበት ፡ አገር ፡ የእህል ፡ ዋጋ ፡ በካፒታሊስት ፡ ሥልተ ፡ ምርት ፡ ከሚተዳደር ፡ አገር ፡ የ

እህል ፡ ዋጋ ፡ ካነሰባቸው ፡ ምክንያቶች ፡ አንደኛው ፡ ምን
ድን ፡ ነው? («ካፒታል» ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 340) ምክንያ
ቱም ፡ ገበሬው ፡ ለኅብረተሰቡ (ማለት ፡ ለካፒታሊስቱ ፡
መደብ) በትርፍ ፡ ከሚያፈራው ፡ ምርት ፡ ከፊሉን ፡ በነፃ ፡
ስለሚያስረክብ ፡ ነው ። «ይህ ፡ ዝቅተኛ ፡ የእህልና ፡ የሌሎ
ች ፡ የእርሻ ፡ ምርቶች ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ሊኖር ፡ የቻለ
ው ፡ የአምራቾቹ ፡ ድህነት ፡ ምክንያት ፡ እንጂ ፡ በሞያቸ
ው ፡ ምርት ፡ ፍሪያማነት ፡ አይደለም ።» («ካፒታል» ፤
ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 340) ። በካፒታሊዝም ፡ ሥርዓት ፡
ሥር ፡ የዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ አመራረት ፡ መደበኛው ፡ መልክ ፡
ማለት ፡ ለአነስተኛ ፡ ይዞታ ፡ ሥርዓት ፡ እየተዳከመና ፡ እ
የፈረሰ ፡ በመሔድ ፡ በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ይጠፋል ። «በአን
ድ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረው ፡ የመሬቶች ፡ ባለን
ብረትነት ፡ በጠባዩ ፡ የኅብረተሰብን ፡ የምርት ፡ ኃይሎች ፡
ዕድገት ፤ የኅብረተሰብን ፡ የሙያ ፡ ዓይነቶች ፡ የኅብረተሰ
ብን ፡ የካፒታል ፡ ክምችት ፤ ሰፊ ፡ የከብት ፡ ርቢንና ፡ የሳ
ይንስን ፡ አገልግሎት ፡ የሚያደናቅፍ ፡ ነው ። የአራጣና ፡
የግብር ፡ ሥርዓት ፡ ኅብረተሰቡን ፡ ያደኸየዋል ። ለመሬ
ት ፡ ኪራይ ፡ የሚወጣው ፡ ካፒታል ፡ ለልማት ፡ የሚያስ
ፈልገውን ፡ ካፒታል ፡ ያራቁተዋል ። የምርት ፡ መገልገ
ያዎች ፡ መበታተንና ፡ የራሳቸው ፡ የአምራቾቹ ፡ መነጣጠ
ል» (የኰኦፐራቲቭ ፡ ማኅበሮች ፡ ማለት ፡ ትናንሽ ፡ የገበ
ሬዎች ፡ ማኅበሮች ፡ እጅግ ፡ ተራማጅ ፡ የሆነ ፡ የቡርዥዋ ፡
ሚና ፡ እየተጫወቱ ፡ ይህንኑ ፡ ዝንባሌ ፡ ባያስወግዱትም ፡
ያዳክሙታል ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ እነዚህ ፡ የኰኦፐ
ራቲቭ ፡ ማኅበሮች ፡ ለበለጸጉት ፡ ገበሬዎች ፡ ብዙ ፡ ሲያ
በረክቱ ፡ ለሰፊውና ፡ ለድሀው ፡ ገበሬ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አ
ያደርጉለትም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ቢያደርጉለትም ፡ እ
ጅግ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የገበሬዎች ፡ ማኅበ
ሮች ፡ እራሳቸው ፡ የቅጥር ፡ ሞያ ፡ በዝባገሮች ፡ ይሆናሉ ።)
«አያሌ ፡ የሰው ፡ ጉልበት ፡ ይባክናል ። «ምርት ፡ የማምረ



ት ፡ ሁናቴዎች ፡ መጃጃልና ፡ የምርት ፡ መገልገያዎች ፡ ዋ
ጋ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ አይቀርም ፡ ተብሎ ፡ የሚጠበቅ ፡ የሐብ
ት ፡ ምንጮች ፡ የግል ፡ ባለንብረትነት ፡ ደንብ ፡ ናቸው ።»
በኢንዱስትሪ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ካፒታሊዝም ፡
በእርሻም ፡ በኩል ፡ የምርት ፡ ሒደትን ፡ የሚቀይረው «በ
አምራቾቹ ፡ መስዋዕትነት ፡ ነው ።» «በገጠር ፡ የሚሠሩ ፡
ሞያተኞች ፡ በሰፊ ፡ ሥፍራዎች ፡ መበታተን ፡ የሚመጣ
ባቸውን ፡ ለመቋቋም ፡ ያላቸውን ፡ ኃይል ፡ ሲቀንሰው ፡
በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መከማቸታቸው ፡ ደግሞ ፡ ያጠናክራ
ቸዋል ። በከተማ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡
እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ በዘመናዊ ፡ እርሻም ፡ በምርቱና ፡
በቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የሞያ ፡ ጥራት ፡ የሚገኘው ፡
የሞያ ፡ ኃይልን ፡ እራሱን ፡ በማዳከምና ፡ በመበዝበዝ ፡
ነው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በካፒታሊስት ፡ እርሻ ፡ በኩል ፡
የሚከናወነው ፡ እርምጃ ፡ ሞያተኛውን ፡ በመግፈፍ ፡ ጥበ
ብ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ መሬቱንም ፡ በማራቆት ፡ ጭ
ምር ፡ ነው … ስለዚህ ፡ የካፒታሊስት ፡ አመራረት ፡ ቴክ
ኒዮሎጂን ፡ የሚያሳድገውና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሒደቶችን ፡ ወ
ደ ፡ አንድ ፡ የማኅበራዊ ፡ አካል ፡ የሚያጠቃልለው ፡ የጠ
ቅላላ ፡ ሐብትን ፡ መሠረተ ፡ ምንጮች ፡ ማለት ፡ አፈሩን
ና ፡ ሞያተኛውን ፡ በማሟጠጥ ፡ ብቻ ፡ ነው» («ካፒታል» ፤
ቅጽ ፡ አንድ ፤ የምዕራፍ ፡ 13 መጨረሻ ።)

## ሶሺያሊዝም ።

የካፒታሊስት ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉና ፤
በተለይ ፡ ከዘመናዊው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፡ የኤኮ
ኖሚ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኅብረተሰብዓዊነት ፡ ሊለወጥ ፡ እንደ
ሚችል ፡ ማርክስ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ከተገለጸው ፡ ሁናቴ ፡
የተረዳው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ማርክስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለ
ም ፡ በሞት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ባለፉት ፡ አምሳ ፡ ዓመታት ፡

ውስጥ ፡ ከፍተኛና ፡ ሰፊ ፡ የምርት ፡ አቀራረብ ፡ የካፒታሊስት ፡ ካርቴልስ ፡ ሲንዲካቶችና ፡ ትረስቶች ፡ የተበራከቱ ፡ በመሆናቸውና ፡ የገንዘብ ፡ ካፒታልም ፡ መስመሩና ፡ አቋሙ ፡ እየተጠናከረ ፡ በመሔዱ ፡ የሙያ ፡ በማኅበራዊ ፡ መንገድ ፡ መኪያሔድ ፡ መስፋፋቱና ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ መበራከቱ ፡ ለሶሺያሊዝም ፡ ሥርዓት ፡ መምጣት ፡ ዋናውን ፡ የማቴሪያል ፡ መሠረት ፡ ይጥላል ። ለዚህ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሥርዓት ፡ ለውጥ ፡ ምሑሩና ፡ የሞራል ፡ ግብ ፡ ኀይሉ ፡ እንዲሁም ፡ አድራጊ ፡ ፈጣሪው ፡ ካፒታሊዝም ፡ ያሠለጠነው ፡ ወዝ ፡ አደሩ ፡ ነው ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ በይዘቱ ፡ አብሮ ፡ የሚታየው ፡ ወዝ ፡ አደሩ ፡ ከቡርዥዋው ፡ ጋር ፡ የሚያደርገው ፡ ትግል ፡ በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ወዝ ፡ አደሩ ፡ የፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ ለመጨበጥ ፡ የሚያደርገው ፡ የፖለቲካ ፡ ትግል ፡ ይሆናል ። («የወዝ ፡ አደሩ ፡ አምባ ፡ ገነንነት») ምርትን ፡ በማኅበራዊ ፡ ሥርዓት ፡ ማኪያሔድ ፡ የማምረቻ ፡ መሣሪያዎች ፡ የኅብረተሰቡ ፡ ንብረት ፡ እንዲሆኑና «የነጣቂዎች ፡ ንብረት ፡ እንዲነጠቅ» ያደርጋል ። ለውጡ ፡ በሙያ ፡ ምርት ፡ ብርካቴ ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድገት ፡ ከማስገኘቱም ፡ በላይ ፡ የሥራ ፡ ቀንን ፡ ያሳጥራል ፤ እንዲሁም ፡ ያለፈውን ፡ ሥርዓት ፡ የተበታተኑ ፡ የምርት ፡ ድርጅቶች ፡ ፍርስራሾችና ፡ ርዝራዦች ፡ በተሻሻለና ፡ በጋርዮሽ ፡ ማለት ፡ በማኅበር ፡ በሚኪያሔዱ ፡ ድርጅቶች ፡ ይተካቸዋል ። ካፒታሊዝም ፡ ለዘለዓለም ፡ ማለት ፡ ይቻላል ፡ በግብርናና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ግንኙነት ፡ ያፈርሳል ፤ ይሁንና ፡ በሚያኪያሒደው ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድገት ፡ ሳይንሳዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድና ፡ ማኅበራዊ ፡ ሙያን ፡ በአጠቃላይ ፡ በማጠናከርና ፡ እንዲሁም ፡ የሕዝብን ፡ መኖሪያ ፡ እንደገና ፡ በመለዋወጥ ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ ሁኔታ ፡ በግብርናና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ መካከል ፡ ለነበረው ፡ ግንኙነት ፡ አዲስ ፡ ዘርፎች ፡ ይከፍታል ። (በዚህም ፡ አኳኋን ፡ በገጠር ፡ የነበረውን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መቅረት ፡



ግለኝነትና ፡ መኃይምነት ፡ በመደምሰስ ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ የነበረውን ፡ የሕዝብ ፡ መጣበብ ፡ ያስወግዳል ።) በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ የካፒታሊዝም ፡ የኑሮ ፡ አመራር ፡ ሥርዓት ፡ አዲስ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ሁኔታ ፤ አዲስ ፡ የሴቶች ፡ አቋምና ፡ በወጣቱ ፡ ትውልድ ፡ አስተዳደግ ፡ አዲስ ፡ ሁኔታዎች ፡ ይመሠረታሉ ። በዘመናዊው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ካፒታሊዝም ፡ የሴቶችንና ፡ የሕፃናትን ፡ ጉልበት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ እንዲሁም ፡ በቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የወንድን ፡ የበላይነት ፡ በመደምሰስ ፡ የሚፈጽመው ፡ ዘዴ ፡ አሰቃቂ ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥና ፡ የሚቀፍ ፡ ነው ። ይሁንና «ዘመናዊ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በማኅበራዊ ፡ መንገድ ፡ በተዘጋጀው ፡ የምርት ፡ ሒደት ፡ ውስጥ ፡ ከቤት ፡ ጣጣ ፡ ውጭ ፡ ለሴቶችና ፡ ለወጣቶች ፤ ለሁለቱም ፡ ጾታ ፡ ሕፃናቶች ፡ ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡ በመመደብ ፡ ለቤተሰብ ፡ ይዞታና ፡ በሁለቱ ፡ ጾታዎች ፡ መካከል ፡ ላሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የተሻለ ፡ አቋም ፡ አዲስ ፡ የኤኮኖሚ ፡ መሠረት ፡ ይጥላል ። በጀርመን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ የነበረውንም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ እንደትክክለኛና ፡ የተሟላ ፡ አድርጎ ፡ መቁጠርም ፤ የጥንት ፡ ሮማዊያን ፤ ግሪካዊያንና ፡ የምሥራቅ ፡ ሕዝቦችም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ ፍጹምነት ፡ የነበረው ፡ ነው ፡ እንደማለት ፡ ስለሚቆጠር ፡ ስሕተት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የቤተሰብ ፡ ቅርጾች ፡ አንድ ፡ የእድገት ፡ ታሪካዊ ፡ መሥመር ፡ ይመሠርታሉ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በግብታዊ ፡ ሁኔታ ፡ በተመሠረተው ፡ በጨካኝ ፡ የካፒታሊስት ፡ መልኩ ፡ ሞያተኛው ፡ የሚኖረው ፡ ለምርት ፡ ሒደት ፡ እንጂ ፡ የምርት ፡ ሒደት ፡ የሚኖረው ፡ ለሞያተኛው ፡ መኖር ፡ ባይሆንምና ፡ ጠቅላላው ፡ የሥርዓቱ ፡ መዋቅር ፡ የተበላሸና ፡ ሌላውን ፡ በባርነት ፡ ለመግዛት ፡ ባተኰረ ፡ ዓላማ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ቢሆንም ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ የተሠማራው ፡ ክፍል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕድሜ ፡ ካላቸው ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ የተውጣጣ ፡ በመሆኑ ፡ አጋጣሚ ፡ ሲ

ፈጠር ፡ የሰብዓዊ ፡ ተግባር ፡ ማመንጫ ፡ ይሆናል» («ካ
ፒታል» ፤ ቅጽ ፡ አንድ ፤ ምዕራፍ ፡ 13 መጨረሻ) ። በፋ
ብሪካዎች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሥርዓት «ለወደፊቱ ፡ ትምህ
ርት ፡ የሚያስፈልገው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሕዋስ ፡ ይገኝ
በታል ። ይህ ፡ ትምህርት ፡ ከተወሰነ ፡ ዕድሜ ፡ በላይ ፡ ላ
ሉ ፡ ልጆች ፡ ፍሪያማ ፡ ሙያን ፡ ከትምህርትና ፡ ከሰውነት ፡
ማጠንከሪያ ፡ ጋር ፡ በማጣመር ፡ ለማኅበራዊ ፡ ምርት ፡ ተ
ጨማሪ ፡ ጥንካሬ ፡ ከመስጠቱም ፡ በላይ ፡ የተሟላ ፡ ዕውቀ
ት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለማፍራት ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ እሱ ፡ ብ
ቻ ፡ ነው ።» (ከላይ ፡ ከተጠቀሰው) ። የማርክስ ፡ ሶሺያሊ
ዝም ፡ የብሔርንና ፡ የመንግሥትን ፡ ጉዳዮች ፡ በታሪክ ፡
አመጣጥ ፡ በአንድ ፡ ደረጃ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ያለፈውን ፡
ለመግለጽና ፡ ለማብራራት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የወደፊቱን ፡
በትክክል ፡ ለመተንበይና ፡ ለፍጻሜውም ፡ ትክክለኛ ፡ ተግ
ባራዊ ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ ጭምር ፡ ነው ። ብሔሮች ፡
በቡርዡዋ ፡ የዕድገት ፡ ዘመን ፡ የማይቀሩ ፡ የታሪክ ፡ ው
ጤቶች ፡ ናቸው ። የሠራተኛው ፡ መደብ «በብሔር ፡ ውስ
ጥ ፡ ራሱን ፡ ካላደራጀ» ሊጠነክርና ፡ በአድራጎቱም ፡ የበ
ሰለ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ ይህም ፡ ማለት (እንደ ፡ ቡርዡ
ዋዎች ፡ አባባል ፡ ሳይሆን) ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ሊኖረው ፡
ይገባል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁንና ፡ የካፒታሊዝም ፡ ዕድገ
ት ፡ በብሔሮች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ልዩነቶች ፡ አስወግ
ዶ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠሩትን ፡ ብቸኝነቶች ፡ በ
መደምሰስ ፡ በብሔር ፡ ግጭቶች ፡ ፈንታ ፡ የመደብ ፡ ግጭ
ቶችን ፡ ይፈጥራል ። ስለዚህ ፡ በበለፀጉ ፡ የካፒታሊስት ፡
አገሮች ፡ ውስጥ «ሠራተኛ ፡ ሰው ፡ አገር ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡
የማያጠራጥር ፡ ነው» ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ የሰለጠኑት ፡ አገ
ሮች ፡ ሠራተኞች «በኅብረት ፡ የሚወሰዱት ፡ እርምጃ»
በወዝ ፡ አደሩ ፡ ነፃነት ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ የመጀመሪያ ፡
ሁናቴዎች ፡ አንዱ ፡ ነው» («የኮሙኒስት ፡ ፓርቲ ፡ ማኒፌ
ስቶ») ። መንግሥት ፡ የተደራጀ ፤ በኃይል ፡ የሚመራ ፤



የማስገደጃ ፡ መሣሪያ ፡ ሲሆን ፡ የተፈጠረውም ፡ የኅብረተ
ሰብ ፡ ዕድገት ፡ ከአንድ ፡ የተወሰነ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ማለት ፡
ኅብረተሰቡ ፡ በማይታረቁ ፡ መደቦች ፡ ተከፋፍሎ ፡ ከኅብረ
ተሰቡ ፡ በላይና ፡ ከሱም ፡ ተለይቶ ፡ የተደራጀ «ባለሥል
ጣን ፡ ኃይል» ካልኖረ ፡ በስተቀር ፡ ተስማምተው ፡ ለመኖር ፡
ካልቻሉበት ፡ ደረጃ ፡ በደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። መንግ
ሥት ፡ በመደቦች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ቅራኔ ፡ ምክንያት ፡
ተፈጥሮ «በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ኃይለኛ ፡
የሆነው ፡ መደብ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ መደብ ፡
በመንግሥቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ክፍሎች ፡ አማካኝ
ነት ፡ የፖለቲካም ፡ ተፅዕኖና ፡ የበላይነት ፡ የሚኖረው ፡ በ
መሆኑ ፡ የተጨቆነውን ፡ መደብ ፡ ለመጫንና ፡ ለመበዝ
በዝ ፡ የሚያስችሉ ፡ አዲስ ፡ መሣሪያዎች ፡ ይኖሩታል ።
በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ መሆኑ ፡ ነው ፤ ጥንታዊው ፡ መንግሥት ፡
ባሪያዎችን ፡ ለመጨቆን ፡ የተመሠረተ ፡ የባሪያ ፡ ገዥዎች ፡
መንግሥት ፡ ሲሆን ፡ የፊውዳሉም ፡ መንግሥት ፡ ገባሮች
ን ፡ ለመጨቆን ፡ የተቋቋመ ፡ የመሣፍንቱ ፡ መሣሪያ ፡ እን
ደመሆኑ ፡ ሁሉ ፤ ዘመናዊውም ፡ የባለጊዜዎች ፡ ተወካይ ፡
መንግሥት ፡ የተቀጣሪውን ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ጉልበት ፡ ለማ
ስበዝበዝ ፡ የተቋቋመ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ።» (ይህ ፡ የተገለ
ጸው ፡ ኤንግልስ ፡ የራሱንና ፡ የማርክስን ፡ አስተያየቶች ፡
በማስፋፋት «የቤተ ፡ ሰብ ፤ የግል ፡ ንብረትና ፡ የመንግ
ሥት ፡ አመጣጥ» በተባለው ፡ ሥራው ፡ ውስጥ ፡ ባቀረበ
ው ፡ ሐሳብ ፡ ነው ።) ዴሞክራሲያዊ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ተብሎ ፡
የሚጠራው ፡ የተሻለ ፡ ነፃነት ፡ የሚገኝበትና ፡ ከሌሎቹ ፡
እጅግ ፡ ተራማጅ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ የቡርዡዋ ፡ መንግ
ሥት ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ሃቅ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ሊሠርዘው ፡
አይችልም ፤ የሚያደርገው ፡ ቢኖር (በመንግሥቱና ፡ በን
ግድ ፡ ድርጅቶች (stock exchange) መካከል ፡ ያሉ
ትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በቀጥታና ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ የሚኪያ
ሔዱትን ፡ የሥልጣን ፡ ብልግናዎችን ፡ እና ፡ የጋዜጦችን ፡

አቋም) በጠቅላላው ፡ የሁሉንም ፡ መልክ ፡ እንደጊዜው ፡ መለዋወጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሶሺያሊዝም ፡ መደቦችን ፡ ለማጥፋት ፡ ሲያመራ ፡ መንግሥትንም ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ያጠፋዋል ። ኤንግልስ ፡ «አንቲ ፡ ዱሪንግ» በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ሲጽፍ «መንግሥት ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ስም ፡ የምርት ፡ መሣሪያዎችን ፡ በመያዝ ፡ የሚፈጽመው ፡ የመጀመሪያው ፡ ተግባር ፡ እንደመንግሥትነቱ ፡ በነፃነት ፡ የሚፈጽመው ፡ የመጨረሻውም ፡ ተግባር ፡ ይሆናል ። መንግሥቱ ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ግንኙነቶች ፡ ውስጥ ፡ በየመስኩ ፡ የሚፈጽመውም ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ከልክ ፡ ያልፍና ፡ እራሱ ፡ ይቆማል ። መንግሥት ፡ ሰዎችን ፡ የሚያስተዳድር ፡ ድርጅት ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተቋሞችን ፡ በማስተዳደርና ፡ የምርት ፡ ሒደትን ፡ በመምራት ፡ ይተካል ። መንግሥት «አይደመሰስም» እራሱ ፡ ሟሽሾ ፡ ይጠፋል» ብሏል ። «ምርትን ፡ በእኩልነትና ፡ በነፃነት ፡ በተመሠረተ ፡ ማኅበር ፡ እንደገና ፡ የሚያደራጀው ፡ ኅብረተሰብ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥትን ፡ የሥራ ፡ ቁሳቁሶች ፡ በሙሉ ፡ አጠቃሎ ፡ ወደሚገባቸው ፡ ሥፍራ ፡ ጊዜ ፡ ወደአለፈባቸው ፡ እቃዎች ፡ ሙዚየም ፡ በማስገባት ፡ ከሌሎች ፡ ጥንታዊ ፡ ቁሳቁሶች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ይቀላቅላቸዋል» (ኤንግልስ ፤ «የቤተ ፡ ሰብ ፤ የግል ፡ ንብረትና ፡ የመንግሥት ፡ አመጣጥ») ።

በመጨረሻም ፡ የሌሎችን ፡ ንብረት ፡ የግላቸው ፡ አድርገው ፡ ይዘባነኑ ፡ የነበሩት ፡ ንብረታቸውን ፡ በሚነጠቁበትም ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስለማይቀረው ፡ ስለአነስተኛ ፡ ግብርና ፡ የማርክስ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ስለአለው ፡ አቋም ፡ የማርክስን ፡ አስተያየት ፡ የሚገልጸውን ፡ የኤንግልስን ፡ መግለጫ ፡ መመልከት ፡ ያስፈልገናል ። «የመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ በጨበጥንበት ፡ ጊዜ ፡ ታላላቆቹን ፡ ባለርስቶች ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ እንዳደረግነው ፡ ሁሉ ፡ አነስተኛ ፡ ገበሬዎችን (ካሳ ፡ ተሰጥቶ ፡ ሆነ ፡ ሳይሰጥ) ንብረታቸውን ፡



በኃይል ፡ ለመንጠቅ ፡ ማሰብ ፡ እንኳ ፡ አይኖርብንም ። አነስተኛ ፡ ገበሬን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በቅድሚያ ፡ የሚኖርብን ፡ ተግባር ፡ ያለውን ፡ የግል ፡ ድርጅቱንና ፡ የግል ፡ ንብረቱን ፡ በኃይል ፡ ሳይሆን ፡ ምሳሌዎች ፡ በማሳየት ፡ ወደ ፡ ሕብረት ፡ ድርጅቶች ፡ ማሸጋገር ፡ ሲሆን ፡ ለዚህም ፡ የማኅበራዊ ፡ ዕርዳታ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ። ከዚያም ፡ ያለጥርጥር ፡ በዛሬውም ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ለአነስተኛው ፡ ገበሬ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ አጉልቶ ፡ ለማሳየት ፡ የሚያስችሉ ፡ አያሌ ፡ ምሳሌዎች ፡ ይኖሩናል» (ኤንግልስ «የግብርና ፡ ጥያቄ ፡ በምዕራብ» ፤ ገጽ ፡ 17 የታተመው ፡ በአሌክሴየቫ ፡ በሩስያ ፡ ትርጉሙ ፡ ስሕተቶች ፡ አሉት ። አሪጅናሉ ፡ በ «Neue Zeit» ።)

## የወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ የትግል ፡ ስልቶች ።

ማርክስ ፡ የቀድሞው ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ በተለይ ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የሚገባውን ፡ አብዮታዊ ፡ አድራጎት ፡ አስፈላጊነትና ፡ ጠቅላላ ፡ ሁናቴዎችን ፡ በመገንዘብ ፡ ረገድ ፡ የነበረውን ፡ ጉድለት ፡ በመረዳት ፡ ያኪያሒደው ፡ ከነበረው ፡ የቴዎሪ ፡ ሥራው ፡ ጋር ፡ በማጣመር ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ በስልት ፡ በኩል ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ መደብ ፡ ትግል ፡ የነበረበትን ፡ ችግር ፡ ያለመሰልቸት ፡ ይከታተል ፡ ነበር ። በማርክስ ፡ ሥራዎች ፡ በሙሉ ፡ በተለይም ፡ ከኤንግልስ ፡ ጋር ፡ በተጻጻፈባቸው ፡ እ. ኤ. አ. በ 1913 ዓ. ም. ታትመው ፡ በወጡት ፡ ባለአራት ፡ ቅጽ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሰፊ ፡ አስተያየቶች ፡ ተሰጥተዋል ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ ማቴሪያል ፡ እስከ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ቢሆን ፡ ተሰብስቦ ፡ ተመርምሮና ፡ ተጠንቶ ፡ አብቅቷል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ስለዚህ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ሙሉ ፡ መልኩን ፡ ሳይዝ ፡ ብቃት ፡ ያለው ፡ የማያዳላና ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ለማለት ፡

አይቻልም ፡ ብሎ ፡ ማርክስ ፡ በጠቅላላው ፡ በሰጠው ፡ አስተያየት ፡ መወሰን ፡ ይኖርብናል ። ማርክስ ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ የትግል ፡ ሥልቶች ፡ መሠረታዊ ፡ ተግባር ፡ ያብራራው ፡ ከማቴሪያላዊና ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ አስተያየቶቹ ፡ ጋር ፡ በማስማማት ፡ ነው ። አንድ ፡ በትግል ፡ ላይ ፡ የቆየ ፡ ተራማጅ ፡ መደብ ፡ በሚያኪያሒደው ፡ ትግል ፡ ለሚያስፈልገው ፡ የትግል ፡ ትክክለኛ ፡ ሥልት ፡ መሠረት ፡ የሚሆነው ፡ በአለበት ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መደቦች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ በመረዳትና ፡ ከዚያም ፡ ይኸው ፡ ኅብረተሰብ ፡ የደረሰበትን ፡ ዕድገት ፡ ደረጃና ፡ ከሌሎች ፡ ኅብረተሰቦች ፡ ጋር ፡ ያሉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በጥሞና ፡ በመገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ መደቦችና ፡ አገሮች ፡ በሙሉ ፡ በአሉበት ፡ የሚኖሩ ፡ የመይለወጡ ፡ ሳይሆኑ ፡ በከፍተኛ ፡ ኃይል ፡ በቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው (ሕጎቻቸውም ፡ በየአንዳንዱ ፡ መደብ ፡ ኑሮ ፡ የኤኮኖሚ ፡ አቋም ፡ የሚወሰኑ ፡ ናቸው) ። ቅስቃሴ ፡ ደግሞ ፡ በተራው ፡ የሚታየው ፡ ወይንም ፡ ለመገንዘብ ፡ የሚቻለው ፡ ያለፈውን ፡ በሚመለከተው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በወደፊቱም ፡ ጭምር ፡ በመሆኑና ፤ ይኸውም ፡ ቀሰስተኛ ፡ ለውጥ ፡ ብቻ ፡ የሚታያቸው «የአዝጋሚ ፡ ለውጥ ፡ አማኞች» እንደሚሉት ፡ ሳይሆን ፡ በዲያሌክቲካዊ ፡ መንገድ ፡ ነው ። «በዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ሁናቴ ፡ ክንውን ፡ ውስጥ ፡ ሀያ ፡ ዓመታት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቢቆጠሩ ፡ ነው» ሲል ፡ ማርክስ ፡ ለኤንግልስ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ገልጿል ። ከዚህም ፡ አያይዞ «ምን ፡ አልባት ፡ ወደፊት ፡ ሀያ ፡ ዓመታት ፡ ያዘሉ ፡ ቀናት ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉ ፡ ቢሆንም» ሲል ፡ ማርክስ ፡ በተጨማሪ ፡ አስገንዝቧል («ደብዳቤዎች» ፤ ቅጽ ፡ 3 ፤ ገጽ ፡ 127) ። የወዝ ፡ አደሩ ፡ የትግል ፡ ስልት ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ የመደብን ፡ ንቃተ ፡ ሕሊና ፡ ለመመሥረት ፡ የታጋዩን ፡ የበሰለውን ፡ መደብ ፡ የትግል ፡ ወኔ ፡ ለማጠናከር ፡ የፖለቲካ ፡ አለመ



ስፋፋትንና «ሠላማዊ» ዕድገት ፡ ተብሎ ፡ በአንዳንዶቹ ፡ ዘንድ ፡ የሚጠራው ፡ ጉታታ ፡ ዕድገት ፡ የተፈጸመባቸውን ፡ ክፍለ ፡ ዘመናት ፡ መሣሪያ ፡ በማድረግ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ጥረት ፡ በጠቅላላው ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ግብ ፡ ማለት «ሀያ ፡ ዓመታት ፡ በውስጣቸው ፡ አልፈው ፡ በሚገኙባቸው» ታላላቅ ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ለሚፈጸሙት ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባሮች ፡ ተጨባጭ ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ወደሚያስችለው ፡ ደረጃ ፡ የመደቡን ፡ ግሥጋሤ ፡ በመምራት ፤ በማንኛውም ፡ የእድገት ፡ ደረጃና ፡ በማንኛውም ፡ ቅጽበት ፡ የማይቀሩትን ፡ ነባራዊ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ዲያሌክቲክ ፡ መገንዘብ ፡ አለበት ።» በዚህ ፡ ረገድ ፡ ማርክስ ፡ ያቀረባቸው ፡ ሁለት ፡ ክርክሮች ፡ የተለየ ፡ ጠቃሚነት ፡ አላቸው ፤ አንደኛው «የፍልስፍና ፡ ድህነት» በተባለው ፡ ሥራው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ የሚመለከተው ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትግልና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ድርጅቶች ፡ ነው ። ሌላው ፡ ደግሞ ፡ የሚገኘው «በኮሙኒስት ፡ ማኒፌስቶ» ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ የሚመለከተውም ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ የፖለቲካ ፡ ተግባሮች ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፤ «ከፍተኛ ፡ መጠን ፡ ያለው ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የማይተዋወቁ ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ያከማቻል ። በመካከላቸው ፡ ያለው ፡ ውድድር ፡ ይከፋፍላቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአለቃቸው ፡ ጋር ፡ ባላቸው ፡ የጋራ ፡ ቅራኔ ፡ በአንድ ፡ ሀሳብ ፡ የሚያስተባብራቸው ፡ የአበል ፡ መኖር ፡ ነው ። ይህም ፡ የሠራተኞቹን ፡ ማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ ይመሠርታል… በመጀመሪያ ፡ በተነጣጣይ ፡ እራሳቸውን ፡ በቡድኖች ፡ ይመሠርታሉ ፤ የካፒታል ፡ ቋሚ ፡ ትብብር ፡ በተነሳባቸው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከአበላቸው ፡ ይልቅ ፡ ለእነሱ ፡ አሳሳቢ ፡ የሚሆንባቸው ፡ የማኅበሩ ፡ መኖር ፡ ነው … በዚህ ፡ ትግል — የእርስ ፡ በእርስ ፡ ጦርነት — ማለት ፡ ይቻላል ፡ ለሚቀጥለው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁናቴዎች ፡ ሁሉ ፡ እየተከማቹና ፡ እየተጠናከሩ ፡ ይ

ሔዳሉ ። ማኅበሩ ፡ እዚህ ፡ ነጥብ ፡ ወይንም ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ከደረሰ «በኋላ ፡ የፖለቲካ ፡ ጠባይ ፡ ይኖረዋል ። » እዚህ ፡ ላይ » ለሚመጣው ፡ ፍልሚያ» ወዝ ፡ አደሩ ፡ ኃይሎቹን ፡ ለሚያዘጋጅበት ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለብዙ ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ የሚያስፈልገው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትግል ፡ ፕሮግራምና ፡ ስልቶችና ፡ እንዲሁም ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ እንቅስቃሴ ፡ ይኖራሉ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ የኢንዱስትሪ «ብልጽግና ፡ ወዝ ፡ አደሩን ፡ በገንዘብ ፡ ለመግዛት» እንዴት ፡ እንደሚያሳስብ ፤ («ለኤንግልስ ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎች» ፤ ቅጽ ፡ አንድ ፤ ገጽ ፡ 136) ከትግላቸው «ለመቀልበስ» ፤ እንዴት ፡ እንደተሞከረ ፡ በጠቅላላው ፡ ይህ ፡ ብልጽግና «የሠራተኛውን ፡ ሞራል ፡ እንዴት ፡ እንደሚያዳክመው» (ቅጽ ፡ ሁለት ፤ ገጽ ፡ 218) የእንግሊዝ ፡ ወዝ ፡ አደር «የቡርዧዋ ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያድርበት» ይህ ፡ ከብሔሮች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የቡርዧዋ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ብሔር ፡ ከቡርዧዋው ፡ አስተዳደር ፡ ጐን ፡ የቡርዧዋ ፡ መሣፍንቶችና ፡ መንፈሳቸው ፡ በቡርዧዋነት ፡ የተመረዘ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ለማሠለፍ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጥረት (ቅጽ ፡ ሁለት ፤ ገጽ ፡ 290) የወዝ ፡ አደሩ ፡ አብዮታዊ ፡ ኃይልና ፡ ወኔ ፡ እንዴት ፡ እንደመነመነ» (ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 124) «የእንግሊዝ ፡ ሠራተኞች ፡ በቡርዧዋ ፡ መንፈስ ፡ ከተለከፉበት ፡ በሽታ ፡ እስኪያገግሙ ፡ ድረስ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ መቆየት ፡ እንዴት ፡ እንደሚያስፈልግ» (ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 127) የእንግሊዝ ፡ የሞያተኞች ፡ ንቅናቄ ፡ እንዴት «የቻርቲስቶች ፡ ንቅናቄ ፡ ብርታት ፡ እንደሚጐለው » (1866 ፤ ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 305) የእንግሊዝ ፡ የሠራተኞች ፡ መሪዎች ፡ በተስፈንጣሪ ፡ ቡርዧዋና ፡ በሠራተኛው ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡ እንደሚገኙ (ሆሊኦክን ፡ በሚመለከተው ፡ ላይ ፤ ቅጽ ፡ አራት ፤ ገጽ ፡ 209) በእንግሊዝ ፡ ሞኖፖሊ ፡ ምክንያትና ፡ ይህ ፡ ሞኖፖሊ ፡ እስከአለ ፡ ድረስ ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደማይንቀሳቀስ (ቅጽ ፡ አራት ፤ ገጽ ፡ 436) በማሳየትና ፡ በማብራራት ፡ ስለእንግሊዝ ፡ የሞያተ



ኞች ፡ እንቅስቃሴ ፡ ኤንግልስና ፡ ማርክስ ፡ ካቀረቧቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ ጋር ፡ በማመዛዘን ፡ መታየት ፡ አለበት ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትግል ፡ ስልቶች ፡ ጠቅላላውን ፡ ይዘትና ፡ (ውጤቱን) በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የታዩት ፡ ሰፊ ፡ ባለ ፤ አጠቃላይ ፡ ዲያሌክቲካዊና ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ አብዮታዊ ፡ አቋም ፡ ነው ።

«የኮሙኒስት ፡ ማኒፌስቶ» የፖለቲካ ፡ ትግልን ፡ ስልቶች ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ ማርክሳዊ ፡ መርሆ ፡ አቅርቧል ። «ኮሙኒስቶች ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ አስቸኳይ ፡ ዓላማዎች ፡ ከግብ ፡ እንዲደርሱና ፡ ቅጽበታዊ ፡ ፍላጐቶቹ ፡ እንዲሟሉ ፡ የሚታገሉ ፡ ሲሆን ፤ በጊዜው ፡ ንቅናቄ ፡ ግን ፡ የንቅናቄውን ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ ጠብቀውና ፡ ወክለው ፡ ይታገላሉ ።» በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው «እ. ኤ. አ. በ 1846 ዓ. ም. ፖላንድ ፡ ውስጥ ፡ የክራኮቮን ፡ ዓመፅ «የገበሬዎችን ፡ አብዮት» ያስከተለውን ፡ ፓርቲ»[9] ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. የደገፈው ። ማርክስ ፡ ጀርመንም ፡ ውስጥ ፡ ጭልጥ ፡ ያሉትን ፡ አብዮታዊ ፡ ዴሞክራቶችን ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1848-49 ዓ. ም. ድረስ ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የደገፈ ፡ ሲሆን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስለትግል ፡ ስልቶች ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አላጠፈውም ። ማርክስ ፡ የጀርመንን ፡ ቡርዧዋ ፡ የተመለከተው «ከመጀመሪያው ፡ ጀምሮ ፡ ሕዝቡን ፡ ለመክዳት ፡ ያዘነበለና» (ዓላማዎቹን ፡ ከግብ ፡ ለማድረስ ፡ ብቻ ፡ ከገበሬው ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገባ) «ከቀድሞው ፡ ኅብረተሰብ ፡ ቀንደኛ ፡ እንደራሴዎች ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ መሆኑን» በመገንዘብ ፡ ነው ። ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ የቡርዧዋ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ አብዮት ፡ በተኪያሒያደ ፡ ጊዜ ፡ የቡርዧዋው ፡ መደብ ፡ የነበረውን ፡ አቋም ፡ ማርክስ ፡ በሚከተለው ፡ አስተያየት ፡ ገልጾታል ። ማርክስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጀርመን ፡ ቡርዧዋ ፡ መደብ ፡ ስለነበረው ፡ አቋም ፡ የሰጠው ፡ ትንታኔ ፡ ወደኋላ ፡ በቀረ ፡ ባልበሰለ ፡ አስተሳሰብ ፡ በሚታይ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ሳ

ይሆን ፡ ኅብረተሰብ ፡ በትክክለኛው ፡ እንቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ የሚመረምር ፡ የማቴሪያሊዝም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ «… በራሱ ፡ ዕምነት ፡ የሌለው ፤ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ዕምነቱን ፡ ያልጣለ ፤ ከበላዩ ፡ ባሉት ፡ የሚያጉረመርም ፤ ከበታቹ ፡ ባሉት ፡ የሚርበደበድ … በዓለም ፡ ማዕበል ፡ ያለፍላጐቱ ፡ የተገደደ ፤ … በየትኛውም ፡ መንገድ ፡ ኃይል ፡ የሌለው ፤ የሌሎቹን ፡ የራሱ ፡ አስመስሎ ፡ የሚቀጥፍ … አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ የሌለው ፤ … ጤናማና ፡ ጠንካራ ፡ ያልሆነ ፡ አዲስ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያላቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ጽኑ ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ጃጀ ፡ አስተሳሰቡና ፡ ወደግል ፡ ጥቅሙ ፡ ለመጠምዘዝ ፡ የሚጥር ፡ ዓመለ ፡ መጥፎ ፡ ገዝጋዛ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ።» («አዲሱ ፡ የሬይን ፡ ጋዜጣ» 1848፤ «የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ውርስ» ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 212 ይመልከቱ) ። ማርክስ ፡ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ለኤንግልስ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ (ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 224) እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. የተነሳው ፡ አብዮት ፡ የከሸፈው ፡ ቡርዥዋዎች ፡ ለመብት ፡ ለመታገል ፡ ከመነሳት ፡ ይልቅ ፡ በሠላም ፡ በባርነት ፡ መኖርን ፡ ስለመረጡ ፡ ነው ። ከ 1848-49 ዓ. ም. የነበረው ፡ አብዮታዊ ፡ ትግል ፡ እንዳበቃ ፡ በአብዮት ፡ ለመጫወት ፡ የሚደረገውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሙከራ ፡ ማርክስ ፡ በመቃወም (ከሻፔርና ፡ ከቪሊኽ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ትግል) «ሠላማዊ» በሚመስል ፡ ሁናቴ ፡ ውስጥ ፡ ለአዲስ ፡ አብዮት ፡ ዝግጅት ፡ እንዲደረግ ፡ በሰፊው ፡ ጥሯል ። ማርክስ ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ እንዲኪያሔድ ፡ የፈለገበትን ፡ መንፈስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1856 ዓ. ም. ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረው ፡ ሁናቴ ፡ ከገለጸው ፡ አድናቆት ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ የአድሃሪዎች ፡ የጭለማ ፡ ዘመን ፡ ነበር ። ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ አቅጣጫውን ፡ የሚይዘው ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ አብዮት «የገበሬው ፡ ጦርነት» እንደገና ፡ በማስነሣት ፡ ለመደገፍ ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ ነው (ለኤንግልስ ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎች» ፤



ቅጽ ፡ ሁለት ፤ ገጽ ፡ 108) ። ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ የዴሞክራት (የቡርዥዋዎች) አብዮት ፡ ያልተሟላ ፡ ሆኖ ፡ በቀረበት ፡ ጊዜ ፡ የገበሬውን ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ ኃይል ፡ ለማጐልመስ ፡ ስለሚቻልበት ፡ መንገድ ፡ ማሰብ ፡ የሶሺያሊስት ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ስልት ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ ማርክስ ፡ አተኩሮ ፡ ተመልክቶታል ። ላሳል «ለፕሩስያ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ የሠራተኞችን ፡ ንቅናቄ ፡ የከዳው (ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 210) የባለርስቶችንና ፡ የፕሩስያን ፡ ብሔረተኛነት ፡ መንፈስ ፡ የሚደግፍ ፡ ስለነበር ፡ ነው ። ኤንግልስ ፡ ከማርክስ ፡ ጋር ፡ ወደፊት ፡ በጋራ ፡ ቤት ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ስለሚያወጡት ፡ መግለጫ ፡ ሲጻጻፉ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1865 ዓ. ም. ለማርክስ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ «ግብርና ፡ ይበልጡን ፡ እጅ ፡ በያዘበት ፡ አገር ፡ በባላባቶች ፡ መሣፍንትነት ፡ ከንድ ፡ ሥር ፡ ስለሚበዘበዙት ፡ የገጠር ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ቃል ፡ ሳይናገሩ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ቡርዥዋውን ፡ ለይቶ ፡ ለመወንጀል ፡ መነሳት ፡ ገበሬውን ፡ እንደመክዳት ፡ ይቆጠራል» (ቅጽ ፡ ሦስት ፤ ገጽ ፡ 217) ። እ. ኤ. አ. ከ 1864 ዓ. ም. እስከ 1870 ዓ. ም. ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ በጀርመን ፡ ይኪያሔድ ፡ የነበረው ፡ የቡርዥዋዎች ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ አብዮት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ ያበቃበት ፡ ዘመን ፡ ነበር ። ይህ ፡ ዘመን ፡ የፕሩስያና ፡ የአውስትሪያ ፡ በዝባዥ ፡ መደቦች ፡ ይህንኑ ፡ አብዮት ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ከላይ ፡ ሆነው ፡ የሚታገሉበት ፡ ዘመን ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማርክስ ፡ ከቢስማርክ ፡ ጋር ፡ ይሞካሽ ፡ የነበረውን ፡ ላሳልን ፡ ብቻ ፡ በመንቀፍ ፡ ሳይወሰን «በአውስትሮፊልዝም» እና ፡ ለግለሰቦች ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ በመከራከር ፡ የተለከፈውን ፡ ሊብክነኽትን ፡ አርሞታል ። ማርክስ ፡ የፈለገው «ድል ፡ አድራጊ» የሆነው ፡ የፕሩስያ ፡ ዩንከር[10] ፡ ተቀብሎ ፡ የማይጠቀምበት ፡ የፕሩስያ ፡ ጦር ፡ ኃይል ፡ ባገኛቸው ፡ ድሎች ፡ ሁናቴ ፡ በእሱ ፡ ላይ ፡ የተኪያሔደውን ፡ አብዮታዊ ፡ ትግል ፡ ወዲያውኑ ፡ የሚያድስ ፡

ቢስማርክንና ፡ አስትሮፊልስን ፡ በጭካኔ ፡ የሚፋለም ፡ ስልት ፡ ነው («ለኤንግልስ ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎች» ቅጽ ፡ ሶስት ፤ ገጾች ፡ 134, 136, 147, 179, 204, 210, 215, 418, 437, 440-441) ። ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1870 ዓ. ም. መስከረም ፡ 9 ቀን ፡ ለኢንተርናስዮናል ፡ ባቀረበው ፡ ከፍተኛ ፡ መልዕክት ፡ የፈረንሳይ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ያለሰዓቱ ፡ እንዳያምፁ ፡ አስጠንቅቆ ፡ ነበር ። ይሁንና (እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም. ) ባመፅ ፡ ጊዜ (ለኩገልማን ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ) የሰፊውን ፡ ሕዝብ ፡ አብዮታዊ ፡ እርምጃ ፡ በከፍተኛ ፡ ስሜት ፡ አድንቋል ። በማርክስ ፡ ዲያሌክቲካዊ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ አስተያየት ፡ በዚያን ፡ ሁናቴ ፡ ውስጥ ፡ አብዮታዊ ፡ ትግል ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ድል ፡ መመታት ፡ በብዙ ፡ ቦታዎች ፡ እንደደረሰው ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ ትግልና ፡ ውጤት ፡ ሲታይ ፡ ይዞታን ፡ ከመልቀቅና ፡ ያለምንም ፡ ትግል ፡ እጅን ፡ ከመስጠት ፡ የተሻለ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ እጅ ፡ መስጠት ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ ሞራል ፡ ሰብሮ ፡ የትግል ፡ ወኔውን ፡ ያከስመዋል ። ማርክስ ፡ በፖለቲካ ፡ ውድቀት ፡ ጊዜና ፡ የቡርዥዋው ፡ ተጽዕኖ ፡ በነገሠበት ፡ ወቅት ፡ በሕግ ፡ መንገድ ፡ የሚኪያሔደውን ፡ ትግል ፡ በሙሉ ፡ እየደገፈ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1877-1878 ዓ. ም. የተለየ ፡ ፀረ-ሶሺያሊስት ፡ ሕግ[11] ፡ እንደወጣ ፡ የሞስትን «አብዮታዊ ፡ ቃላቶች» በጥብቅ ፡ አውግዟል ። እንዲሁም ፡ ከዚሁ ፡ ባላነሰ ፡ ሁናቴ ፡ የነበረው ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራት ፡ ፓርቲ ፡ ያደረበትን ፡ የአድርባይ ፡ ስሜት ፡ በወጣው ፡ ፀረ-ሶሺያሊስት ፡ ሕግ ፡ ምክንያት ፡ ያለማወላወል ፡ በቆራጥነት ፡ በአብዮታዊ ፡ ወኔና ፡ ዝግጅት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ የጊዜው ፡ ሥርዓት ፡ የሚያወግዘው ፡ ትግል ፡ ወዲያውኑ ፡ ባለመጀመሩ ፡ በጽኑ ፡ ነቅፎታል ። («ለኤንግልስ ፡ የተጻፉ ፡ የማርክስ ፡ ደብዳቤዎች» ቅጽ ፡ አራት ፤ ገጾች ፡ 397, 404, 418, 472, 424 ። ለዞርጌ ፡ የተጻፉትንም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይመልከቱ ። )

የተጻፈው ፡ እ. ኤ. አ. በ 1914 ዓ. ም.
ከሐምሌ ፡ እስከ ፡ ሕዳር ።

ቅጽ ፡ 26 ፤
ገጾች ፡ 43-81



## ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ።

እንዴት ፡ ያለ ፡ የእውቀት ፡ ነበልባል ፡ ጠፋ ፤
ምን ፡ ዓይነት ፡ የልብ ፡ ትርታ ፡ አከተመ[12]!

እ. ኤ. አ. በ 1895 ዓ. ም. ነሐሴ ፡ 5 ቀን ፡ ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለየ ። ኤንግልስ ፡ ጓደኛው ፡ ካርል ፡ ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1883 ዓ. ም. ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ በሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ የቀረው ፡ ታላቁ ፡ ምሁርና ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ መምሕር ፡ እሱ ፡ ነበረ ። ማርክስንና ፡ ኤንግልስን ፡ እንደሚባለው ፡ የአርባ ፡ ቀን ፡ ዕድላቸው ፡ የሕይወት ፡ ዕጣቸው ፡ ካገናኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ ዕድሚያቸውን ፡ በሙሉ ፡ ለአንድ ፡ የጋራ ፡ ዓላማ ፡ አውለውታል ። ስለዚህ ፡ ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ ለወዝ ፡ አደሩ ፡ ምን ፡ እንዳደረገ ፡ ለመረዳት ፡ ማርክስ ፡ ለዘመናዊው ፡ ሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ዕድገት ፡ ያከናወናቸው ፡ ሥራዎች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ፍሬያማ ፡ መሆናቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። የወዝ ፡ አደሩን ፡ መደብ ፡ ከቡርዥዋው ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የፈጠረውና ፡ ያደራጀው ፡ የጊዜው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሥርዓት ፡ መሆኑንና ፡ የሠራተኛው ፡ መደብና ፡ ጥያቄዎቹ ፡ የፈለቁት ፡ ከዚሁ ፡ ሥርዓት ፡ መሆኑን ፡ በመጀመሪያ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ለማስረዳት ፡ የቻሉት ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ናቸው ። የሰውን ፡ ልጅ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከተጫኑት ፡ ጠንቆች ፡ የሚገለግለውና ፡ ነፃ ፡ የሚያወጣው ፡ ቅን ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ ግለሰቦች ፡ መልካም ፡ ጥረት ፡ ሳይሆን ፡ የተደራጀው ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ የመደብ ፡ ትግል ፡ መሆኑን ፡ ያሳዩ

ት ፡ ሁለቱ ፡ ጓዶች ፡ ናቸው ። ሶሺያሊዝም ፡ የሕልመኞች ፡ ፈጠራ ፡ ሳይሆን ፡ የዘመናዊ ፡ ኅብረተሰብ ፡ የምርት ፡ ኃይሎች ፡ ዕድገት ፡ የመጨረሻ ፡ ግብና ፡ አስፈላጊ ፡ ውጤት ፡ መሆኑን ፡ በሳይንሳዊ ፡ ሥራዎቻቸው ፡ ያረጋገጡት ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ናቸው ። እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ የተመዘገበው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ የመደቦች ፡ ትግል ፡ ውጤት ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ መደብ ፡ ሌላውን ፡ መደብ ፡ እየጣለ ፡ ባገኘው ፡ ድልና ፡ የአገዛዝ ፡ ሥልጣን ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። ይህም ፡ የታሪክ ፡ ሒደት ፡ የመደብ ፡ ትግልና ፡ አንዱ ፡ መደብ ፡ ሌላውን ፡ መደብ ፡ የመጨቆን ፡ ሥርዓት — የግል ፡ ባለንብረትነትና ፡ ሥርዓተ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ የኅብረተሰብ ፡ የምርት ፡ አቀራረብ ፡ መሠረቶች ፡ እስኪወገዱ ፡ ድረስ ፡ ይቀጥላል ። የወዝ ፡ አደሩ ፡ ዓላማ ፡ እነዚህ ፡ መሠረቶች ፡ እንዲደመሰሱ ፡ የታቀደ ፡ በመሆኑ ፡ የተደራጁ ፡ ሠራተኞች ፡ ተገቢ ፡ ትግል ፡ በእነሱ ፡ ላይ ፡ መዝመት ፡ አለበት ። ስለዘህ ፡ ማንኛውም ፡ የመደብ ፡ ትግል ፡ የፖለቲካ ፡ ትግል ፡ ነው ።

የማርክስና ፡ የኤንግልስ ፡ አስተያየቶች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለነፃነታቸውና ፡ ለመብታቸው ፡ በሚታገሉ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ እ. ኤ. አ. በ 1840 ዎቹ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በነበረው ፡ የሶሺያሊስት ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍና ፡ የኅብረተሰብ ፡ ንቅናቄ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ የነበሩ ፡ ሲሆን ፡ የፈጸሙትም ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ ተደርጎ ፡ የማይታወቅ ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ያለው ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለፖለቲካ ፡ መብት ፡ ከነገሥታት ፤ ከፖሊሶችና ፡ ከቀሳውስት ፡ ጋር ፡ በተደረገው ፡ ትግል ፡ በቡርዥዋውና ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ ፍላጎቶች ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ መፃረር ፡ ለመገንዘብ ፡ የማይቻሉ ፡ ተሰጥዎ ፡ ያላቸውና ፡ የሌላቸው ፡ ሀቀኞችና ፡ ቀጣፊዎች ፡ የሆኑ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ በግሉ ፡ አንድ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኃይል ፡ በመሆን ፡



ንቅናቄ ፡ እንዲያኪያሒድ ፡ የሚጠቁመውን ፡ ሀሳብ ፡ አይደግፉትም ፡ ነበር ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በጊዜው ፡ ለነበሩት ፡ ገዥዎችና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የአስተዳደርና ፡ የፍትሕ ፡ ጉድለት ፡ ብቻ ፡ በማስረዳት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሠላምና ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጠቅላላ ፡ ደህንነት ፡ ለመመሥረት ፡ ይቻላል ፡ ብለው ፡ የሚያስቡ ፡ ከመካከላቸውም ፡ ብልሆች ፡ ናቸው ፡ የሚባሉ ፡ አያሌ ፡ ሕልመኞች ፡ ነበሩ ። ትግል ፡ የሌለው ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ያልሙ ፡ ነበር ። ከነአካቴውም ፡ በመጨረሻው ፡ በጊዜው ፡ የነበሩት ፡ ሶሺያሊስቶችና ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ ወዳጆች ፡ ነን ፡ ባዮች ፡ በሙሉ ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፤ ወዝ ፡ አደሩን ፡ የተመለከቱት ፡ እንደ ፡ አንጀት ፡ ሕመም ፡ አድርገው ፡ ነው ። ከኢንዱስትሪም ፡ ዕድገት ፡ ጋር ፡ እያደገ ፡ ሲሔድ ፡ ተሸብረውና ፡ የሚያደርጉትንም ፡ አጥተው ፡ ነበር ። ስለዚህ «የታሪክን ፡ ጐማ» ከመሽከርከር ፡ ለመግታት ፡ የኢንዱስትሪንና ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ ዕድገት ፡ ለማቆም ፡ ስለሚቻልበት ፡ ዘዴ ፡ ሁሉም ፡ ማሰብ ፡ ጀመረ ። ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ ዕድገት ፡ የተፈጠረው ፡ ጠቅላላ ፡ መሸበር ፡ አልተመለከታቸመም ፤ ይልቁንም ፡ ሁለቱ ፡ ጓዶች ፡ ተስፋቸውን ፡ በወዝ ፡ አደሩ ፡ የማያቋርጥ ፡ ዕድገት ፡ ላይ ፡ መሠረቱ ። የወዝ ፡ አደሩ ፡ ቁጥር ፡ እየበረከተ ፡ ሲሔድ ፡ እንደ ፡ አብዮተኛ ፡ መደብ ፡ የሚኖረውም ፡ ኃይሉ ፡ እየተጠናከረ ፡ በመሔዱ ፡ የሶሺያሊዝም ፡ መምጣት ፡ እየተቃረበ ፡ ከመሔዱም ፡ በላይ ፡ ዕውን ፡ ይሆናል ። ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ለሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ያበረከቱት ፡ በጎ ፡ አገልግሎት ፡ በጥቂት ፡ ቃላት ፡ ሊገለጹ ፡ ይችላሉ ፤ ሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ እራሱን ፡ እንዲያውቅና ፡ ስለራሱ ፡ እንዲያስብ ፡ አስተምረውታል ። እንዲሁም ፡ ሳይንስን ፡ ከሕልም ፡ ወደ ፡ ዕውን ፡ ለውጠውታል ።

የኤንግልስ ፡ ስምና ፡ ሕይወት ፡ በጠቅላላው ፡ በየአንዳንዱ ፡ ሠራተኛ ፡ ዘንድ ፡ መታወቅ ፡ ያለበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። የኛ ፡ እትመቶች ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ በሩሲያ ፡ ሠራ

ተኞች ፡ ዘንድ ፡ በመደብ ፡ ረገድ ፡ የሕሊና ፡ ንቃት ፡ እንዲ
ኖር ፡ የታቀደ ፡ ሲሆን ፡ በእነዚህም ፡ አርቲክሎች ፡ ለማስተ
ማር ፡ የታቀደው ፡ ይህንኑ ፡ ስለሆነ ፡ የዘመናዊው ፡ ወዝ
አደር ፡ ሁለት ፡ መምሕራን ፡ ከሆኑት ፡ የአንደኛውን ፡ ማለ
ት ፡ የኤንግልስን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ ማቅረብ ፡
ያለብን ፡ ምክንያቱ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

ኤንግልስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1820 ዓ. ም. በባርመን ፡ ከተማ ፡
በፕሩስያ ፡ ግዛት ፡ በሬይን ፡ አውራጃ ፡ ተወለደ ። አባቱ ፡
የአንድ ፡ ፋብሪካ ፡ ባለቤት ፡ ነበር ። ኤንግልስ ፡ እ. ኤ. አ.
በ 1838 ዓ. ም. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርቱን ፡ በቤተሰቦ
ቹ ፡ ምክንያት ፡ ሳይጨርስ ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡
ውስጥ ፡ በጸሓፊነት ፡ ተቀጥሮ ፡ መሥራት ፡ ተገደደ ። የ
ንግድ ፡ ሥራ ፡ ኤንግልስን ፡ የሳይንስና ፡ የፖለቲካ ፡ ትምህ
ርቱን ፡ ከመከታተል ፡ አላገደውም ። ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ት
ምህርት ፡ ቤት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የነገሥታት ፡
አገዛዝንና ፡ ቢሮክራሲ ፡ የሚፈጽመውን ፡ በደል ፡ እጅግ ፡
አድርጐ ፡ ይጠላ ፡ ነበር ። የፍልስፍና ፡ ትምህርትም ፡ በ
መከታተሉ ፡ ይህ ፡ ጥላቻው ፡ ይበልጥ ፡ እየተጠናከረ ፡ እን
ዲሔድ ፡ አድርጐታል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሔግል ፡ ትምህ
ርት ፡ በጀርመን ፡ ፍልስፍና ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ተጽንኦ ፡ ስለ
ነበረው ፡ ኤንግልስም ፡ የእሱ ፡ ተከታይ ፡ ሆነ ። ምንም ፡
እንኳ ፡ ሔግል ፡ የፕሩስያ ፡ የነገሥታት ፡ አገዛዝ ፡ ደጋፊ ፡
ሆኖ ፡ ይህንኑ ፡ መንግሥት ፡ በማገልገል ፡ በበርሊን ፡ ዩኒ
ቬርሲቲ ፡ በፕሮፌሰርነት ፡ ይሠራ ፡ የነበረ ፡ ቢሆንም ፡
ትምህርቱ ፡ አብዮታዊ ፡ ነበር ። ሔግል ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ አእ
ምሮ ፡ አስተዋይነት ፡ በመብቱ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ እምነት
ና ፡ ጠቅላላው ፡ ዓለም ፡ ያለማቋረጥ ፡ የለውጥና ፡ የዕድገ
ት ፡ ሒደት ፡ እንደሚያከናውን ፡ የነበረው ፡ ፍልስፍና ፡
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጊዜውን ፡ ሁናቴ ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፤
የነበሩትን ፡ የበርሊኑን ፡ ፈላስፋ ፡ ተማሪዎች ፡ ገሚሶቹ ፡



በጊዜው ፡ የነበረውን ፡ ሁናቴ ፡ በመቃወም ፡ የሚኪያሔደ
ው ፡ ትግል ፡ ክፉውንና ፡ የተዛባውን ፡ ሥርዓት ፡ በመቃ
ወም ፡ ይኪያሔድ ፡ የነበረው ፡ ትግል ፡ እራሱ ፡ በዘለዓለ
ማዊው ፡ የሁናቴዎች ፡ ዕድገት ፡ ሒደት ፡ ውስጥ ፡ ሥሩን ፡
የሰደደ ፡ መሆኑን ፡ እንዲያምኑ ፡ አድርጓቸዋል ። ነገሮች ፡
ሁሉ ፡ ዕድገት ፡ ካላቸውና ፡ አንድ ፡ ሁናቴ ፡ ለሌላ ፡ ሁናቴ ፡
ቦታ ፡ ከለቀቀ ፡ የፕሩስያ ፡ ንጉሥ ፤ ወይንም ፡ የሩሲያ ፡ ፃር ፡
አገዛዝ ፡ በብዙዎቹ ፡ ድሕነት ፡ የጥቂቶቹ ፡ መበልጸግ ፡
ወይንም ፡ የቡርዥዋው ፡ የበላይነት ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ለ
ምን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀጥላል? የሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ የሚ
ያትተው ፡ ስለአእምሮና ፡ ስለሐሳብ ፡ ነበር ፤ በመሆኑም ፡
ሐሳባዊ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ፍልስፍና ፡ የተፈጥሮን ፡ የሰውና ፡
እንዲሁም ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ማኅበራዊ ፡ ግንኙነት ፡ ዕድ
ገት ፡ የመሠረተው ፡ በአእምሮ ፡ ዕድገት ፡ ላይ ፡ ነው ። ማ
ርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ስለዘለዓለማዊ ፡ ዕድገት ፡ ሒደት* ፡
የሔግልን ፡ ሐሳብ ፡ ሳይቃወሙ ፡ ሐሳባዊ ፡ የሆነውን ፡ ፍ
ልስፍና ፡ ባለመቀበል ፡ የተፈጥሮን ፡ ዕድገት ፡ የሚወስነ
ው ፡ የአእምሮ ፡ ዕድገት ፡ ሳይሆን ፡ ይልቁንም ፡ የአእምሮ ፡
ዕድገት ፡ የሚወሰነው ፡ ከተፈጥሮ ፡ ከማተር ፡ መሆኑን ፡
ለመገንዘብ ፡ ችለዋል ... ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ከሔግል
ና ፡ ከሌሎቹ ፡ የሔግል ፡ ተከታዮች ፡ ተለይተው ፡ ማቴሪ
ያሊስቶች ፡ ነበሩ ። ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ዓለምንና ፡ የሰ
ውን ፡ ልጅ ፡ ጠቅላላ ፡ ታሪክ ፡ በማቴሪያላዊ ፡ መንገድ ፡
በመመልከት ፡ የተፈጥሮ ፡ ክስተት ፡ በሙሉ ፡ የሚወሰነው ፡
በማቴሪያል ፡ ምክንያት ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የሰውም ፡

* ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ በአዕምሮ ፡ ዕድገታቸው ፡ የታ
ላላቆቹ ፡ የጀርመን ፡ ፈላስፋዎች ፡ በተለይ ፡ የሔግል ፡ ባለ
ውለታዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ደጋግመው ፡ ገልጸዋል ፤ «ያ
ለ ፡ ጀርመን ፡ ፍልስፍና ፡ ሳይንሳዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ አይኖ
ርም ፡ ነበር» ሲል ፡ ኤንግልስ ፡ አስረድቷል ።

ልጅ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፡ የሚወሰነው ፡ በማቴሪ
ያል ፡ ኃይሎች ፡ ማለት ፡ በምርት ፡ ኃይሎች ፡ መሆኑን ፡
ለመረዳት ፡ ችለዋል ። የሰውን ፡ ልጅ ፡ ፍላጐት ፡ ለማር
ካት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማምረት ፡ በሚደረገው ፡
ጥረት ፡ ሰዎች ፡ በመካከላቸው ፡ የሚመሠርቱት ፡ ግንኙነ
ቶች ፡ የሚገነባው ፡ በምርት ፡ ኃይሎች ፡ ዕድገት ፡ ነው ።
የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ክስተቶች ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምኞቶች ፡
ሐሳቦችና ፡ ሕጐችም ፡ የሚመሠረቱት ፡ በነዚህ ፡ ግንኙነ
ቶች ፡ ላይ ፡ ነው ። የምርት ፡ ኃይሎች ፡ ዕድገት ፡ በግል ፡
ባለንብረትነት ፡ የተመሠረተ ፡ የኅብረተሰብ ፡ ግንኙነት ፡
ይመሠርታል ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ የምርት ፡ ኃይሎ
ች ፡ ዕድገት ፡ አብዛኞቹን ፡ ከንብረታቸው ፡ አላቆ ፡ ጥቂቶ
ቹን ፡ የሚያበለጽግ ፡ መሆኑን ፡ እናያለን ፤ የዘመናዊ ፡ ማኅ
በራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡
አስወግዶ ፡ እራሱ ፡ ሶሺያሊስቶች ፡ ወደ ፡ አቀዱት ፡ ግብ ፡
ለማድረስ ፡ ጥረት ፡ ያደርጋል ። ሶሺያሊስቶች ፡ በሙሉ ፡
ማድረግ ፡ ያለባቸው ፡ በዘመናዊ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡
በራሱ ፡ አቋም ፡ ምክንያት ፡ ሶሺያሊዝምን ፡ ለማምጣት ፡
የሚመኘውን ፡ የኅብረተሰብ ፡ ኃይል ፡ ለይቶ ፡ ማወቅና ፡
ይህ ፡ ኃይል ፡ በፍላጐቱና ፡ በዓላማው ፡ እንዲነቃና ፡ ታሪ
ካዊ ፡ ግዳጁን ፡ እንዲፈጽም ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ይህ ፡ ኃይል ፡
ወዝ ፡ አደሩ ፡ ነው ። ኤንግልስ ፡ ወዝ ፡ አደሩን ፡ የተዋወ
ቀው ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ የእንግሊዝ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ መዲ
ና ፡ በነበረችው ፡ ማንቸስተር ፡ ውስጥ ፡ አባቱ ፡ በሽርክና ፡
ባለንብረት ፡ በነበረበት ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡
ውስጥ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1842 ዓ. ም. ተቀጥሮ ፡ በመሥራት ፡
ኑሮውን ፡ በቀጠለበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ኤንግልስ ፡ በዚህች ፡
ከተማ ፡ ይኖር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በቢሮ ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰ
ን ፡ ሠራተኞቹ ፡ የተፋፈጉባቸውን ፡ ጐጆዎች ፡ በመዘዋ
ወር ፡ ድሕነታቸውንና ፡ የመከራ ፡ ኑሮአቸውን ፡ በዓይኑ ፡
ለማየት ፡ በቅቷል ። ኤንግልስ ፡ እየተዘዋወረ ፡ በመመልከ



ት ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ስለእንግሊዝ ፡ ሠራተኛ ፡ መደብ ፡
በግልጽ ፡ የተጻፉትንና ፡ በእጁ ፡ ሊገቡ ፡ የቻሉትን ፡ የመን
ግሥት ፡ ሰነዶች ፡ በሙሉ ፡ ያነብ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡
ባደረገው ፡ ጥናትና ፡ መከታተል ፡ የተገኘው ፡ ፍሬ ፡ እ. ኤ.
አ. በ 1845 ዓ. ም. የታተመው «በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሠራ
ተኛው ፡ መደብ ፡ ሁኔታ» የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይ
ህን ፡ መጽሐፍ ፡ በመጻፍ ፡ ኤንግልስ ፡ ያበረከተው ፡ አስተ
ዋጽኦ ፡ ምን ፡ እንደነበር ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ገልጸናል ። ከኤን
ግልስም ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ መከራ ፡ በመግ
ለጽ ፡ እርዳታ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ያስገነዘቡ ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ። ወዝ ፡ አደሩ ፡ መከራ ፡ ተቀባይ ፡ መደብ ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የተራቆተው ፡ የኤኮኖሚ ፡ አቋሙ ፡ ለመብ
ቱ ፡ ያለማቋረጥ ፡ እንዲታገል ፡ የሚያስገድደው ፡ መሆኑን ፡
በመጀመሪያ ፡ ያስታወቀው ፡ ኤንግልስ ፡ ነው ። ታጋዩ ፡
ወዝ ፡ አደርም ፡ እራሱን ፡ በእርግጥ ፡ ይረዳል ። የሠራተኛ
ው ፡ መደብ ፡ የፖለቲካ ፡ ንቅናቄ ፡ ሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ለ
ችግሩ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ መፍትሔ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ብቻ ፡
መሆኑን ፡ ያስገነዝበዋል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ሶሺያሊዝም ፡
አንድ ፡ ኃይል ፡ የሚሆነው ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ የፖለ
ቲካ ፡ ትግል ፡ ዓላማ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኤንግልስ ፡ ስ
ለእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሠራተኛ ፡ ሕዝብ ፡ ሁናቴ ፡ በጻፈው ፡
መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የገለጻቸው ፡ ሐሳቦች ፡ በዚህ ፡ አስተ
ሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ሲሆኑ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡
አዲስ ፡ ቢሆኑም ፡ ዛሬ ፡ በአርቆ ፡ አስተዋይና ፡ ታጋይ ፡
ወዝ ፡ አደሮች ፡ ዘንድ ፡ ሙሉ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል ።
እነዚህ ፡ አሳቦች ፡ በከፍተኛ ፡ የድርሰት ፡ ሥልት ፡ በተዘጋ
ጀ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ትክክለኛ ፡ በሆኑ ፡ የእንግሊዝን ፡
ወዝ ፡ አደሮች ፡ የመከራ ፡ ኑሮ ፡ በሚያሳዩ ፡ አሳዛኝ ፡ ሥዕ
ሎች ፡ በተብራራ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጸዋል ። መጽ
ሐፉ ፡ በካፒታሊዝምና ፡ በቡርዥዋው ፡ ላይ ፡ የቀረበ ፡
አጋላጭና ፡ ከፍተኛ ፡ ክስ ፡ በመሆኑ ፡ የጋለ ፡ ስሜትን ፡

ፈጥሯል ። የኤንግልስ ፡ መጽሐፍ ፡ የዘመኑን ፡ ወዝ ፡ አደ
ር ፡ የችግር ፡ ኑሮ ፡ በገሐድ ፡ በማሳየቱ ፡ በየሥፍራው ፡ ይ
ነገርለት ፡ ጀመር ። በእርግጥም ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1845 ዓ. ም.
በፊትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ስለሠራተኛው ፡ መደብ ፡
ችግር ፡ እውነተኛና ፡ አስቃቂ ፡ ሐቅ ፡ የቀረበ ፡ ማስረጃ ፡
የለም ።

ኤንግልስ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ሶሺ
ያሊስት ፡ አልነበረም ። ማንቸስተር ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡
ጊዜ ፡ በዘመኑ ፡ በነበረው ፡ የሞያተኞች ፡ ንቅናቄ ፡ ውስጥ ፡
ከፍተኛ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ይፈጽሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡
ግንኙነት ፡ በመመሥረት ፡ ለእንግሊዝ ፡ ሶሺያሊስት ፡ ዕት
ሞች ፡ መጻፍ ፡ ጀመረ ። ኤንግልስ ፡ ከማርክስ ፡ ጋር ፡ ቀደ
ም ፡ ሲል ፡ ሲጻጻፍ ፡ የነበረ ፡ ቢሆንም ፤ የተዋወቁት ፡ እ.
ኤ. አ. በ 1844 ዓ. ም. ወደ ፡ ጀርመን ፡ ሲመለስ ፡ እግረ ፡
መንገዱን ፡ ፓሪስ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ማርክስም ፡ በዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሶሺያሊስቶችና ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕ
ይወት ፡ በመማረክ ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሆኖዋል ። ፓሪስ ፡ ውስ
ጥ ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞች «ቅዱስ ፡ ቤተሰብ ፡ ወይም ፡ የሂሳዊ ፡
ሂስ ፡ ሂስ» የተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ በጋራ ፡ ቤት ፡ ጻፉ ። ይህ ፡
መጽሐፍ «የእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ሁናቴ»
ከተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የ
ታተመና ፡ በአብዛኛው ፡ በማርክስ ፡ የተጻፈ ፡ ሲሆን ፡ የአ
ብዮታዊ ፡ ማቴሪያላዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ መሠረቶችን ፡ ያዘለ ፡
ነው ። ዋና ፡ ዋና ፡ ሐሳቦቹንም ፡ ከላይ ፡ ገልጸናል ። «ቅዱ
ስ ፡ ቤተሰብ» ለባወር ፡ ወንድማማቾች ፡ ለፈላስፋዎችና ፡
ለተከታዮቻቸው ፡ የተሰጠ ፡ አስቂኝ ፡ የቅጽል ፡ ስም ፡ ነው ።
እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከእውነተኛ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ከፓርቲዎ
ችና ፡ ከፖለቲካዎች ፡ በሙሉ ፡ የራቁና ፡ የተለየ ፡ ተግባራ
ዊ ፡ ሥራዎችን ፡ በሙሉ ፡ የተውና ፡ በአካባቢያችን ፡ ያለ
ውን ፡ ዓለምና ፡ ከእሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ የሚራመዱትን ፡
ሁናቴዎች ፡ በማሰላሰል ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ሒስ ፡ ሲሰብ



ኩ ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ። የባወር ፡ ወንድማማቾች ፡ ወዝ ፡ አደ
ሩን ፡ የተመለከቱት ፡ በአካባቢው ፡ ስለሚፈጸሙት ፡ ስሕ
ተቶች ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ አድርገው ፡ ነው ። ማርክስና ፡ ኤንግ
ልስ ፡ ይህን ፡ የተወናበደና ፡ ክፋት ፡ ያዘለ ፡ አስተሳሰብ ፡
በጥብቅ ፡ ተቃውመዋል ። በመንግሥቱና ፡ በባለሥልጣኑ ፡
መደብ ፡ በግፍ ፡ በተገዛውና ፡ በተጨቆነው ፡ በሰብዓ
ዊው ፡ ፍጡር ፡ በሠራተኛው ፡ ስም ፡ ማሰላሰል ፡ ብቻ ፡
ሳይሆን ፡ ለትክክለኛ ፡ ኅብረተሰብ ፡ ትግል ፡ እንዲደረግ ፡
ጠይቀዋል ። ወዝ ፡ አደሩን ፡ የተመለከቱት ፡ ይህን ፡ ትግል ፡
ለማኪያሔድ ፡ የሚችልና ፡ በትግሉም ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡
ኃይል ፡ አድርገው ፡ ነው ። «ቅዱስ ፡ ቤተሰብ» የተባለው ፡
መጽሐፍ ፡ ታትሞ ፡ ከመውጣቱም ፡ በፊት ፡ ኤንግልስ ፡ ማ
ርክስና ፡ ሩጌ ፡ ያሳትሙት ፡ በነበረው «የጀርመንና ፡ የፈ
ረንሳይ ፡ መጽሔት» በተባለው ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ «ስለ
ፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሒስ ፡ አዘል ፡ ጽሑፉን» አሳትሟል ።
በዚህ ፡ ጽሑፉ ፡ የዘመናዊውን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዋና ፡ ክስተት ፡
ሥርዓት ፡ ከሶሺያሊስት ፡ አስተሳሰብ ፡ አንፃር ፡ በመመልከ
ት ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ደንብ ፡ ያለጥርጥር ፡ የወለዳቸው ፡ መ
ሆኑን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሰፊ ፡ ምርምር ፡ አቀርቧ
ል ። የማርክስ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሥራዎች ፡ እጅግ ፡
ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ ያስከተሉ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡
ለመሠማራት ፡ የወሰነበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ከኤንግ
ልስ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ግንኙነት ፡ ነው ።

ኤንግልስ ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1845 ዓ. ም. እስከ 1847 ዓ.
ም. ድረስ ፡ ፓሪስና ፡ ብሩሴልስ ፡ ውስጥ ፡ በጀርመን ፡ ሠራ
ተኞች ፡ መካከል ፡ ሳይንሳዊና ፡ ተግባራዊ ፡ ሥራዎችን ፡
አጣምሮ ፡ በማኪያሒድ ፡ ኖሯል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ማርክስ
ና ፡ ኤንግልስ ፡ በምስጢር ፡ ከሚኪያሔደው ፡ የጀርመን
«ኮሙኒስት ፡ ኅብረት» ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለመመሥረት ፡
ችለዋል ። ኅብረቱም ፡ ሁለቱ ፡ ጓዶች ፡ የነበራቸውን ፡
የሶሺያሊዝም ፡ ፍልስፍና ፡ እንዲያስፋፉት ፡ ወከላቸው ።

በዚህም ፡ መንገድ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. ታትሞ ፡ የወ
ጣው ፡ ዝነኛው «የኮሙኒስት ፡ ፓርቲ ፡ ማኒፌስቶ» ተሠረ
ፀ ። ይህ ፡ ትንሽ ፡ መጽሔት ፡ እንደ ፡ ታላላቅ ፡ ቅጾች ፡ የ
ሚቆጠር ፡ ነው ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የዚህ ፡ መጽሔት ፡
መንፈስ ፡ መላውን ፡ የተደራጀውንና ፡ ታጋዩን ፡ የሠለጠ
ነውን ፡ ዓለም ፡ ወዝ ፡ አደር ፡ ከማነቃቃቱም ፡ በላይ ፡ በት
ግሉ ፡ ድልን ፡ እንዲጐናጸፍ ፡ ይመረዋል ።

በመጀመሪያ ፡ ፈረንሳይ ፡ ውስጥ ፡ የፈነዳውና ፡ በኋላ
ም ፡ በሌሎች ፡ የምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡
ያንሰራራው ፡ እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. የተቀሰቀሰው ፡ አብ
ዮት ፡ ማርክስንና ፡ ኤንግልስን ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገራቸ
ው ፡ መልሷቸዋል ። የሬይን ፡ ፕሩስያ ፡ ውስጥ ፡ ማርክስ
ና ፡ ኤንግልስ ፡ ኰሎኝ ፡ ውስጥ ፡ እየታተመ ፡ ይወጣ ፡ የነ
በረውን «አዲሱ ፡ የሬይን ፡ ጋዜጣ» የተባለውን ፡ ጋዜጣ ፡
በኃላፊነት ፡ ተረክበው ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመሩ ። ሁለቱ ፡ ጓ
ደኞች ፡ የሬይን ፡ ፕሩስያ ፡ ውስጥ ፡ ለነበረው ፡ ዴሞክራ
ቲካዊ ፡ የአብዮት ፡ ሒደት ፡ ሕይወት ፡ ነበሩ ። ሁለቱም ፡
ለሰፊው ፡ ሕዝብ ፡ መብትና ፡ ፍላጐት ፡ ከአድኃሪ ፡ ኃይሎ
ች ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ ሕይወታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ታግለ
ዋል ። እንደሚታወቀው ፡ የአድኃሪው ፡ ኃይል ፡ በርትቶ
«አዲሱ ፡ የሬይን ፡ ጋዜጣ» እንዳይታተም ፡ ተከለከለ ።
ማርክስ ፡ ከስደት ፡ ላይ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የፕሩስያ ፡ ዜግነ
ቱን ፡ የተነፈገ ፡ ሲሆን ፡ አሁንም ፡ ከሀገር ፡ እንዲወጣ ፡
ተደርጓል ። ኤንግልስ ፡ በሰፊው ፡ ሕዝብ ፡ የመሣሪያ ፡ ትግ
ል ፡ ተሳትፎ ፡ በሶስት ፡ ውጊያዎች ፡ ላይ ፡ ተዋግቶ ፡ የሕዝ
ቡ ፡ ዓመፅ ፡ ድል ፡ በተመታ ፡ ጊዜ ፡ በስዊዘርላንድ ፡ በኩል ፡
ወደ ፡ ለንደን ፡ አምልጧል ።

ማርክስም ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ ኑሮውን ፡ መሠረተ ።
ኤንግልስ ፡ ደግሞ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደገና ፡ እ. ኤ. አ. 1840
ኛዎቹ ፡ ዓ. ም. አካባቢ ፡ ይሠራ ፡ በነበረበት ፡ በማንቸስ
ተር ፡ የንግድ ፡ ኩባንይ ፡ ውስጥ ፡ ጸሐፊ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራ ፡



በኋላም ፡ በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ በሽርክና ፡ ባለመብት ፡
ሆኗል ። ኤንግልስ ፡ እ. ኤ. አ. እስከ 1870 ዓ. ም. ድረስ ፡
ማንቸስተር ፡ ውስጥ ፡ የኖረ ፡ ሲሆን ፡ ማርክስ ፡ ደግሞ ፡ የኖ
ረው ፡ ለንደን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ በ.ራራቁ
ም ፡ በመካከላቸው ፡ የነበረው ፡ የበለፀገ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋ
ወጥ ፡ ሳይቋረጥ ፡ በየቀኑ ፡ ሲጻጻፉ ፡ ኖረዋል ። ሁለቱ ፡ በየ
ጊዜው ፡ በመጻጻፍ ፡ አስተያየቶችና ፡ የምርምር ፡ ውጤቶ
ች ፡ ከመለዋወጣቸውም ፡ በላይ ፡ ሳይንሳዊ ፡ ሶሺያሊዝም
ን ፡ ለመመሥረት ፡ ትብብራቸውን ፡ ቀጥለዋል ። እ. ኤ. አ.
በ 1870 ዓ. ም. ኤንግልስ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ተዛውሮ ፡ ሁለ
ቱም ፡ እጅግ ፡ አድካሚ ፡ የሆነውን ፡ የምሁር ፡ ሥራቸው
ን ፡ ማርክስ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1883 ዓ. ም. ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞ
ት ፡ እስከተለየበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ቀጥለዋል ።
የሁለቱ ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ያስገኘው ፡ ፍሬ ፡ በማርክስ ፡ በ
ኩል ፡ በዘመናችን ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ ስለፖለቲካ ፡ ኤኮኖ
ሚ ፡ የሚያስረዳው «ካፒታል» የተባለው ፡ ሥራ ፡ ሲሆን ፡
በኤንግልስ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ታላላቅና ፡ ትናንሽ ፡ የሆኑ ፡
አያሌ ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ። ማርክስ ፡ የካፒታሊስት ፡ ኤ
ኮኖሚን ፡ የተወሳሰበ ፡ ክስተት ፡ በሥራው ፡ ተንትኖታ
ል ። ኤንግልስ ፡ ደግሞ ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ በቀ
ላሉ ፡ የተጻፉ ፡ ሥራዎች ፡ የታሪክን ፡ ማቴሪያላዊ ፡ ጽንሰ ፡
ሐሳብና ፡ የማርክስን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ቴዎሪ ፡ በተመረኰዘ ፡
መንፈስ ፡ ስለአለፈውና ፡ ስለጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለ
ከቱ ፡ በተለያዩ ፡ ክስተቶችና ፡ ጠቅላላነት ፡ ባላቸው ፡ ሳ
ይንሳዊ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ጽፏል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ከኤንግል
ስ ፡ ሥራዎች ፡ ዱሪንግን ፡ በመቃወም ፡ ስለአቀረበው ፡ ክ
ርክር ፡ አዘል ፡ ሥራ (በፍልስፍና ፡ በተፈጥሮ ፡ ሳይንስና ፡
በሶሺያል ፡ ሳይንሶች ፡ መስክ ፡ ያከናወናቸውን ፡ ሥራዎ
ች)* እንጠቅሳለን ፤ «የቤተሰብ ፤ የግል ፡ ንብረትና ፡ የመንግ

---

* ይህ ፡ እጅግ ፡ የበለፀገና ፡ ትምህርታዊ ፡ የሆነ ፡ መጽሐ

ሥት ፡ አመጣጥ» (ወደ ፡ ሩሲያኛ ፡ ተተርጉሞ ፡ ሴንት ፡ ፒተርቡርግ ፡ ውስጥ ፡ ታተመ ፡ 3 ኛው ፡ እትም ፡ እ. ኤ. አ. በ 1895 ዓ. ም.)«ሉድዊግ ፡ ፎየርባኽ» (ወደ ፡ ሩሲያኛ ፡ የተተረጐመውና ፡ ማብራሪያ ፡ የተጻፈበት ፡ በፕሌኻኖቭ ፤ ጀኔቭ ፤ እ. ኤ. አ. 1892 ዓ. ም.) ስለሩሲያኛ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ አመራር ፡ የተጻፈ ፡ ጽሑፍ (ወደ ፡ ሩሲያ ፡ የተተረጐመው ፡ በጀኔቭ «ሶሺያል-ዴሞክራት» አንደኛና ፡ ሁለተኛ ፡ ቁጥሮች) ስለመኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጉዳይ ፡ የተጻፉ ፡ ተዳናቂ ፡ ጽሑፎች ፡ በመጨረሻ ፡ ስለሩሲያ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ የተጻፉ ፡ ሁለት ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎች («ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ ስለሩሲያ» ወደ ፡ ሩሲያኛ ፡ የተተረጐመው ፡ በዛሱሊች ፤ ጀኔቭ ፤ እ. ኤ. አ. 1894 ዓ. ም.) ማርክስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ የተለየው ፡ ካፒታል ፡ ውስጥ ፡ ላቀረበው ፡ ሰፊ ፡ ሥራ ፡ የመጨረሻውን ፡ ዕልባት ፡ ከማበጀቱ ፡ በፊት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የማርክስ ፡ ሥራ ፡ ረቂቅ ፡ አልቆ ፡ ነበርና ፤ ከዚህ ፡ ዓለምም ፡ በሞት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ጓደኛው ፡ ኤንግልስ ፡ የካፒታልን ፡ ሁለተኛና ፡ ሶስተኛ ፡ ቅጾች ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አድካሚና ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ተረክቦ ፡ ቀጥሏል ። ኤንግልስ ፡ ሁለተኛውን ፡ ቅጽ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1885 ዓ. ም. ሲያሳትም ፡ ሶስተኛውን ፡ ቅጽ ፡ ደግሞ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1894 ዓ. ም. አሳተሚል ። (የአራተኛውን ፡ ቅጽ ፡ ዝግጅት ፡ አልጨረሰም) እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ቅጾች ፡ እጅግ ፡ አያሌ ፡ የሆነ ፡ ሥራና ፡ ድካም ፡ የሚጠይቁ ፡ ነበር ። የአውስትሪያው ፡ ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራት ፡ አድለር ፡ በትክክል ፡ እንደገለጸው ፡ ኤን

---

ፍ ፡ ነው ። የሚያሳዝነው ፡ ወደ ፡ ሩሲያ ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐመው ፡ ስለሶሺያሊዝም ፡ ታሪካዊ ፡ ዕድገት ፡ የሚገልጸው ፡ ጥቂት ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው ። (የሳይንሳዊ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ዕድገት ፡ ሁለተኛ ፡ እትም ፡ ጀኔቭ ፡ እ. ኤ. አ. 1892 ዓ. ም.)



ግልስ «የካፒታልን» ሁለተኛና ፡ ሶስተኛ ፡ ቅጾች ፡ ጨርሶ ፡ በማሳተም ፡ ጓደኛው ፡ ለነበረው ፡ ታላቅ ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ግርማ ፡ ያለውን ፡ ሀውልት ፡ ያቆመለት ፡ ሲሆን ፡ በዚህም ፡ ሀውልት ፡ ላይ ፡ ሳያስበው ፡ የራሱን ፡ ስም ፡ በማይፋቅ ፡ ሁኔታ ፡ ቀርጾታል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ « የካፒታል » ቅጾች ፡ በርግጥ ፡ የሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ናቸው — የማርክስና ፡ የኤንግልስ ። ከጥንት ፡ አፈ ፡ ታሪኮች ፡ የሚነገሩ ፡ ስለ ፡ ወዳጅነት ፡ ብዙ ፡ ልብ ፡ የሚነኩ ፡ ምሳሌዎች ፡ አሉ ። የአውሮፓ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መመሪያቸው ፡ የሆነው ፡ ርዕዮተ ፡ ዓለማቸው ፡ የተፈጠረው ፡ ልብ ፡ ከሚነኩ ፡ የጥንት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የወዳጅነት ፡ ታሪኮች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠና ፡ የጠነከረ ፡ ወዳጅነት ፡ ባላቸው ፡ ምሁራንና ፡ ታጋዮች ፡ መሆኑን ፡ ዛሬ ፡ ሊናገሩ ፡ ይችላሉ ። ኤንግልስ ፡ ሁል ጊዜና ፡ በጠቅላላውም ፡ በትክክል ፡ ራሱን ፡ ከማርክስ ፡ በታች ፡ ያውል ፡ ነበር ። ኤንግልስ ፡ ለአንድ ፡ ጓደኛው ፡ ሲጽፍ «ማርክስ ፡ በሕይወት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሚናዬ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የተወሰነ ፡ ነው» ብሏል ። ማርክስ ፡ በሕይወት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜና ፡ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ ኤንግልስ ፡ ለርሱ ፡ የነበረው ፡ ፍቅርና ፡ ክብር ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ። ይህ ፡ ጠንካራ ፡ ታጋይና ፡ በግል ፡ ጥቅምና ፡ ምቾት ፡ ሳይታለል ፡ ለሌሎች ፡ ያስብ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በርግጥ ፡ ተወዳጅ ፡ ነፍስ ፡ የነበረው ፡ ነው ።

እ. ኤ. አ. 1848-49 ዓ. ም. ከነበረው ፡ ንቅናቄ ፡ በኋላ ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ በስደት ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ራሳቸውን ፡ በሳይንሳዊ ፡ ምርምር ፡ ብቻ ፡ አልገቱም ። እ. ኤ. አ. 1864 ዓ. ም. ማርክስ ፡ የኢንተርናስዮናል ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበርን ፡ አቋቁሞ ፡ ይህን ፡ ማኅበር ፡ ለአስር ፡ ዓመት ፡ መርቷል ። ኤንግልስም ፡ በዚህ ፡ ማኅበር ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ተሳታፊ ፡ ሆኖአል ። የኢንተርናስዮናል ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ በማርክስ ፡ ዕቅድ ፡ መሠረት ፡ የመላውን ፡ ሀገሮች ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ ያስተባበረ ፡ ሲሆን ፡ በሠራተኛው ፡ መደብ ፡

ንቅናቄ ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋጽኦ ፡ አለው ። የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ማኅበር ፡ እ. ኤ. አ. 1870 ዎቹ ፡ ዓ. ም. ቢዘጋም ፡ ቅሉ ፡ የማርክስና ፡ የኤንግልስ ፡ የአስተባባሪነት ፡ ሚና ፡ አላቋረጠም ። እንዲያውም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ የመንፈስ ፡ መሪዎች ፡ በመሆን ፡ የነበራቸው ፡ ከፍተኛ ፡ አስተዋጽኦ ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ባለማቋረጥ ፡ በመቀጠሉ ፡ የነሱም ፡ ከፍተኛነት ፡ ቀጥሏል ። ማርክስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ኤንግልስ ፡ የአውሮፓ ፡ ሶሺያሊስቶች ፡ መሪና ፡ አማካሪ ፡ በመሆን ፡ ብቻውን ፡ ቀጥሏል ። የኤንግልስ ፡ ምክርና ፡ አመራር ፡ የመንግሥት ፡ ጭቆና ፡ ቢፈጸምባቸውም ፡ ኃይላቸው ፡ በፍጥነት ፡ እየተጠናከረ ፡ ይሔድ ፡ በነበረው ፡ በጀርመን ፡ ሶሺያሊስቶችና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተው ፡ በነበሩት ፡ እንደስፓኝ ፤ እንደሩማንያና ፡ እንደሩሲያ ፡ በነበሩት ፡ አገሮች ፡ እንደራሴዎች ፡ ይፈለግ ፡ ነበር ። የእነዚህ ፡ አገሮች ፡ እንደራሴዎች ፡ የመጀመሪያ ፡ ሙከራ ፡ ለማድረግ ፡ ዕቅድ ፡ ነበራቸው ። ሁሉም ፡ በዕድሜ ፡ ከገፋው ፡ ከኤንግልስ ፡ የበለፀገ ፡ ልምድና ፡ ጥበብ ፡ ይቀስሙ ፡ ነበር ።

ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ሁለቱም ፡ የሩሲያ ፡ ቋንቋ ፡ ያውቁ ፡ ነበር ። የሩሲያን ፡ አብዮታዊ ፡ ንቅናቄ ፡ በቅን ፡ አስተያየት ፡ ይመለከቱት ፡ የነበረ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከሩሲያ ፡ አብዮተኞች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ነበራቸው ። ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ሶሺያሊስቶች ፡ የሆኑት ፡ ዴሞክራት ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ በፖለቲካ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የነበራቸው ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ ጥላቻ ፡ እጅግ ፡ የጠነከረ ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ የነበራቸው ፡ ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ የፖለቲካ ፡ ስሜት ፡ በፖለቲካ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥልጣንና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ጭቆና ፡ መካከል ፡ ስለአለው ፡ ግንኙነት ፡ ከነበራቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የቴዎሪ ፡ ዕውቀትና ፡ ስለሕይወት ፡ ከነበራቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ ተጣምሮ ፡ ወደር ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ በፖለቲካ ፡ በኩል ፡ ንቁ ፡ አድርጓቸዋ



ል ። ጭብጥ ፡ የማይሞሉት ፡ የሩሲያ ፡ አብዮተኞች ፡ በሩሲያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ የጀግንነት ፡ ትግል ፡ በእነዚህ ፡ በወጣላቸው ፡ አብዮተኞች ፡ ዘንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ስሜት ፡ ያሳደረው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጊዜያዊ ፡ ለሆነ ፡ ለኤኮኖሚ ፡ ጥቅም ፡ ብሎ ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊና ፡ አስቸኳይ ፡ ከሆነው ፡ የፖለቲካ ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ ከሚደረገው ፡ ከሩሲያ ፡ ሶሺያሊስቶች ፡ ተግባር ፡ ለመሸሽ ፡ የነበረው ፡ ዝንባሌ ፡ ያጠራጠራቸው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ቁም ፡ ነገሩን ፡ ማለት ፡ የኅብረተሰብን ፡ አብዮት ፡ እንደመክዳት ፡ የሚቆጠር ፡ መሆኑ ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ተገምቷል ። «የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ነፃ ፡ መውጣት ፡ የራሱ ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ተግባር ፡ መሆኑን» ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ባለማቋረጥ ፡ አስተምረዋል ። ወዝ ፡ አደሩ ፡ ከኤኮኖሚ ፡ ጭቆና ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ አንዳንድ ፡ የፖለቲካ ፡ መብቶች ፡ በትግል ፡ መጐናፀፍ ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ማርክስና ፡ ኤንግልስ ፡ ሩሲያ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጠር ፡ የፖለቲካ ፡ አብዮት ፡ ለምዕራብ ፡ አውርፓ ፡ ሥራተኞች ፡ ንቅናቄ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ተመልክተዋል ። ወሰን ፡ የሌለው ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ገዥ ፡ ትገዛ ፡ የነበረችው ፡ ሩሲያ ፡ ለአውሮፓ ፡ አድኃሪያን ፡ ተግባር ፡ መከታ ፡ ነበረች ። እ. ኤ. አ. በ 1870 ዓ. ም. የተኪያሔደው ፡ ጦርነት ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ በፈረንሳይና ፡ በጀርመን ፡ መካከል ፡ ጭቅጭቅ ፡ ትፈጥር ፡ ለነበረችው ፡ ሩሲያ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጠቃሚ ፡ አጋጣሚ ፡ የፈጠረ ፡ ሲሆን ፡ የሩሲያን ፡ የአድኃሪነት ፡ አቋም ፡ ይበልጥ ፡ አጠናክሮታል ። ፖላንድን ፤ ፊንላንድን ፤ ጀርመንን ፤ አርሜንያንና ፡ ሌሎች ፡ አነስተኛ ፡ ብሔሮችን ፡ ለመጨቆንና ፡ ወይንም ፡ ፈረንሳይንና ፡ ጀርመንን ፡ ለማጣላት ፡ ፍላጐት ፡ የሌላት ፡ ነፃዋ ፡ ሩሲያ ፡ ብቻ ፡ ነች ። ዘመናዊ ፡ አውሮፓን ፡ ከጦርነት ፡ ነፃ ፡ አውጥታ ፡ የአውሮፓን ፡ አድኃሪ ፡ ኃይሎች ፡ በማድ

ከም ፡ የአውሮፓን ፡ የሠራተኞች ፡ መደብ ፡ ለማጠንከር ፡ የምትችለው ። በምዕራብም ፡ ለሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ዕድገት ፡ ሲባል ፡ ሩሲያ ፡ ውስጥም ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ የፖለቲካ ፡ መብት ፡ እንዲመሠረት ፡ ኤንግልስ ፡ በጽኑ ፡ የተመኘው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ኤንግልስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ በመለየቱ ፡ ሩሲያውያን ፡ አብዮተኞች ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጃቸውን ፡ አጥተዋል ።

ታላቁን ፡ ታጋይና ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ መምህር ፡ ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ ለዘለዓለም ፡ እናስታውስ!

በ 1895 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. የተጻፈ ።   ቅጽ ፡ 2 ፤ ገጾች ፡ 1-14

## ማብራሪያዎች ።

[1] «የማርክሲዝም ፡ ሶስቱ ፡ ምንጮች ፡ እና ፡ ሶስቱ ፡ የተዋሀዱ ፡ አካሎች» የተባለው ፡ ጽሑፍ ፡ በሌኒን ፡ የተደረሰው ፡ ለካርል ፡ ማርክስ ፡ 30 ኛው ፡ ዓመት ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ።

ገጽ ፤ ፳

[2] ሜንሼቪኮች — በሩሲያ ፡ የሶሺያል ፡ ዴሞክራቲክ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ውስጥ ፡ የንዑስ ፡ ከበርቴ ፡ አድርባዮች ፡ መስመር ፡ ተከታዮች ። ሜንሼቪኮች ፡ መጠሪያቸውን ፡ ያገኙት ፡ እ.ኤ.አ. በ 1903 ዓ. ም.በ 2 ኛው ፡ የሩሲያ ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ፓርቲ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የፓርቲው ፡ ማዕከላዊ ፡ ኮሚቴ ፡ ሲመረጥ ፡ አነስተኛ ፡ ድምጽ (አነስተኛ — «ሜንሺንስትቮ» ከሚባለው ፡ የሩሲያንኛ ፡ ቃል) በማግኘታቸው ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በሌኒን ፡ የሚመሩት ፡ አብዮታውያን ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራቶች ፡ ከፍተኛ ፡ ድምጽ ፡ በማግኘታቸው ፡ ቦልሼቪኮች (ከፍተኛ — «ቦልሺንስትቮ» ከሚባለው ፡ የሩሲያንኛ ፡ ቃል) ተብለዋል ።

እ. ኤ. አ. ከ 1917 ዓ. ም. የየካቲት ፡ አብዮት ፡ በኋላ ፡ ሜንሼቪኮች ፡ በቡርዥዋው ፡ ጊዜያዊ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በመሳተፍ ፤ መንግሥቱ ፡ የሚከተለውን ፡ የኢምፔሪያሊስታዊ ፡ ፖለቲካ ፡ በመደገፍ ፡ የሚያድገውን ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ መደብ ፡ አብዮት ፡ በመቃወም ፡ ታግለዋል ።

ከታላቁ ፡ የጥቅምት ፡ የሶሺያሊስት ፡ አብዮት ፡ በኋላ ፡ ሜንሼቪኮች ፡ በግልጽ ፡ ወደ ፡ ፀረ-አብዮት ፡ መንደር ፡ ጠቅለው ፡ በመግባት ፤ ሴራና ፡ ቅዋሜን ፡ በማዘጋጀትና ፡ ተሳታፊም ፡ በመሆን ፡ የሶቪዬትን ፡ ሥልጣን ፡ ለመገልበጥ ፡ አልመው ፡ ነበር ።

ገጽ ፤ ፲፯

[3] እ. ኤ. አ. በ 1914 ዓ. ም. ለግራናት ፡ ኢንሳይክሎፒድያ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በተጻፈው ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ሌኒን ፡ ስለማርክስና ፡ ስለኤንግልስ ፡ ጽሑፎችና ፡ በማርክሲዝም ፡ ላይ ፡ ስለተደረሱት ፡ መጽሐፍቶች ፡ ያትታል ። ይህ ፡ ሐተታ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አልታተመም ።

ገጽ ፤ ፲፱

[4] እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. በየካቲት ፡ ወር ፡ የተኪያሔደው ፡ የፈረንሳይ ፡ ቡርዥዋ ፡ አብዮት ።

ገጽ ፤ ፳፩

[5] እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. በመጋቢት ፡ ወር ፡ የጀመረው ፡ የጀርመንና ፡ የአውስትሪያ ፡ የቡርዥዋ ፡ አብዮት ።

ገጽ ፤ ፳፩

[6] እ. ኤ. አ. በ 1848 ዓ. ም. ፈረንሳይ ፡ ውስጥ ፡ የረቀቀውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሪፑብሊኩ ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ አብዛኞቹ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ በማንቋሸሽ ፡ ስለአልተቀበሉት ፡ ፓሪስ ፡ ውስጥ «ጋራ» ፓርቲ ፡ በተባለው ፡ የንዑስ ፡ ከበርቴ ፡ የፖለቲካ ፡ ድርጅት ፡ መሪነት ፡ የሕዝብ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ተደርጎ ፡ ተበትኖአል ።

ገጽ ፤ ፳፪



[7] ፓሪስ ፡ ኮሙን — የፓሪስ ፡ ሠራተኞች ፡ እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም. ባኪያሔዱት ፡ አመጽ ፡ ያቋቋሙት ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ አብዮታዊ ፡ መንግሥት ፡ ሲሆን ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተቋቋመው ፡ የወዝ ፡ አደሩ ፡ አምባ ፡ ገነንነት ፡ ነው ። በሥልጣን ፡ ላይ ፡ የቆየው ፡ መጋቢት ፡ 18 ቀን ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 28 ቀን ፡ ድረስ ፡ ለ 72 ቀናት ፡ ነው ።

ገጽ ፤ ፳፬

[8] የቀድሞው ፡ መንግሥት ፡ እንደገና ፡ ሥልጣን ፡ መያዝ (la Restauration) — በፈረንሳይ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ (እ. ኤ. አ. 1814-1830 ዓ. ም.) የነበረ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሲሆን ፡ በፈረንሳይ ፡ ቡርዥዋ ፡ አብዮት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1792 ዓ. ም. ከሥልጣን ፡ ተወግዶ ፡ የነበረው ፡ የቦርቦን ፡ ንጉሣዊ ፡ አገዛዝ ፡ እንደገና ፡ ሥልጣን ፡ የያዘበት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ገጽ ፤ ፴፫

[9] ጽሑፉ ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1815 ዓ. ም. ጀምሮ ፡ በአውስትሪያ ፤ በፕሩስያና ፡ በሩሲያ ፡ የጋራ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ የሆነውን ፡ የክራኮቭ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ አመጽ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የአመጹ ፡ ተካፋዮች ፡ የፌውዳልን ፡ የሞያ ፡ አገልግሎት ፡ በመሻርና ፡ መሬትን ፡ ከባለእርስቶች ፡ ያለካሣ ፡ ነጥቆ ፡ ለገበሬዎች ፡ በመስጠት ፡ መግለጫ ፡ ያወጣ ፡ አንድ ፡ ብሔራዊ ፡ መንግሥት ፡ አቋቁመው ፡ ነበር ። በሌሎችም ፡ መግለጫዎቹ ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ በከፍተኛ ፡ መጠን ፡ የሚከፈልባቸው ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ማቋቋሙንና ፡ ለዜጎቹ ፡ በሙሉ ፡ ዕኩልነትን ፡ መደንገጉን ፡ አውጅዋል ። ይህ ፡ በብሔራዊ ፡ ነፃነት ፡ ስም ፡ የተኪያሒያደው ፡ አመጽ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተደምስሷል ።

ገጽ ፤ ፳፱

10 ዩንከር — የፕሩስያ ፡ የመሳፍንት ፡ ዘር ፡ የሆነ ፡ ባለእ
ርስት ።

ገጽ ፤ ፸፩

11 የተለየ ፡ ፀረ-ሶሻሊስት ፡ ሕግ ፡ በጀርመን ፡ የታወጀው ፡ እ. ኤ. አ. በ 1878 ዓ. ም. በቢስማርክ ፡ መንግሥት ፡ ሲሆን ፤ ዓላማውም ፡ የሠራተኛውን ፡ መደብና ፡ የሶሺያሊስትን ፡ ንቅናቄዎች ፡ ለመግታት ፡ የታቀደ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሕግ ፡ የሶሺያል-ዴሞክራሲ ፡ ድርጅቶችና ፡ የሰፊው ፡ ሕዝብ ፡ የሞያተኞች ፡ ድርጅቶች ፡ በሙሉና ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ጋዜጦች ፡ ታግደዋል ። ሶሺያሊስት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ ተወርሰዋል ። ሶሺያል-ዴሞክራቶች ፡ ተሰቃይተዋል ፤ ስደትም ፡ ሄደዋል ። እ. ኤ. አ. በ 1890 ዓ. ም. ተቆጥቶ ፡ በተነሳው ፡ በሰፊው ፡ ሕዝብ ፡ ሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ተጽዕኖ ፡ ሕጉ ፡ ተሽሯል ።

ገጽ ፤ ፸፪

12 በሩሲያ ፡ ባለቅኔ ፡ በኒኮላይ ፡ ኔክራሶቭ ፡ ከተደረሰው «የዶብሮሉቦቭ ፡ መታሰቢያ» ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተጠቀሱ ፡ መሥመሮች ፡ ናቸው ።

ገጽ ፤ ፸፫

## የስሞች ፡ ማብራሪያ ።

ህዩም ፤ ዴቪድ (Hume) (እ. ኤ. አ. 1711-1776 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ ፈላስፋ ፡ ሲሆን ፡ ሐሳባዊ ፡ አግኖስቲክ ፤ የታሪክ ፡ አዋቂ ፤ ኢኮኖሚስት ፡ ነበር ።

ገጽ ፡ ፳፯

ሆሊኦክ ፤ ጆርጅ ፡ ጃኮብ (Holyoake) (እ. ኤ. አ. 1817-1906 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ የኮኦፐራቲቭ ፡ ንቅናቄ ፡ መሪና ፡ የጥገና ፡ ለውጥ ፡ ደጋፊ ።

ገጽ ፡ ፳፯

ሊብክነኽት ፤ ዊልኼልም (Liebknecht) (እ. ኤ. አ. 1826-1900 ዓ. ም.) — የታወቀ ፡ የጀርመንና ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ መሪ ፤ ከጀርመን ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ፓርቲ ፡ መሥራቾችና ፡ መሪዎች ፡ አንዱ ፡ የነበረ ፤ በመጀመሪያው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ በሰፊው ፡ የተካፈለና ፡ ሁለተኛውንም ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ ለመመሥረት ፡ ከፍተኛ ፡ ጥረት ፡ ያደረገ ።

ገጽ ፡ ፸፩

ላሳል ፤ ፌርዲናንድ (Lassale) (እ. ኤ. አ. (1825-1864 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ንዑስ ፡ ከበርቴ ፡ ሶሺያሊስት ። የመላው ፡ ጀርመናውያን ፡ የወዝ ፡ አደሮች ፡ ማኅበርን ፡ እ. ኤ. አ. በ 1823 ዓ. ም. ላይ ፡ ካቋቋሙት ፡ መካከል ፡ አንዱ ። የዚህ ፡ ማኅበር ፡ መቋቋም ፤ ለወዝ ፡ አደሮች ፡ እንቅስቃሴ ፡ ከፍተኛ ፡ ጠቀሜታ ፡ ነበረው ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ላሳል ፡

የዚህ ፡ ማኅበር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሁኖ ፡ በመመረጡ ፡ ማኅበሩን ፡ የአድርባይነት ፡ አቋም ፡ ሊያስይዘው ፡ በቃ ። የላሳል ፡ ቴዎሬቲካዊና ፡ ፖለቲካዊ ፡ አመለካከት ፡ ፉርሽ ነት ፡ ካርል ፡ ማርክስና ፡ ፍሬደሪክ ፡ ኤንግልስ ፡ በሚገባ ፡ አጋልጠውት ፡ ነበር ።

ገጽ ፤ ፳፫ ፤ ፸፩

ላፋርግ ፤ ላኡራ (Lafargue) (እ. ኤ. አ. 1845-1911 ዓ. ም.) — ፈረንሳይ ፡ ውስጥ ፡ በሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ የታወቀች ፤ የካርል ፡ ማርክስ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነች ።

ገጽ ፡ ፳፮

ሎንጌ ፤ ጄኒ (Longuet) (እ. ኤ. አ. 1844-1883 ዓ. ም.) — በኢንተርናስዮናል ፡ የሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ በጽኑ ፡ የተሳተፈች ፡ የካርል ፡ ማርክስ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሴት ፡ ልጅ ።

ገጽ ፡ ፳፮

ሎንጌ ፤ ሻርል (Longuet) (እ. ኤ. አ. 1839-1903 ዓ. ም.) — በፈረንሳይ ፡ የሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ ተካፋይ ፡ የነበ ረው ፤ ጋዜጠኛ ።

ገጽ ፡ ፳፮

ሎንጌ ፤ ዣን (Longuet) (እ. ኤ. አ. 1876-1938 ዓ. ም.) — የፈረንሳይ ፡ ሶሺያሊስት ፡ ፓርቲና ፡ የሁለተኛው ፡ ኢንተር ናስዮናል ፡ መሪ ፤ ጸሐፊ ፤ የቻርልስ ፡ ሎንጌና ፡ የጄኒ ፡ ማር ክስ ፡ ልጅ ።

ገጽ ፤ ፳፮

ሔግል ፤ ጌኦርግ ፡ ዊልኼልም ፡ ፍሬደሪክ (Hegel) (እ. ኤ. አ. 1770-1831 ዓ. ም.) — ከፍተኛ ፡ የጀርመን ፡ ፈላስፋ ፤ ነባራዊ ፡ ሐሳባዊና ፡ የጀርመን ፡ ቡርዧዋ ፡ ርዕዮተ ፡ ዓለም ፡



ዶጋፊ ፡ ነበር ። የዲያሌክቲክስ ፡ ትምህርት ፡ በይበልጥ ፡ ያጠናከረና ፡ ያስፋፋ ፡ ሰው ፡ ነው ። ማርክስና ፡ ኤንግ ልስ ፡ የሔግልን ፡ ሐሳባዊ ፡ የዲያሌክቲክስ ፡ ሥራ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አስተሳሰብና ፡ የነባራዊውን ፡ ዓለም ፡ ዕድገት ፡ ጠቅ ላላ ፡ ሕጎችን ፡ ወደሚገልጸው ፡ ማቴሪያሊስት ፡ ዲያሌ ክቲክስ ፡ ለውጠውታል ።

ገጽ ፤ ፯ ፤ ፲፯ ፤ ፲፰ ፤ ፳ ፤ ፳፯-፳፰ ፤ ፴-፴፪ ፤ ፸፮ ፤ ፸፯

ሚኚየ ፤ ፍራንሷ (Mignet) (እ. ኤ. አ. 1796-1884 ዓ. ም.) — የፈረንሳይ ፡ ቡርዧዋ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ ሲሆን ፡ ድርሰቶቹ ፡ በሊበራል ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ነበሩ ።

ገጽ ፡ ፴፰

ማርክስ ፤ ሄንሪሀ (Marx) (እ. ኤ. አ. 1782-1838 ዓ. ም.) — የካርል ፡ ማርክስ ፡ አባት ፡ ጠበቃ ፡ የነበረ ፡ በኋላም ፡ ትሬ የር ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፡ የሊበራል ፡ አስተያየት ፡ የነበረው ።

ገጽ ፡ ፲፯

ማርክስ-አቬሊንግ ፤ ኤልያኖር (Marx-Aveling) (እ. ኤ. አ. 1855-1898 ዓ. ም.) — በእንግሊዝና ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሠራተኛው ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ በጽኑ ፡ የተካፈለች ፡ የካ ርል ፡ ማርክስ ፡ የመጨረሻ ፡ ሴት ፡ ልጅ ።

ገጽ ፡ ፳፮

ማርክስ ፤ ካርል (Marx) (እ. ኤ. አ. 1818-1883 ዓ. ም.) — የሳይንሳዊ ፡ ኮሙኒዝም ፡ አባት ፤ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ መሪና ፡ መምሕር ።

ገጽ ፤ ፮-፹፰

ማርክስ (ፎን ፡ ቬስትፋለን) ጄኒ (Marx, von Westphalen)

(እ. ኤ. አ. 1814-1881 ዓ. ም.) — የካርል ፡ ማርክስ ፡ ባለ ቤት ፤ ታማኝ ፡ ወዳጅና ፡ የሥራ ፡ ጓድ ።

ገጽ ፤ ፲፱ ፡ ፳፭

ማዚኒ ፤ ጁዜፔ (Mazzini) (እ. ኤ. አ. 1805-1872 ዓ. ም.) — ከፍተኛ ፡ አቋም ፡ የነበረው ፡ ኢጣሊያዊ ፡ አብዮተኛ ፤ ቡርዥዋ ፡ ዴሞክራት ፡ የነበረ ፤ ከኢጣሊያ ፡ ብሔራዊ ፡ የነፃነት ፡ ንቅናቄ ፡ መሪዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነ ፡ ኢጣሊያን ፡ ነፃ ፡ የቡርዥዋ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ለማድረግ «ከሥር» ለማስ ተባበር ፡ ፕሮግራም ፡ ያወጣ ፡ ነው ። በማዚኒ ፡ አስተሳሰብ ፡ ዋናው ፡ የትግል ፡ መንገድ ፡ አመጽ ፡ ነው ። የገበሬውን ፡ ፍላጐት ፡ ችላ ፡ በማለት ፡ ሴራንና ፡ አመጽን ፡ ሲከታተል ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ ነው ። ማዚኒ «ሞያንና ፡ ካፒታልን ፡ በማዋሀድ» የሠራተኛውን ፡ ችግር ፡ ለመፍታት ፡ ተምኔታዊ ፡ የሆነ ፡ የንዑስ ፡ ከበርቴ ፡ ሐሳብ ፡ የለፈፈ ፡ ሰው ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፳፫

ሞሌሾት ፤ ዣኮብ (Moleschott) (እ. ኤ. አ. 1822-1893 ዓ. ም.) — ፊዚዮሎጂስት ፡ የነበረ ፡ የስድ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ እንደራሴዎች ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፳፱

ሞስት ፤ ዮሐን ፡ ዮዘፍ (Most) (እ. ኤ. አ. 1846-1906 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራት ፡ የነበረ ፡ በኋላም ፡ አናርኪስት ፡ የሆነ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1878 ዓ. ም. የፀረ-ሶሺያሊስት ፡ ሕግ ፡ እንደታወጀ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ የተሰደደና ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ሔዶ ፡ የሥርዓተ ፡ አልበኛነት ፡ ፕሮፓጋንዳውን ፡ የቀጠለ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፴፪

ሩጌ ፤ አርኖልድ (Ruge) (እ. ኤ. አ. 1802-1880 ዓ. ም.) —



ጀርመናዊ ፡ ጸሐፊ ፤ ወጣት ፡ የሔግል ፡ ፈላስፋ ፡ ተከታይና ፡ ተስፈንጣሪ ፡ ቡርዥዋ ፡ የነበረ ፡ ነው ።

ገጽ ፤ ፲፱ ፤ ፳ ፤ ፹፩

ሪካርዶ ፤ ዴቪድ (Ricardo) (እ. ኤ. አ. 1772-1823 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ ኤኮኖሚስት ፤ የታወቀ ፡ የክላሲካል ፡ ቡርዥዋ ፡ ፖለቲካዊ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ወኪል ።

ገጽ ፤ ፱ ፤ ፶፫

ሮድቤርቱስ-ያጌጾቭ ፤ ዮሐን ፡ ካርል (Rodbertus-Jagetzow) (እ. ኤ. አ. 1805-1875 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ስድ ፡ ኤኮኖሚስት ፡ ከፕሩስያ ፡ «የመንግሥት ፡ ሶሺያሊዝም» ቴዎሪ ፡ አፍላቂዎች ፡ አንዱ ፡ የነበረ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፶፫

ስሚት ፤ አዳም (Smith) (እ. ኤ. አ. 1723-1790 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ ኤኮኖሚስትና ፡ የታወቀ ፡ የክላሲካል ፡ ቡርዥዋ ፡ የፖለቲካ ፡ ኤኮኖሚ ፡ እንደራሴ ፡ የነበረ ።

ገጽ ፤ ፱ ፤ ፵፯

ሻፔር ፤ ካርል (Schapper) (እ. ኤ. አ. 1812-1870 ዓ. ም.) — ከፍተኛ ፡ የጀርመንና ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ መሪ ፡ በኮሙኒስት ፡ ኅብረት ፡ ጽኑ ፡ ተሟጋች ፡ የነበረ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1850 ዓ. ም. ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ የተሰደደ ፡ ከኅብረቱ ፡ ተነጣይና ፡ ጀብደኛ ፡ አንጃ ፡ መሪዎች ፡ አንዱ ፡ የነበረ ፡ ሲሆን ፡ ስህተቱን ፡ በመገንዘብ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1856 ዓ. ም. ከማርክስና ፡ ከኤንግልስ ፡ ጋር ፡ ግንኙነቱን ፡ እንደገና ፡ ያደሰ ፡ ሰው ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፭

ሽቴይን ፤ ሎሬንጽ (Stein) (እ. ኤ. አ. 1815-1890 ዓ.

ም.) — ጀርመናዊ ፡ የቡርዥዋ ፡ ዳኛ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ የነበረ ፡ ስድ ፡ ኤኮኖሚስት ።

ገጽ ፡ ፴፫

ቡኽነር ፤ ፍሬደሪክ ፡ ካርል ፡ ክርስቲያን ፡ ሉድዊግ (Büchner) (እ. ኤ. አ. 1824-1899 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ፈላስፋ ፡ የስድ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ እንደራሴዎች ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ።

ገጽ ፡ ፳፱

ቢስማርክ ፤ ኦቶ (Bismarck) (እ. ኤ. አ. 1815-1898 ዓ. ም.) — የፕሩስያና ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣንና ፡ ዲፕሎማት ። የቢስማርክ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የተቆራረጡት ፡ ትንንሽ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥታትን «በደምና ፡ በብረት» አስተባብሮ ፤ በዩንኬር ፡ ፕሩስያ ፡ የበላይነት ፡ አንድ ፡ የጀርመን ፡ ግዛት ፡ መመስረት ፡ ነበር ። እ. ኤ. አ. በጥር ፡ 1871 ዓ. ም. ቢስማርክ ፡ የጀርመን ፡ ግዛት (ኢምፓየር) የረይህ ፡ ቻንስለርነትን ፡ ቦታ ፡ በመያዝ ፤ የመሬት ፡ ከበርቴ-ዩንኬሮችን ፡ ጥቅም ፡ እየጠበቀና ፤ እንደዚሁም ፡ በዩንኬሮችና ፡ በትልልቅ ፡ ቡርዥዋዎች ፡ መካከል ፡ ኅብረትን ፡ ለመመስረት ፡ እየሞከረ ፤ ለሃያ ፡ ዓመታት ፡ የጀርመንን ፡ መላ ፡ የውጭና ፡ የውስጥ ፡ ፖለቲካ ፡ መርቷል ። በሱ ፡ አሳሳቢነት ፡ እ. ኤ. አ. በ 1878 ዓ. ም. በተላለፈው ፡ የተለየ ፡ ፀረ-ሶሺያሊስት ፡ ሕግ ፡ መሰረት ፡ የወዝ ፡ አደሩን ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ አንቆ ፡ ለመግደል ፡ ያደረገው ፡ ሙከራ ፡ አልተሳካለት ። እ. ኤ. አ. በ 1890 ዓ. ም. ይህ ፡ የተለየ ፡ ፀረ-ሶሺያሊስት ፡ ሕግ ፡ ተሽሮአል ። ቢስማርክም ፡ ከሥልጣን ፡ ወረደ ።

ገጽ ፤ ፳ ፤ ፸፩

ባኩኒን ፤ ሚኻኢል (እ. ኤ. አ. 1814-1876 ዓ. ም.) — ሩሲያዊ ፡ አብዮተኛና ፡ የሥርዓተ ፡ አልበኝነት ፡ አፈ ፡ ቀላ



ጤ ፤ እ. ኤ. አ. ከ 1848-1849 ዓ. ም. በጀርመን ፡ በተኪያሔደው ፡ አብዮት ፡ በሰፊው ፡ የተካፈለ ፤ የመጀመሪያው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ አባል ፡ ሲሆን ፡ የዓለምን ፡ የሠራተኛ ፡ መደብ ፡ ንቅናቄ ፡ አመራር ፡ ለመያዝ ፡ በማርክስና ፡ በኤንግልስ ፡ ላይ ፡ የመነጣጠል ፡ ሴራ ፡ ተግባር ፡ ያኪያሔደ ። እ. ኤ. አ. በ 1872 ዓ. ም. ከኢንተርናስዮናል ፡ የተወገደ ።

ገጽ ፤ ፳፫ ፤ ፳፬

ባወር ፤ ብሩኖ (Bauer) (እ. ኤ. አ. 1809-1882 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ የሆነ ፡ ሐሳባዊ ፡ ፈላስፋ ፡ ከከፍተኞቹ ፡ ወጣት ፡ የሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ ተከታዮች ፡ አንዱ ፡ የሆነ ። እንደ ፡ አንድ ፡ ተስፈንጣሪ (ራዲካል) ቡርዥዋ ፡ የጋዜጠኛነት ፡ ሥራ ፡ የጀመረ ፡ እ. ኤ. አ. ከ 1860 ዓ. ም. በኋላ ፡ የቢስማርክ ፡ ተከታይ ፡ የሆነ ።

ገጽ ፤ ፲፯ ፤ ፲፰

ባወር ፤ ኤድጋር (Bauer) (እ. ኤ. አ. 1820-1886 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ጋዜጠኛ ፡ ወጣት ፡ የሔግል ፡ ፍልስፍና ፡ ተከታይ ፤ የብሩኖ ፡ ባወር ፡ ወንድም ።

ገጽ ፡ ፹፩

ቪሊኽ ፤ አውጉስት (Willich) (እ. ኤ. አ. 1810-1878 ዓ. ም.) — በጀርመን ፡ የተኪያሒያደው ፡ አብዮታዊ ፡ ንቅናቄ ፡ አባል ። እ. ኤ. አ. በ 1847 ዓ. ም. የኮሙኒስት ፡ ኅብረት ፡ አባል ፡ የሆነ ፤ እ. ኤ. አ. ከ 1848-1849 ዓ. ም. ድረስ ፡ በጀርመን ፡ በተኪያሒያደው ፡ አብዮት ፡ ተካፋይ ፡ የነበረ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1850 ዓ. ም. ከኮሙኒስት ፡ ኅብረት ፡ የተነጠለውን ፡ ተገንጣይ ፡ አንጃ ፡ የመራ ።

ገጽ ፡ ፸

ቬስትፋለን ፤ ዤኒ (Westphalen) — ማርክስ ፡ ዤኒን ፡ ተመልከት ።

ቬስትፋለን ፤ ፌርዲናንድ ፡ ኦቶ (Westphalen) (እ. ኤ. አ. 1799-1876 ዓ. ም.) — የፕሩስያ ፡ መንግሥት ፡ መሪ ፤ የፕሩስያ ፡ ፊውዳል ፡ መሣፍንት ፡ እንደራሴ ፤ ሞናርኪስት ፡ የነበረ ፡ ሲሆን ፡ የካርል ፡ ማርክስ ፡ ባለቤት ፡ ወንድም ፡ ነው ። እ. ኤ. አ. ከ1850-1858 ዓ. ም. የፕሩስያ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ነበር ።

ገጽ ፡ ፲፱

ቲየሪ ፤ አጉስተን (Thierry) (እ. ኤ. አ. 1795-1856 ዓ. ም.) — ፈረንሳዊ ፡ ቡርዥዋ ፡ ሊበራል ፡ የሆነ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፤ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የመደብ ፡ ትግል ፡ ያለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ተጽዕኖ ፡ በጥብቅ ፡ ለማስረዳት ፡ ሞክሯል ።

ገጽ ፡ ፴፰

ቲየር ፤ አዶልፍ (Thiers) (እ. ኤ. አ. 1797-1877 ዓ. ም.) — ፈረንሳዊ ፡ የመንግሥት ፡ መሪ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ እ. ኤ. አ. በ 1871 ዓ. ም. በፓሪስ ፡ ኮሙን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብን ፡ የፈጀ ።

ገጽ ፡ ፴፰

አቬሊንግ ፤ ኤድዋርድ (Aveling) (እ. ኤ. አ. 1851-1898 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ ሶሺያሊስት ፤ ጸሐፊ ፤ ኤልያኖር ፡ የተባለችው ፡ የማርክስ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ባሊቤት ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፳፫

ኤንግልስ ፤ ፍሬደሪክ (Engels) (እ. ኤ. አ. 1820-1895 ዓ. ም.) — የሳይንሳዊ ፡ ኮሙኒዝምን ፡ ከመሠረቱት ፡ አንዱ ፤ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ወዝ ፡ አደሮች ፡ መሪና ፡ መምሕር ፤ የማርክስ ፡ ጓደኛና ፡ የሥራ ፡ ጓድ ።

ገጽ ፤ ፯ ፤ ፲፰ ፤ ፳-፳፱ ፤ ፳፯-፴፱ ፤ ፴፮ ፤ ፴፯ ፤ ፵፬ ፤ ፳፫-፳፯ ፤ ፳፰ ፤ ፷-፸፰



ኤፒኩሩስ — ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ 341 እስከ 270 ዓ. ም. የነበረ ፡ ጥንታዊ ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፋ ፤ ማቴሪያሊስት ፤ ፀረ-አማኝ ።

ገጽ ፡ ፲፯

ኩገልማን ፤ ሉድዊግ (Kugelmann) (እ. ኤ. አ. 1830-1902 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራት ፤ የማርክስ ፡ ጓደኛ ። እ. ኤ. አ. በ 1848-1849 ዓመታት ፡ በጀርመን ፡ በተካሄደው ፡ አብዮት ፡ ተካፍሏል ። የአንደኛው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ አባል ።

ገጽ ፡ ፸፱

ካንት ፤ ኢማኑኤል (Kant) (እ. ኤ. አ. 1724-1804 ዓ. ም.) — የጀርመን ፡ ፈላስፋና ፡ የጀርመን ፡ ክላሲካል ፡ ሐሳባዊነት ፡ እንደራሴ ።

ገጽ ፡ ፳፰

ኼክስሊ ፤ ቶማስ ፡ ሔንሪ (Huxley) (እ. ኤ. አ. 1825-1895 ዓ. ም.) — እንግሊዛዊ ፡ ናቹራሊስት ፤ በፍልስፍና ፡ የህዩም ፡ ተከታይ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ በሚያስብበት ፡ ጊዜ ፡ የማቴሪያሊስት ፡ አቋም ፡ ያለው ።

ገጽ ፤ ፳፰ ፤ ፳፱

ዛሱሊች ፤ ቬራ (እ. ኤ. አ. 1849-1919 ዓ. ም.) — በናሮድኒክ ፡ ንቅናቄ ፡ በሰፊው ፡ የተሣተፈችና ፡ ከዚያም ፡ በሩሲያ ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ንቅናቄ ፡ የተሣተፈች ፡ ነች ፤ በኋላ ፡ የሜንሼቪክ ፡ አስተሳሰብ ፡ ደጋፊ ፡ ሆናለች ።

ገጽ ፡ ፹፩

ዞርጌ ፤ ፍሬደሪክ ፡ አዶልፍ (Sorge) (እ. ኤ. አ. 1828-1906 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ሶሺያሊስት ፤ የአሜሪካና ፡

የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሠራተኛ ፡ መደብና ፡ የሶሺያሊስት ፡ ንቅናቄዎች ፡ ከፍተኛ ፡ መሪ ፤ የመጀመሪያው ፡ ኢንተርናስዮናል ፡ አባል ፡ የማርክስና ፡ የኤንግልስ ፡ ወዳጅና ፡ የቅርብ ፡ የሥራ ፡ ጓድ ።

ገጽ ፡ ፳፪

ዱሪንግ ፤ አይገን (Dühring) (እ. ኤ. አ. 1833-1921 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ፈላስፋና ፡ ኤኮኖሚስት ፤ የእሱ ፡ የፍልስፍና ፡ አስተያየቶች ፡ የፖዘቲቪዝም ፡ የሜታፊዚካል ፡ ማቴሪያሊዝምና ፡ የሐሳባዊነት ፡ ቅልቅሎች ፡ ናቸው ።

ገጽ ፤ ፯ ፤ ፹፫

ጊዞ ፤ ፍራንሷ ፡ ፒየር ፡ ጊዮም (Guizot) (እ. ኤ. አ. 1787-1874 ዓ. ም.) — ፈረንሳዊ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊና ፡ የመንግሥት ፡ መሪ ። የቡርዥዋን ፡ የመደብ ፡ ትግል ፡ ቴዎሪ ፡ ከመሠረቱት ፡ አንዱ ።

ገጽ ፡ ፴፰

ፎየርባኽ ፤ ሉድዊግ (Feuerbach) (እ. ኤ. አ. 1804-1872 ዓ. ም.) — ታላቅ ፡ የጀርመን ፡ ማቴሪያሊስት ፤ ፈላስፋ ፡ ከማርክሲዝም ፡ ቀደምት ፡ ፈላስፋዎች ፡ አንዱ ።

ገጽ ፤ ፯ ፤ ፲፯ ፤ ፲፰ ፤ ፳፯-፳፰ ፤ ፹፬

ፎግት ፤ ካርል (Vogt) (እ. ኤ. አ. 1817-1895 ዓ. ም.) — ጀርመናዊ ፡ ባሕርያት ፡ ሳይንቲስት ፤ ከስድ ፡ ማቴሪያሊዝም ፡ ዋና ፡ እንደራሴዎች ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ።

ገጽ ፡ ፳፱

ፕሌኻኖቭ ፤ ጌኦርጊይ (እ. ኤ. አ. 1856-1918 ዓ. ም.) — በሩሲያና ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ የወዝ ፡ አደር ፡ ንቅናቄ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ሰው ። በሩሲያ ፡ የመጀመሪያ ፡ የማርክሲዝም ፡ ፕሮፓጋንዲስት ። እ. ኤ. አ. በ 1883 ዓ. ም. ፕሌኻኖቭ ፡ በጄኔቭ ፡ የወዝ ፡ አደር ፡ ነፃ ፡ አውጪ ፡ የተባለውን ፡ ቡድን ፡ መሠረተ ። ፕሌኻኖቭ ፡ ናሮድኒዝምን ፡ ታግሏል ። በዓለም ፡ አቀፍ ፡ የወዝ ፡ አደር ፡ ንቅናቄ ፡ ውስጥ ፡ ክላሽንትን ፡ ተዋግቷል ። እ. ኤ. አ. በ 1900 ዎቹ ፡ ዓመታት ፡ መጀመሪያ ፡ «ኢስክራ» (ብልጭታ) የተባለውን ፡ ጋዜጣና ፡ «ዛርያ» (ጎህ) የተባለውን ፡ መጽሔት ፡ ከሚያዘጋጁ ፡ አንዱ ፡ ነበር ።

እ. ኤ. አ. ከ 1883 እስከ 1903 ዓ. ም. ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ፕሌኻኖቭ ፡ ማቴሪያሊስታዊ ፡ ርዕዮተ ፡ ዓለምን ፡ በመከላከልና ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ በማስፋፋት ፡ ከፍተኛ ፡ሚና ፡ የተጫወቱ ፡ ብዙ ፡ ሥራዎች ፡ ጽፏል ። ሆኖም ፡ ያኔም ፡ ቢሆን ፡ ከባድ ፡ ስህተቶች ፡ ነበሩት ። እነዚህ ፡ ስህተቶች ፡ ለወደፊት ፡ የሜንሼቪክ ፡ ርዕዮቱ ፡ መሠረቶች ፡ ሆነዋል ። ከሁለተኛው ፡ የሩሲያ ፡ ሶሺያል ፡ ዴሞክራቲክ ፡ የወዝ ፡ አደር ፡ ፓርቲ (ሩ. ሶ. ዴ. ወ. ፓ.) ጉባዔ ፡ በኋላ ፡ ፕሌኻኖቭ ፡ ከአድርባይነት ፡ ጋር ፡ የመታረቅን ፡ አዝማሚያ ፡ ያዘ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከሜንሼቪኮች ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ። በአንደኛው (እ. ኤ. አ. የ 1905 ዓ. ም.) የሩሲያ ፡ አብዮት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጥያቄዎች ፡ በሙሉ ፡ አቋሙ ፡ ሜንሼቪክ ፡ ነበር ። በአንደኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ አቋሙ ፡ ሶሺያል ፡ ሾቪኒስት ። እ. ኤ. አ. ከ 1917 ዓ. ም. የየካቲቱ ፡ የቡርዥዋ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ አብዮት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሩሲያ ፡ ተመልሶ ፡ የቀኝ ፡ አክራሪው ፡ የሜንሼቪኮች ፡ ቡድንን ፡ መርቷል ። ሩሲያ ፡ ወደ ፡ ሶሺያሊዝም ፡ ለመሸጋገር ፡ ገና ፡ አልደረሰችም ፡ በማለት ፡ ቦልሼቪኮችንና ፡ ሶሺያሊስታዊ ፡ አብዮትን ፡ ተቃውሟል ። የጥቅምቱ ፡ ሶሺያሊስት ፡ አብዮትን ፡ አልደገፈም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሶቪዬት ፡ መንግሥት ፡ በመቃወም ፡ በተደረገው ፡ ትግል ፡ አልተካፈለም ።

ገጽ ፤ ፹፬

ፕሩዶን ፤ ፕየር ፡ ጆዘፍ (Proudhon) (እ. ኤ. አ. 1809-1865 ዓ. ም.) — ፈረንሳዊ ፡ ጸሐፊ ፤ ኤኮኖሚስትና ፡ ሶሺኦሎጂስት ። የንዑስ-ቡርዥዋ ፡ አይዲኦሎጂስት ። ሥርዓተ ፡ አልበኛነትን ፡ ከመሠረቱት ፡ አንዱ ።

ገጽ ፤ ፳ ፤ ፳፫

В. И. Ленин

КАРЛ МАРКС И ЕГО УЧЕНИЕ

*на амхарском языке*